Almaz & Bedilu
Sept. 2005

# እግዚአብሔር መለኮት

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ

በመልሳቸው መስፍን (ዶ/ር)

የቅጂ መብት - © መልሳቸው መስፍን - 1996
© Melisachew Mesfin – 2004

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::
ይህን መጽሐፍ ለንግድ ወይም ትርፍ ለሚያስገኝ ሥራ በሙሉም ሆነ በከፊል አባዝቶ መጠቀም አይፈቀድም:: ሆኖም በደራሲው ፈቃድ ለማስተማር አገልግሎት በጥቂትም ሆነ በብዙ አባዝቶ በነጻ ማሰራጨትና መጠቀም ይበረታታል::

በክፍሉ ካልተጠቀሰ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1962 ከታተመው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው::

የመጀመሪያ እትም 1996 ዓ.ም.
First printing - 2004

በመጽሐፉ ላይ አስተያየት ቢኖርዎት ለጸሐፊው በፖ. ሳ. ቁጥር 31716፣ አዲስ አበባ ብሎ መላክ ይቻላል::



# ማስታወሻ

ይህንን መጽሐፍ

ለውድ ባለቤቴ ለብፅዓት ትርፌ

አበረክታለሁ::

## ማውጫ


መቅድም _________________________ 8

መግቢያ _________________________ 9

ምዕራፍ 1. የእግዚአብሔር ሕልውና _________________ 11

1.1 ለእግዚአብሔር ሕልውና የሚቀርቡ ማስረጃዎች ___ 11
1.1.1 የኅሊና ምስክርነት _________________ 11
1.1.2 የተፈጥሮ ምስክርነት _________________ 12
1.1.3 የሰው ልጅ የተፈጥሮ ዝንባሌ _____________ 12
1.2 የእግዚአብሔርን ሕልውና የክህደት መልኮች ______ 13
1.2.1 «እግዚአብሔር የለም» ባይነት ___________ 13
1.2.2 «አምላክ አንድ ሳይሆን ብዙ ናቸው» የሚሉ ____ 14
1.2.3 «እግዚአብሔርን ማወቅ አልችልም» ባይነት ___ 14
1.2.4 «እግዚአብሔር በሁሉ ነው፣ ሁሉ እግዚአብሔር ነው» ባይነት _________________ 15
1.2.5 «እግዚአብሔር ከፈጠረው ሩቅ ነው» ባይነት __ 15

ምዕራፍ 2. እግዚአብሔር ማን ነው? _________________ 16

2.1 እግዚአብሔርን ማወቅ _________________ 16
2.1.1 ስለ እግዚአብሔር በሙሉ መረዳት አይቻልም __ 17
2.1.2 እግዚአብሔርን ማወቅ ይቻላል ____________ 18
2.1.3 እግዚአብሔርን የማወቅ ዓላማ ___________ 19
2.2 እግዚአብሔርን የማወቂያ መንገድ (መገለጥ) ______ 19
2.2.1 አጠቃላይ መገለጥ _________________ 20
2.2.2 ልዩ መገለጥ _________________ 22
2.3 የእግዚአብሔር መሠረታዊ ማንነት _____________ 24
2.3.1 እግዚአብሔር ሕያው አምላክ ነው _________ 24
2.3.2 እግዚአብሔር መንፈስ ነው _______________ 25
2.3.3 እግዚአብሔር እኔነት አለው _______________ 26
2.3.4 እግዚአብሔር ፍቅር ነው _______________ 27
2.3.5 እግዚአብሔር ብርሃን ነው _______________ 27

ምዕራፍ 3. የእግዚአብሔር ስሞች _______ 29

3.1 የብሉይ ኪዳን ስሞች _______ 30
3.1.1 ኤል / ኤሎሂም _______ 30
3.1.2 ያህዌ _______ 32
3.1.3 አዶናይ _______ 34
3.2 የአዲስ ኪዳን ስሞች _______ 34
3.2.1 ቲዎስ _______ 34
3.2.2 ጌታ _______ 35
3.2.3 አባት _______ 35

ምዕራፍ 4. የእግዚአብሔር ባሕርያት _______ 36

4.1 የማይተላለፉ ባሕርያት _______ 37
4.1.1 እግዚአብሔር ራሱ በራሱ የሚኖር ነው _______ 38
4.1.2 እግዚአብሔር አይለወጥም _______ 39
4.1.3 እግዚአብሔር ወሰን የለውም _______ 43
4.2 የሚተላለፉ ባሕርያት _______ 46
4.2.1 የማወቅ ባሕርያት _______ 46
4.2.2 የሞራል ባሕርያት _______ 52
4.2.3 የሁሉ የበላይ / ገዥ፣ ሁሉን ቻይ _______ 57

ምዕራፍ 5. ሥላሴ _______ 60

5.1 የሥላሴ ትምህርት በታሪክ ውስጥ _______ 61
5.2 እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው _______ 66
5.3 ሥላሴ:- በአንድነት - ሦስትነት _______ 67
5.3.1 በብሉይ ኪዳን _______ 68
5.3.2 በአዲስ ኪዳን _______ 71
5.4 የሥላሴ ትምህርት መግለጫ _______ 76
5.4.1 እግዚአብሔር በሦስት አካላት ይኖራል _______ 76
5.4.2 እያንዳንዱ የሥላሴ አካል እግዚአብሔር ነው _______ 78
5.4.3 እግዚአብሔር አንድ ነው _______ 78
5.5 ስለ ሥላሴ ምሳሌያዊ አገላለጾች _______ 79
5.6 የሥላሴ ትምህርት ማጠቃለያ _______ 82
5.6.1 ልዩነቶች _______ 82
5.6.2 በሥላሴ መካከል ያለው ተዛምዶ _______ 85

ምዕራፍ 6. የሥላሴ አካላት _______ 89

6.1 አብ / አባት _______ 89
6.1.1 ወልድ ከአብ ጋር ስላለው ተዛምዶ _______ 89
6.1.2 አብ የፍጥረት ሁሉ አባት _______ 90
6.1.3 እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለው ዝምድና/ አብ የእስራኤል ሁሉ አባት _______ 90
6.1.4 አብ የአማኞች ሁሉ አባት ነው _______ 91

6.2 ወልድ _______ 92
6.2.1 ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው _______ 93
6.2.2 የመለኮት ባሕርይ አለው _______ 100
6.2.3 የመለኮት ሥልጣን አለው _______ 102
6.2.4 አምልኮና ክብር ይገባዋል _______ 105
6.2.5 የወልድን መለኮትነት የሚክዱ ክፍሎች የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች ትንታኔ _______ 107

6.3 መንፈስ ቅዱስ _______ 116
6.3.1 መንፈስ ቅዱስ እኔነት አለው _______ 116
6.3.2 መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው _______ 117
6.3.3 የመንፈስ ቅዱስ ስሞችና መግለጫዎች _______ 119

ምዕራፍ 7. የእግዚአብሔር ሥራዎች _______ 125

7.1 ማቀድ _______ 125

7.2 መምረጥ _______ 126
7.2.1 ሰው ነጻ ፈቃድ አለው _______ 126
7.2.2 እግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣን አለው _______ 127

7.3 መፍጠር _______ 130
7.3.1 የመፍጠር መንገድ _______ 131
7.3.2 የተፈጠረው ሁሉ መልካም ነበር _______ 131
7.3.3 የፍጥረት ዓላማ _______ 132

7.4 መጠበቅ / መንከባከብ ____ 132
7.4.1 የሚያስፈልገውን በመስጠት ____ 133
7.4.2 ከክፉ በመጠበቅ ____ 133
7.4.3 በመምራት ____ 133

አባሪ

አባሪ 1: የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔና የሰው ነጻ ፈቃድ ____ 135

አባሪ 2: TWO VIEWS ON SALVATION AND ETERNAL SECURITY OF THE BELIEVER ____ 144



# መቅድም

እግዚአብሔር ማነው? አጀንዳውስ ምንድን ነው? እኔ ማነኝ? ለምን ተፈጠርኩ? የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ አውቆና በመልሶቹ መመራት ክርስትና ነው። የክርስትና ሀ ሁ. . . እግዚአብሔርን ማወቅና ከእርሱ ጋር በኅብረት መኖር ነው።

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር የነበረው ፊልጶስ ጌታን አንድ ጥያቄ ጠይቆት ነበር። ጥያቄው «ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል» የሚል ነበር። አብን አሳየን ይበቃናል ሲል ምን ማለቱ ነበር? ይህ ጥያቄ ሙሴ እግዚአብሔርን የጠየቀውን ይመስላል። «እባክህ ክብርህን አሳየኝ » (ዘጸ 33:19)።

እግዚአብሔርን ማየት እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ነው። ይህ እውቀት በቂ ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ ነውና።

ስለ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ (Doctrine) የክርስትና እምነት መሠረታዊ ትምህርት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፣ ባሕርይ፣ ሥራና ስለ ሥላሴ የሚያስተምረውን ማወቅና በተረዱት መሠረት መኖር የእውነተኛ ክርስትና መሠረት ሲሆን ይህ ከስህተት ትምህርት ይጠብቃል። የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ይህንኑ ለማስገንዘብ ነው።

ስለ እግዚአብሔር ሕልውና፣ ማንነቱ፣ ስሞቹ፣ ባሕርያቱ ስለ ሥላሴና ስለ እግዚአብሔር ሥራዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው በቅደም ተከተል ቀርቧል።

ዶር መልሳቸው ይህን ትምህርት ያዘጋጀው ትምህርተ መለኮት ለሚማሩ ተማሪዎች፣ በግል ማጥናት ለሚፈልጉና ለሥልጠና አገልግሎት እንዲውል በመሆኑ አቀራረቡ ያተኮረው ዋና ዋና ሀሳቦችን በአጭሩ አቅርቦ በጥቅሶች በመደገፍ የትምህርቱን መጽሐፍ ቅዱሳዊነት በማሳየት ላይ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች በመጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እያገናዘቡ እንዲያጠኑ ይጠበቅባቸዋል።

ዮሐንስ ምዕራፍ 17: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ (ለኛም) የጸለየው ጸሎት ነው። በዚያ ጸሎት እንዲህ ብሏል። «የዘላለም ሕይወትም ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶን ማወቅ ነው» (17:3)። አብንና ወልድን ማወቅ ዋና ነገር ነው። የዚህም መጽሐፍ ቁም ነገር ይህ ነው።

ሚሊዮን በለጠ

# መግቢያ

ስለ እግዚአብሔር ትምህርት (The Doctrine of God /Theology proper) በክርስትና እምነት መሠረታዊ ትምህርት ነው:: ይህ እግዚአብሔር መለኮት:- መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የተሰኘው መጽሐፍ ቀዳሚ ዓላማ አንባብያን ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ባሕሪይ እንዲያውቁ ማገዝ ሲሆን ሁለተኛው ከእግዚአብሔር ማንነትና ከሥላሴ ጋር በተያያዘ ላሉ የስህተት ትምህርቶች መልስ ለመስጠት የሚያስችል አጭር ትንታኔ ለማቅረብ ነው::

በ1983 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀውና አሁን ደግሞ ተሻሽሎ የቀረበው ይህ መጽሐፍ መሠረቱ ስለ ሥላሴ ትምህርት ለመረዳት በግል ያደረግሁት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው:: በተጨማሪ ከአዲስ አበባ ኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ (ኢ.ቲ.ሲ) እና በየጊዜው ካነበብኳቸው በርካታ መጽሐፍት ያገኘኋቸውን ትምህርቶች ያጠቃልላል:: ከተለያዩ መጽሐፍት ያገኘኋቸውን ማስረጃዎችና ማብራሪያዎች ሁሉንም ወደ አማርኛ መልሶ ከማስቀመጥ ይልቅ አንዳንዶቹ የበለጠ ግልጽ ሆነው የሚታዩት በተጻፉበት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደሆነ በማሰብ በዛ ያሉ የግርጌ ማስታወሻዎች በእንግሊዝኛ ቀርበዋል:: ይህ ዓይነቱ አቀራረብ ሀሳቡን አጉልቶ ለመግለጽ ይረዳል በሚል ታሳቢነት የቀረበ ስለሆነ አንባቢዎች ይህንን እንዲረዱለት ጸሐፊው በትሕትና ለማሳሰብ ይወዳል::

መጽሐፉ ሰባት ምዕራፎች አሉት:: የእግዚአብሔር ሕልውና፣ እግዚአብሔር ማን ነው? የእግዚአብሔር ስሞችና የእግዚአብሔር ባሕሪያት የሚሉት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ከምዕራፍ 1 እስከ 4 የቀረቡ ሲሆን ምዕራፍ 5 ስለ ሥላሴ፣ ምዕራፍ 6 ስለ ሥላሴ አካላት ይገልጻሉ:: የመጨረሻው ምዕራፍ 7 ስለ እግዚአብሔር ሥራዎች ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላ 1:12 «... በእግዚአብሔር ዕውቀት እያደጋችሁ» እንደሚል የዚህ መጽሐፍ መልዕክት እኛ ሁላችንም እግዚአብሔርን በማወቅ እናድግ ዘንድ በጌታ ፍቅር ጥሪ ለማድረግ ነው:: ዕድገታችን እርሱን በማወቅ ከእርሱ ጋር መልካም ኅብረት እንዲኖረን፣ ለጌታ እንደሚገባ በመኖር ብዙ ፍሬ እንድናፈራና በሁሉም እርሱን ደስ እናሰኘው ዘንድ ነው::

ይህን መጽሐፍ በኮምፒውተር በማስገባት በዚህ መልክ እንዲወጣ ያደረጉትን ወገኖች ሁሉ አመሰግናለሁ:: ጽሑፉ በረቂቅ ደረጃ እያለ በማንበብ አስተያየት የሰጡትን ወገኖች:- ስምዖን ሙላት (በከፊል)፣ ምሕረቱ ጴጥሮስ፣ ፍጹም መክብብ፣ ተስፋዬ ጋቢሶ፣ አያሌው ተሰማ፣

ንጉሤ ቡልቻ፣ ዝናቡ ገብረ ማርያም እና አለም ባዘዘውን እንዲሁም ለመጽሐፉ መቅድም የጻፈውን ጋሽ ሚሊዮን በለጠን ከልብ አመሰግናለሁ:: እነዚህን ወገኖች እግዚአብሔር አብዝቶ ይበርካቸው እያልሁ መጽሐፉን በሚመለከት ለሚነሱ ማናቸውም ዓይነት ጥያቄዎች ተጠያቂ የሚሆነው ጸሐፊው ብቻ መሆኑን ለአንባብያን ለማሳሰብ እውዳለሁ::

የፈጠረን፣ እንድናውቀውና ከእርሱም ጋር ኅብረት እናደግር ዘንድ ራሱን የገለጠልን እግዚአብሔር ስሙ ይባረክ:: ክብር፣ ምስጋና፣ ውዳሴ፣ አምልኮ ለሕያው አምላካችን ለእግዚአብሔር ይሁን:: የሰማይና የምድር ጌታ እግዚአብሔር ይህን መጽሐፍ ለክብሩና ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ ያድርገው፣ አሜን::



# ምዕራፍ 1. የእግዚአብሔር ሕልውና

እግዚአብሔር ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር ሕያው አምላክ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መኖር ለማስረዳት ወይም ለማረጋገጥ ማስረጃ በማቅረብ አይጀምርም:: እግዚአብሔር ለዘላለም ሕያው በመሆኑ ለእግዚአብሔር ሕልውና ማስረጃ ሳያስፈልገው «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» በማለት ሥራውን በመናገር ይጀምራል (ዘፍ 1፣1):: ሆኖም በዘመናት ውስጥ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕልውና ለመረዳትና ለማስረዳት፣ የተለያዩ ማስረጃዎችን አቅርበዋል:: እነዚህ ማስረጃዎች ከዚህ በታች በ1.1 የቀረቡ ሲሆን ሕልውናውን ላለማመን የሚፈልጉት የሚያቀርቧቸዉን ዋና ምክንያቶች ደግሞ በ1.2 እንመለከታለን::

## 1.1 ለእግዚአብሔር ሕልውና የሚቀርቡ ማስረጃዎች

የእግዚአብሔርን ሕልውና ለማስረዳት ብዙ ተመራማሪዎችና ፈላስፎች የተለያዩ ማስረጃዎችን ለማቅረብ ሞክረዋል:: እነዚህ ማስረጃዎች በአጠቃላይ የሚያስገነዝቡት ከሰው አፈጣጠር፣ ከተፈጥሮ ሥርዓት፣ በዓለም ላይ ከሚታዩት ሁኔታዎችና ከታሪክ አካሄድ በመነሳት የዚህ ሁሉ ድንቅ ነገር ፈጣሪ የሆነ አንድ ኃይል (Super- natural Being) አለ ብሎ ሕልውናውን ማመን ከአእምሮ ውጪ የሆነ አስተሳሰብ አለመሆኑን ነው:: ማስረጃዎቹ ስለ እግዚአብሔር ሕልውና ወይም አምላክ ስለ መኖሩ የሚያሳዩት ነገር ቢኖርም በራሳቸው ግን እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ አያደርሱም:: እነዚህ ማስረጃዎች ጠቀሜታ ሊኖራቸው ቢችልም በማስረጃዎቹ አማካይነት ሰው የእግዚአብሔርን ማንነት ሊረዳና ሕያው እግዚአብሔርን በቀጥታ ወደ ማምለክ ደረጃ ሊደርስ አይችልም:: ማስረጃዎቹን በሦስት በመክፈል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል::

### 1.1.1 የኀሊና ምስክርነት (Ontological Argument)

የሰው ልጅ ሁሉ እግዚአብሔር ወይም ኃያል የሆነ አምላክ ስለመኖሩ በኀሊናው ስለሚያስብና መንፈሳዊ «ረሃብም» ስላለው በሰው ሁሉ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ስሜትና ፍላጎት ወይም መንፈሳዊ ዝንባሌ ያስቀመጠ በእርግጥም እግዚአብሔር አለ ማለት ነው ብሎ የሚገልጽ ማስረጃ ነው:: በዚህ ማስረጃ መሠረት የእግዚአብሔር ሕልውና

የተመሠረተው ሰው ፈጣሪ  አለ ብሎ በማሰቡ ሲሆን ትክክለኛው አስተሳሰብ መሆን ያለበት ግን እግዚአብሔር ሕያው ስለሆነ ወይም ፈጣሪ ስለሆነ ይህ አስተሳሰብ በሰው ሊኖር ቻለ የሚለው መሆን አለበት። ሆኖም «ፈጣሪ አለ» ብሎ የሚቀበል እምነት ሁሉ የሚያመልከው ሕያው እግዚአብሔርን ነው ለማለት አይቻልም።

### 1.1.2 <u>የተፈጥሮ ምስክርነት</u> (Cosmological Argument)

ይህ ማስረጃ ተፈጥሮን (Universe / Cosmos) ያስገኘ ወይም እንዲኖር ያደረገ ጀማሪ (Cause) መኖር አለበት በማለት የእግዚአብሔርን ሕልውና ለማረጋገጥ ይሞክራል። ከተፈጥሮ መገኘት በተጨማሪ ራሱ ተፈጥሮ በማንም ሊታይ የማይችል ዓላማና ሥርዓት ያለው መሆኑ (Teleological Argument) ይህም ለእግዚአብሔር ሕልውና ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው ይላል። አንድ ሰዓት ወድቆ ያገኘ ሰው ይህን ሰዓት ለሆነ ዓላማ የሠራው ሌላ ሠሪ እንዳለ እንደሚገነዘብ[1] ሁሉ የፀሐይን መውጣትና መጥለቅ (የምድር መዞር)፣ የወራትን መፈራረቅ፣ ወዘተ ... በተፈጥሮ ላይ እንዲሆን ያደረገ አንድ ታላቅ ኃያል አምላክ መኖሩን ያመለክታል፤ ስለሆነም እግዚአብሔር አለ ማለት ነው በማለት ያስረዳል። ይሁን እንጂ በዚህም ትንታኔ ቢሆን ትክክለኛው መረዳት መሆን የሚገባው እግዚአብሔር ስላለ (ስለሚኖር) ተፈጥሮ ሥርዓትና ውበት አላት የሚለው አገላለጽ መሆን አለበት። ሁሉ ነገር ጀማሪ (Causer) ካለው እግዚአብሔር አስጀማሪ የሌለው ጀማሪ (an Uncaused Causer) ነውና።

### 1.1.3 <u>የሰው ልጅ የተፈጥሮ ዝንባሌ (Moral/ Anthroplogical Argument)</u>

ሰው በተፈጥሮው የመልካም ሥራ፣ የፍትሕ፣ ወዘተ ... ፍላጐት ስላለው ይህ ስሜት በሰው ሁሉ ውስጥ እንዲኖር ያደረገ አለ፤ ይህም አንድ ኃይል እግዚአብሔር ነው ብሎ ማስረጃውን ያቀርባል። የዚህም ማስረጃ አቀራረብ እንደ ሌሎቹ ማስረጃዎች ሁሉ «እግዚአብሔር ስላለ (ስለሚኖር) ሰውም በእግዚአብሔር ስለተፈጠረ የመልካም ሥራና የፍትሕ ዝንባሌ አለው» የሚል ሳይሆን «በሰው ውስጥ የመልካም ሥራ ዝንባሌ እንዲኖር ያደረገ ፈጣሪ ወይም እግዚአብሔር አለ ማለት ነው» ብሎ የሚያስረዳ ነው ማስረጃነቱ ጠቃሚ ሆኖ ሳለ የእግዚአብሔርን ሕልውና ግን በተገቢ ሁኔታ ሊገለጽ አይችልም።

---

[1] ይህ የሰዓት ምሳሌ ስለ እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራ በተጻፉ በርካታ መጽሐፍት በምሳሌነት ቀርቧል።



ሰዎች ከሚያዩትና ማገናዘብ ከቻሉት በመነሳት ስለ እግዚአብሔር ሕልውና ለመረዳትና ለመግለጽ ቢሞክሩም ክርስቲያኖች ግን የእግዚአብሔርን ሕልውና ለማመን ወይንም ለማስረዳት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ማቅረብ አያስፈልጋቸውም። የእግዚአብሔር ሕልውና የሚታወቀው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ራሱን በተለያየ መንገድ ስለገለጸና አማኙም ይህን እውነት በእምነት ስለተቀበለው ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲጀምር «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» (ዘፍ 1:1) የሚለው ይህ ቃል የእውነት ሁሉ ቁልፍ/ መሠረት ነው። እግዚአብሔርን ለማወቅ ትክክለኛው መንገድ ይህን እውነት በመቀበልና ከዚህ እውነት በመነሳት እግዚአብሔርን በማመን መኖር ነው። በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን መኖር ለማረጋገጥ ማስረጃ በማቅረብ ለማመን ከመሞከር ይልቅ መኖሩን በእምነት ተቀበሎ ለሕልውናው ማስረጃ ማቅረብ ይቀላል። የእግዚአብሔርን መኖር ለመቀበል ማስረጃ በማቅረብ መነሳት የአእምሮ እውቀት እንጂ የልብ እምነት አይሆንም።

## 1.2 <u>የእግዚአብሔር ሕልውና የክህደት መልኮች</u>

እግዚአብሔር ራሱን በተለያየ መንገድ የገለጸ ሕያው አምላክ ሆኖ ሳለ ሕልውናውን የሚክዱና ለክህደታቸውም የተለያዩ አስተሳበቦችን የሚያቀርቡ አሉ። እነዚህን አስተሳሰቦች እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

### 1.2.1 «<u>እግዚአብሔር የለም» ባይነት</u> (Atheism)

ይህ ዓይነት አስተሳሰብ እግዚአብሐኤር የለም ብሎ ያምናል። ይህን አስተሳሰብ የሚከተሉት ይህን በማሰባቸው ከሕያው እግዚአብሔር ሌላ አምላክ[2] ያበጃሉ። የእግዚአብሔርን ሕልውና የሚክድ ሰው ማናቸውም

---

[2] ይህ «አምላክ» አመለካከታቸውንና አስተሳሰባቸውን የሚቃኙበት የመኖራቸው ዋና ዓላማም ይህን አስተሳሰባቸውን እውን ለማድረግ እንደሆነ አድርገው እንዲቆጥሩ የሚያደርጋቸው መርህ ወይም አመለካከት (Ideology) ነው። የዚህ እምነት ግቡና መጨረሻው ምድራዊ ነው። ስለሆነም ሰዎች ያንን ያሰቡትን ወይም የተመኙትን ነገር በጨበጡ ጊዜ በምድር ላይ የመኖራቸው ወይም የመፈጠራቸው ግብ እንደተሟላ አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ እምነት ከምድር ያለፈና ሰማያዊ የሆነ ግብ የለውም።

ነገር በተፈጥሮ ውስጥ በሚገኝ ኃይል እንደሚመራና እንደሚንቀሳቀስ ከዚህም ውጪ የሆነ ምንም ዓይነት ሌላ መለኮታዊ ኃይል እንደሌለ ማመኑ ነው:: ይሁን እንጂ አንድ ሰው እግዚአብሔር የለም ብሎ ለማመንና ለመናገር አስቀድሞ ራሱ ሁሉን ነገር ያወቀ መሆን ይገባዋል:: ያለዚያ እግዚአብሔር የገለጠውን መቀበል ነው!! ሁሉን ነገር ማወቅ ደግሞ የፍጥረታዊ ሰው ችሎታ አይደለም::

የእግዚአብሔርን ሕልውና የሚክዱ ሰዎችም አለመኖሩን መርምረው አውቀውት ሳይሆን «በእምነት» የሚቀበሉት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው «ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል» (መዝ 14:1):: አንዳንዶችም በአፋቸው የእግዚአብሔርን መኖር ቢያምኑም በተግባራቸው ግን ይክዱታል:: በተግባር የማይገለጽ የአፍ ብቻ እምነት ደግሞ እንደ ክህደት ነው::

### 1.2.2 <u>«አምላክ አንድ ሳይሆን ብዙ ናቸው» የሚሉ</u> (Polytheism)

የ«እግዚአብሔር የለም» ባይነት ተቃራኒው ደግሞ ፈጣሪ አንድ ብቻ (Monotheism) ሳይሆን ብዙ «እግዚአብሔሮች» ወይም አማልክት አሉ የሚል (Polytheism) አስተሳሰብ ነው:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ:: «እስራኤል ሆይ ስማ:- አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» (ዘዳ 6:4)::

### 1.2.3 <u>«እግዚአብሔርን ማወቅ አልችልም» ባይነት</u> (Agnosticism)

የእግዚአብሔርንም ሆነ የሌሎችን አማልክት መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ የለም ብለው የሚያምኑት አግኖስቲክስ (Agnostics) ይባላሉ:: አግኖስቲኮች ሁለት ክፍል አላቸው:: አንዱ ክፍል «የእግዚአብሔርን መኖር አናውቅም» የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ «እግዚአብሔር ይኖር እንደሆን ልናውቅ አንችልም» የሚሉ ናቸው:: ይህ መጠራጠር ወይም የክህደት ዓይነት «እግዚአብሔር ይኖር ይሆናል፤ ምናልባት ላይኖርም ይችላል ደግሞም ይህን ማወቅ ከእኔ መረዳት በላይ ነው» ብሎ በእግዚአብሔር ከማመን ራስን ማግለል ነው::

ይሁን እንጂ ራሱን በተለያየ መንገድ የገለጸውን አምላክ ሕልውና አምኖ ለመቀበል አንድ ሰው ከሚያስፈልገው እምነት ይልቅ



ሕልውናውን ለመካድ የበለጠ እምነት ያስፈልገዋል:: የእግዚአብሔር ሕያውነት በፍጥረቱ ሁሉ ግልጽ ሆኖ ይኖራልና (ሮሜ 1:20):: በሐዋ 17:22-27 እንደተጻፈው እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚችልና ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም::

### 1.2.4 <u>«እግዚአብሔር በሁሉ ነው፣ ሁሉ እግዚአብሔር ነው» ባይነት</u> (Pantheism)

Pantheism ከሁለት የግሪክ ቃላት የተገኘ ሲሆን ይህም 'Pan' ማለት ሁሉ (all or everything) እና "theos" ደግሞ እግዚአብሔር (God) ማለት ነው:: ስለዚህ ትርጉሙ «ሁሉ እግዚአብሔር ነው» "God is everything" ወይም "God is all and all is God" ማለት ይሆናል:: ይህ አስተሳሰብ እግዚአብሔር ከተፈጥሮ ጋር አንድ እንደሆነ አድርጎ ያቀርባል:: በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ተለይቶ የማይታይ ወይም የማይገኝ ነው ይላሉ:: ይህ እግዚአብሔርን ከተፈጥሮ ጋር እኩል ማድረግ ወይም ፍጡራን (ሰዎች) እግዚአብሔር መሆን ይችላሉ የሚለው አስተሳሰብ በዚህ ዘመን ካለው የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ትምህርት ጋር ይቀራረባል:: በዚህ አስተሳሰብ መሠረት እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔር ክፍል ተደርጎ ይቆጠራል:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስገነዝበው እግዚአብሔር ከተፈጥሮ ተለይቶ የሚገኝ የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ነው::

### 1.2.5 «<u>እግዚአብሔር ከፈጠረው ሩቅ ነው» ባይነት</u> (Deism)

እግዚአብሔር ፍጥረትን ከፈጠረ በኃላ ከፍጥረት ርቆና የፈጠረውን ፍጥረት እንደፈቀደው ይሁን ብሎ ትቶታል የሚል ነው:: እግዚአብሔር ምናልባት አንዳንድ ጊዜ በልዩ ሁኔታ ፍጥረቱን ሊመራ ይችላል የሚል አስተሳሰብም በዚሁ እምነት ውስጥ አለ:: ይህ አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: እግዚአብሔር የፍጥረቱ ጠባቂና ተንከባካቢ ነውና (ዕብ 1:2-3፣ ሐዋ 14:17፣ ፤7:27)::

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንዳየነው የእግዚአብሔርን ሕልውና ለመረዳት ሰዎች የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች ትክክለኛ ወደሆነው መረዳት የሚጠጉ ቢሆኑም በቂ ማስረጃዎች ግን አይደሉም:: በአንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕልውና ላለመቀበል ሰዎች ብዙ ትንተናዎች ለማቅረብ ሞክረዋል:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩም በፊትና ከፈጠረ በኋላም ያለ፣ ወደፊትም የሚኖር ሕያው አምላክ ነው:: የዚህን ሕያው እግዚአብሔር ማንነት ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ እንመለከታለን::

# ምዕራፍ 2. እግዚአብሔር ማን ነው?

ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠረ (ዘፍ 1:26-27) እና እግዚአብሔርም መታወቅ የሚፈቅድ አምላክ በመሆኑ ሰው ሁሉ ፈጣሪውን ሊያውቅ ይገባል፡፡ ሰው እግዚአብሔርን በራሱ ጥረትና እውቀት ሊያውቀው አይችልም፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር እርሱነቱን ለሰው በመግለጹና ከሰውም ጋር ግንኙነት በማድረጉ ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ ይችላል፡፡

ለሰው ዘር ሁሉ በቦታ፣ በአካባቢ፣ በባሕል፣ በሥልጣኔ ወዘተ ... የማይለወጥ አንድ እርግጠኛ ነገር አለ፡፡ ይህም ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑ ነው (ሮሜ 1:18-19፣ 3:9-18 እና 23)፡፡ ስለሆነም የሰው ዘር ሁሉ ኃጢአት የሚባል (በሽታ) አለበት፡፡ የዚህ በሽታ መድኃኒት ደግሞ አንድ ብቻ ነው፡- እግዚአብሔርን ማወቅ!! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 17:13 ላይ «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት » ብሏል፡፡

እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚችል አምላክ ነው (ሮሜ 1:19)፣ ሰው እግዚአብሔርን ማወቅ ይችላል (1ቆሮ 2:12)፡፡ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከእርሱ ጋር ግንኙነት (Communicate) እንዲያደርግ በሚችልበት ሁኔታ ስለሆነ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ እግዚአብሔርን ማወቅ ምን እንደሆነ፣ የማወቂያ መንገዶችንና ስለ እግዚአብሔር ማንነት በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

## 2.1 እግዚአብሔርን ማወቅ

ሙሴ እግዚአብሔርን ያውቅ ዘንድ ለመነ (ዘጸ 33:13)፤ ዕዝራ ለሕዝቡ እግዚአብሔርን ማወቅ አስተማረ (ነህ 8:8)፡፡ ዳዊት «ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደማናፍቅ፣ አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች» አለ (መዝ 42:1)፡፡ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሕዝብ ይበረታል (ዳን 11:32)፡፡ እግዚአብሔርን ማወቅ የዘላለም ሕይወት ነው (ዮሐ 17:3)፤ ይህም እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል (ኤር 9:23-24)፡፡

እግዚአብሔርን ማወቅ ቢያንስ በአራት መሠረታዊ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ነው:: እነዚህም በእግዚአብሔር ማመን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግመኛ መወለድ፣ መታዘዝ እና ፍቅር ናቸው::[3] በእግዚአብሔር ማመን እርሱ በሥላሴ:- በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾ የሚኖር እውነተኛ አምላክ መሆኑን ማመን ነው (ዮሐ 17:3፣ 1ቆሮ 2:9-13):: በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ደግሞ ከአብ ዘንድ የመጣው እርሱ እውነተኛ እና ጌታ መሆኑን ማመን እና በእርሱ በማመን ዳግመኛ መወለድ ነው (1ዮሐ 5:20፣ ማቴ 11:27፣ ዮሐ 3:1-8፣ 1ቆሮ 8:5-6):: ለእግዚአብሔር መታዘዝ እርሱን ማወቅን ማሳያው መንገድ ነው (1ሳሙ 15:22-23፣ ማቴ 22:37-40፣ 1ዮሐ 2:2-3):: እርስ በርስ በመዋደድ የሚገለጽ የወንድማማች ፍቅር እግዚአብሔርን የማወቅ መግለጫ ነው (1ዮሐ 4:8)::

## 2.1.1 ስለ እግዚአብሔር በሙሉ መረዳት አይቻልም

---

[3] እግዚአብሔርን ማወቅ ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ለግንዛቤ እንዲረዳ በሚከተለው መንገድ በቀመር መልክ መመልከት ይችላል::

KG = BG + KJ + O + L ወይም በተሻለ አቀራረብ

**KG= f(BG, KJ, O, L)**

where :- **KG = Knowing God** እግዚአብሔርን ማወቅ

**f = function, determinant** (የሚገልጽ፣ የሚወስን)

**BG= Belief in God** በእግዚአብሔር ማመን

**KJ= Knowing Jesus / Rebiirth** በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግመኛ መወለድ

**O = Obedience** መታዘዝ

**L = Love** ፍቅር

ጸሐፊው ይህን ዓይነት ቀመር (Formula/ functional) አገላለጽ በመጠቀም እግዚአብሔርን ማወቅ የሚለውን ሃሳብ ለመግለጽ የሞከረው እግዚአብሔርን ለማወቅ ቁልፍ የእምነትና የተግባር ነጥቦችን በማመልከት እግዚአብሔርን ማወቅ የሚመሠረተው የስሌቱ ክፍሎች ሁሉም በአንድ ላይ ተሟልተው ሲገኙ መሆኑን ለማሳየት ለማስገንዘብና እግዚአብሔርን ማወቅ በእምነትና በሥራ የሚገለጽ መሆኑን አስረግጦ ለማሳየት ነው:: ለምሳሌ የእግዚአብሔር ቃል «ትእዛዛቱን ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን:: አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱን የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው» (1ዮሐ 2:2-4)፣ እንዲሁም «ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና» (4.8) ይላልና::



ሰው የእግዚአብሔርን ማንነት በሙሉ ለማወቅ ፈጽሞ አይችልም:: እግዚአብሔር ከሰው አእምሮ እጅግ የላቀ ነው:: በቦታ፣ በጊዜ፣ በመረዳት ችሎታ፣ ወዘተ ... የተመጠነ ሰው ዘላለማዊና ሁሉን ቻይ የሆነውን፣ በሁሉም ቦታ ያለውን ... እግዚአብሔርን በሙሉ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? (1ነገ 8:27፣ ኢሳ 55:8-9፣ ኤር 23:23-24፣ ኢዮ 11:7)::

ሰው እግዚአብሔርን ሊያውቅ የሚችለው እግዚአብሔር ራሱን እስከገለጸበት ድረስና የሰውም አእምሮ ሊያገናዝብ እስከሚችልበት ደረጃ ድረስ ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ከገለጠው በላይ ማሰብ ከንቱ ልፋት ይሆናል:: እግዚአብሔር የገለጸውና እኛ ልንረዳና ልናገናዝብ የቻልነው ያ ነገር እውነተኛ ነገር ነው:: ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን ሊያውቀው የሚችለው እግዚአብሔር የገለጸውን እውነት በእምነት በመቀበል ነው:: የሰውም የመጨረሻ እውቀት ልክ (የአዋቂነት ደረጃ) እግዚአብሔርን ማወቅ ነው:: እግዚአብሔርንም ማወቅ ትልቅ ማስተዋል ነው (ኢዮ 36:26፣ ሆሴ 6:3፣ ማቴ 11:25-27፣ ዮሐ 14:7፣ ዮሐ 17:3 ፣ ሮሜ 1:21፣ 1ቆሮ 2:6-16)::

## 2.1.2 እግዚአብሔርን ማወቅ ይቻላል

እግዚአብሔር በብዙ ዓይነት መንገድ ራሱን የገለጸ አምላክ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ... በልጁ ... በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን» (ዕብ 1:1-2) ይላል:: እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻለው ራሱን በገጸበት መንገድ በኩል ነው::

እግዚአብሔር ራሱን ገልጾአል ሲባል በሰዎች መታየትን አያመለክትም፣ ከሰው ወይንም ከመላእክት እርሱን ያየው የለምና:: አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት ነበራቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ሙሴና (ዘጸ 24:10፣ ዘኍ 12:8)፣ ኢሳይያስ (ኢሳ 6:1) እግዚአብሔርን አይተውታል ይላል:: ይህም የእግዚአብሔርን ክብር ሊሆን ይችላል (ዮሐ 12:41):: እግዚአብሔር ለሙሴ በዘጸ 33:20 «...ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም» ብሎታል:: እንዲሁም በዮሐ 1:18 «እግዚብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም» ተብሏል::

እግዚአብሔርን ማወቅ ስለ እግዚአብሔር ከማወቅ በላይ ነው:: እግዚአብሔርን ማወቅ ከአእምሮ እውቀት በላይ የሆነና ከእርሱ ጋር

ኅብረት ማድረግን[4] የሚጠቃለል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻል ቢሆንም ስለ እግዚአብሔር ግን ሁሉን ነገር ማወቅ አይቻልም::

### 2.1.3 እግዚአብሔርን የማወቅ ዓላማ

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ነገር ሊገልጽ በአማኞች ውስጥ ይኖራል:: በዚህም ክርስቲያኖች እውነት የሆነውን ከውሸት ለይተው ያውቃሉ (ዮሐ 16:13-15፣ 1ቆሮ 1:10፣ 1ዮሐ 2:27):: እግዚአብሔር እርሱን እናውቅና እንታዘዝለት ዘንድ ይወዳል፣ በቃሉም ያዘናል:: እግዚአብሔርን የማወቅ ዓላማ:- ሰዎችን ወደ ዘላለም ሕይወት ለመምራት (ዮሐ 1:16፣ 17:3፣ 1ጢሞ 2:4) እና አማኞች እርሱን በማወቅ በክርስትና ሕይወታቸው የበለጠ ያድጉ ዘንድ (2ጴጥ 3:18፣ ኤፌ 1:18) ነው::

እግዚአብሔርን ማወቅ ሕይወት ነው:: እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሰው ባሕሪውንም ያውቃል፣ ለእርሱ የሚገባውን መሥዋዕት፣ አምልኮና ስግደት ያቀርባል፣ በአምላኩም ደስ ይለዋል:: ስለሆነም እግዚአብሔርን ማወቅ ማንነቱን በመገንዘብና በመታዘዝ ከእርሱ ጋር ሕያው የሆነ ኅብረት ለማድረግ ያስችላል::

## 2.2 እግዚአብሔርን የማወቂያ መንገድ (መገለጥ)

እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ ራሱን ባይገልጥ ሰው እንዴት ስለ እርሱ ሊያውቅ ይችላል? እርሱ በጥናትና ምርምር የሚገኝ ወይም የሚታወቅ አይደለም:: እርሱ ግን ይታወቅ ዘንድ ስለሚወድ ራሱን ገልጾአል::

እግዚአብሔር በተለያዩ መንገድ ራሱን፣ ባሕሪውን፣ ሀሳቡን፣ ለሰው ያስታወቀበት መንገድ መገለጥ (Revelation) ይባላል:: እግዚአብሔር ራሱን የገለጸባቸው መንገዶች በሁለት ዋና ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ:: እነርሱም «አጠቃላይ መገለጥ» እና «ልዩ መገለጥ» ናቸው:: ሁለቱም የመገለጥ መንገዶች ከእግዚአብሔር የሆኑና ስለ እግዚአብሔር የሚገልጹ ናቸው::

---

4 ከዚህ በፊት በበግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3 በተመለከተው ቀመር ውስጥ የተጠቃለሉት መታዘዝና ፍቅር ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረጊያ መንገዶች ናቸው::



### 2.2.1 አጠቃላይ መገለጥ

አጠቃላይ መገለጥ ማለት እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው በሁሉም ጊዜና በሁሉም ቦታ ራሱን ያሳወቀበት መንገድ ነው:: አጠቃላይ መገለጥ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በፍጥረት፣ በታሪክና በሰው የውስጥ ማንነት አማካይነት ማንነቱን መግለጹን ነው:: በሰው ሁሉ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የተቀመጠ መረዳት (Awareness of God / sensus divinitatis) አለ:: ሆኖም እንደ አቴናውያን እንደነበሩበት ሁኔታ ሰዎች ያላቸው የየራሳቸው ሃይማኖትና ፍልስፍና እውነተኛውን አምላክ እንዳያውቁ ይከለክላቸዋል (ሐዋ 17:22-30)::

አጠቃላይ መገለጥ ቃሉ እንደሚያመለክተው አቀራረቡ አጠቃላይ ነው:: ይህ መገለጥ በየትኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ ለሚገኙ ለሁሉም ሰዎች ነው፣ (ማቴ 5:45፣ ሐዋ 14:17)፣ ለዓለም ሁሉ ነው (መዝ.19:1)፣ በሰው ሁሉ ዘንድ ያለ ነው (ሮሜ 2:14-15):: አጠቃላይ መገለጥ የተገለጠባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ) ተፈጥሮ

ተፈጥሮ ሰውን ጨምሮ ስለ እግዚአብሔር ማንነት ይናገራል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 1:20 ላይ እንደገለጸው የእግዚአብሔር «የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና»[5] ይላል:: ስለሆነም የእግዚአብሔር ኃይሉና አምላክነቱ በፍጥረቱ አማካይነት የሚታወቅ ነው (መዝ 8:1፣ 19:1-4)::

በመዝ 19:1-6 እንደተመለከተው ግዑዝ የሆኑ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ስለ እግዚአብሔር ክብር ይናገራሉ:: እንዲሁም በሮሜ 1:18-32 መሠረት ስለ እግዚአብሔር በተፈጥሮ አማካይነት የሚገለጠውን እውነት የሚገታ የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይወርዳል::

---

5 በአዲሱ መደበኛ ትርጉም እንደሚከተለው ይነበባል: «ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕሪይ ይኸውም ዘላለማዊ ኃይሉና መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል ... »::

### ለ) ሰው

እግዚአብሔር በሰው አማካይነት ራሱን ገልጾአል:: ጆሮን የፈጠረ የሚሰማ አምላክ ነው:: ዓይንን የፈጠረ የሚያይ አምላክ ነው (መዝ 94:9):: በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሰው ሁሉ በውስጡ የኅሊና ሕግ አለው (ሮሜ 2:14-15):: ይህ ሕግ የሚናገረው የግብር ኃጢአቶች ለምሳሌ መስረቅ፣ መዋሸት፣ ሰው መግደል እና የመሳሰሉት ሁሉ የትኛውም ሕብረተሰብ በበጎ ኅሊና የማይቀበላቸው እንደሆኑ ነው:: በሰው ውስጥ ያለው ትክክለኛና ስህተት የሆነውን የሚገልጸው ስሜት እንዲህ አድርጐ የፈጠረውን የእግዚአብሔርን ሕልውና ያሳያል:: እግዚአብሔር በአጠቃላይ መገለጥ አማካይነት ስለ ራሱ ማንነት፣ ባሕርይና ሥራ የሚከተሉትን ገልጿል:-

- ክብሩን (መዝ 19:1)
- የሰማይን ጠፈር (ዓለማትን) መፍጠሩን (መዝ 19)
- ታላቅነቱንና አምላክነቱን (ሮሜ 1:20)
- ተፈጥሮን መቆጣጣሩንና ቸርነቱን (ሐዋ 14:17)
- ለሁሉም ሰው መልካምነቱን (ማቴ 5:45)
- በሰው የተሠራ ወይም የተመሰለ አለመሆኑን (ሐዋ 17:29)

ሰማይ፣ ከዋክብት፣ ፍጥረታት፣ ሰዎች፣ እና የእግዚአብሔር የእጅ ሥራዎች ሁሉ የአንድ የፈጣሪን መኖር እና መኖር ያስቻላቸውን የእርሱን ቸርነት የሚያመለክቱ ናቸው:: ይሁን እንጂ እነዚህ ብቻቸውን እግዚአብሔርን ማወቅ እንደሚገባን አያሳውቁንም እርሱን በማመን ወደሚገኝ የኃጢአት ሥርየትና ደህንነትም አያደርሱም::

አጠቃላይ መገለጥ[6] ስለ እግዚአብሔር የሚያስረዳው መጠነኛ በመሆኑ ልዩ መገለጥ አስፈላጊ ነው:: ስለ ራሱ ሊገልጥ የሚችል እግዚአብሔር

---

6 በአጠቃላይ መገለጥና በሕሊና ሕግ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁት ብዙ ነገር አለ:: ሆኖም አንድ ሰው አምላክ (super natural being) እንዳለ በማመኑና ያም «አምላክ» የሕያው እግዚአብሔር የሆኑ አንዳንድ ባሕርያትና ሥራዎች (ለምሳሌ ሁሉን ቻይነት፣ መፍጠር) አለው በመባሉ ያ አምላክ የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ነው ለማለት አይቻልም:: በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው እግዚአብሔር በሦስት አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተገልጾ የሚኖር አንድ አምላክ ነው:: ይህን የሚክድ እምነት የሚያመልከው በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን ሕያው አምላክ ሳይሆን «ሌላ አምላክ» ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ 11:4 ላይ «ሌላ ኢየሱስ ... ልዩ መንፈስ ... ልዩ ወንጌል» እንዳለው ዓይነት እንዲሁ ይህ አምላክም የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔር የሚመስል ግን «ሌላ አምላክ» ነው::



ነው:: ያለዚያ እንደ አቴና ሰዎች «ለማይታወቅ አምላክ» (ሐዋ 17:22) መስገድ ይሆናል::

ተፈጥሮ በድንቅ ሁኔታ መሠራቱ ፈጣሪ መኖሩንና ይህም ፈጣሪ የፈጠረውን ሁሉ ውብ አድርጎ መሥራቱን ያመለክታል:: ይሁን እንጂ ተፈጥሮ ብቻውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ኅብረት ማድረግ እንደሚችልና እግዚአብሔርም ከሰው ምን እንደሚፈልግ አይገልጽም:: እንግዲህ ተፈጥሮ ስለ እግዚአብሔር የሚያሳውቅ ቢሆንም ከሰው ጋር ሊነጋገርና የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ሊገለጽ ባለመቻሉ ሌላ (ልዩ) መገለጥ አስፈልጓል::

## 2.2.2 ልዩ መገለጥ

ልዩ መገለጥ ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ያመለክታል:: ልዩ መገለጥ እግዚአብሔር ከሰው ዘር ጋር የተነጋገረውንና ፈቃዱን የገለጸበትን መንገድ የሚያመለክት ነው:: ልዩ መገለጥ እግዚአብሔርን በማመንና ቃሉን በማወቅ የሚገኝ ነው::

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ጀምሮ ከሰው ጋር ይነጋገር ነበር፣ ሃሳቡንና ፈቃዱንም ይገልጽ ነበር:: በዘፍ 2:15-17 እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ሲነጋገር ለሰው ዘር ተስፋ ሲሰጥ እናነባለን:: ይህ የእግዚብሔር ዕቅድ ዘመኑን ቆጥሮ በጊዜው በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሟል (ገላ 4:4)::

የእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ ሁለት ዋና መንገዶች አሉት:: እነርሱም በሥጋ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስና የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ናቸው::

### ሀ) የእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ:- በኢየሱስ ክርስቶስ

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በብዙ መንገድ ሲናገር ቆይቶ በመጨረሻ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ተናገረን (ዕብ 1:2):: ራሱ እግዚአብሔር መለኮት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ገለጸው:: እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻለው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ በማቴ 11:27 ላይ «... ከወልድም በቀር፣ ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም» ይላልና:: ኢየሱስ ክርስቶስ አማኑኤል «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ነው (ኢሳ 7:14፣ ማቴ 1:23፣ ዮሐ 1:14፣18፣ ዮሐ 7:46፣ 1ዮሐ 1:1-3)::

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ ነው:: መጽሐፍ እንደሚል «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና፤» (ቆላ 2:9)[7] ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በአካል በመመላለስ የእግዚአብሔርን ባሕሪያት በሙላት ገልጿል::

ለ) የእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ:- በመጽሐፍ ቅዱስ

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት አንዱ መንገድ ስሙን በማሳወቅ ነው:: ሙሴ የሚነደውን ቁጥቋጦ ለማየት ከሄደ በኃላ ማን ላከኝ ልበል ሲል «ያለና የሚኖር» (I am) ላከኝ ትላለህ ብሎታል (ዘጸ 3:14):: እግዚአብሔር ከኖህ ጋር (ዘፍ 8:12-17) ከአብርሃም ጋር (ዘፍ 15፣18፣ 17:1-14) ቃል ኪዳን ገብቷል:: ጳውሎስ እግዚአብሔርን ሊያውቅ ይመኝ ነበር (ፊሊ 3:10):: ይህ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጧል::

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: የእግዚአብሔርን ሃሳብና ፈቃድ ያሳያል:: እግዚአብሔር ሀሳቡን የገለጠባቸውና ለሰው ያስታወቀባቸው መንገዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጸዋል::[8] ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በማመን እግዚአብሔርን ሊያውቅ ይችላል:: መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ሉቃ 24:44):: መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አይገልጽም (ዮሐ 20:30-35):: ይሁን እንጂ ሰው ስለ እግዚአብሔር ሊያውቅ የሚገባው ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጿል:: የተገለጸው ሁሉ ደግሞ እውነት ነው (ዮሐ 17:17)::

---

7 በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና» ይላል ::

8ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንገነዘበው እግዚአብሔር ፈቃዱን ለሰዎች ካስታወቀባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ::

ሀ. ዕጣ:- ምሳ 16:33፣ ሐዋ 1:21-26
ለ. ኡሪምና ቱሚም:- ዘጸ 28:30፣ ዘኁ 27:21፣ ዘዳ 33:18፣ 1ሳሙ 28:6፣ ዕዝ 2:63
ሐ. ሕልም:- ዘፍ 20:3 እና 6፣ 31:11-23 እና 24፣ ኢዮ 2:28
መ. ራእይ:- ኢሳ 1:1፣ 6:1፣ ሕዝ 1:3
ሠ. የእግዚአብሔር መልአክ:- ዘፍ 16:7-14፣ ዘጸ 3:2፣ 2ሳሙ 24:16፣ ዘካ 1:12
ረ. መላእክት:- ዳን.9:20-21፣ ሉቃ.2:10-11፣ ራእ.1:1
ሸ. በጉልህ ድምጽ ....



መጽሐፍ ቅዱስ 39 የብሉይና 27 የሐዲስ ኪዳን በድምሩ 66 መጽሐፍትን በውስጡ የያዘ፣ ከ40 በሚበልጡ ጸሐፊዎች የተጻፈ፣ በ1500 ዓመታት ያህል ጊዜ ውስጥ የተጻፈ ሆኖ ሳለ ሀሳቡ አንድ ነው:: ይኸውም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሊሠራ ስላቀደው፣ ስለሠራውና ስለሚሠራው ሀሳብ መግለጽ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በቃሉ መሠረት በማመን የተለወጡ ሰዎች ሕይወት ስለ እግዚአብሔር ሕልውና የሚያስረዱ ሲሆን እግዚአብሔር ራሱን ለገለጸባቸው መንገዶችም ተጨማሪ ማስረጃ ይሆናል:: ይህን እውነት ቀምሰው ያዩ ሰዎች ይበልጥ ያውቁታል (መዝ 34:8):: የተለወጡ ሰዎች ሕይወት የሚያመለክተው እግዚአብሔር አምላክ በቃሉ እንደተናገረው እንዲሁ በሰዎች ሕይወት ቃሉን የሚፈጽም መሆኑን ነው::

## 2.3 <u>የእግዚአብሔር መሠረታዊ ማንነት</u>

### 2.3.1 <u>እግዚአብሔር ሕያው አምላክ ነው</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ሕያውነት ለማረጋገጥ አይሞክርም:: ይልቁን በዕብ 11:6 እንደተጻፈው «ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና» ይላል:: ፍጥረት ሁሉ ሕይወት የሚያገኘው ከእግዚአብሔር ሲሆን እግዚአብሔር ግን ራሱ በራሱ የሚኖር ሕያው አምላክ ነው (ዮሐ 5:26):: ለመኖር ምንም አያስፈልገውም (ሐዋ 17:25):: ይህ ሕያው አምላክ በታሪክ ውስጥ ማንነቱንና ፈቃዱን ገልጿል፣ ታሪክን ይቆጣጠራል:: እርሱ በሕያውነት ለዘላለም ይኖራል::

መጽሐፍ ቅዱስ «እስራኤል በተራራው ላይ የሕያው አምላክን ድምጽ» ሰማ (ዘዳ 5:26)፣ «የሕያው አምላክ ... መላእክቱን» ይልካል (ራእ 7:2) ይላል:: አማልክት ሁሉ ጸሎትን የማይሰሙ፣ መልስ የማይሰጡ፣ ምናምንቴዎች ናቸው (ኢሳ 40:10፣ ኤር 2:5):: ጣዖታት የብልሃተኞች የእጅ ሥራዎች (ኤር 10:8-9)፣ ዝናብ ማዝነብ የማይችሉ (ኤር 14:22) ናቸው:: ሕያው እግዚአብሔር ግን ትንፋሽ ከሌላቸው የምስል አማልክት ፈጽሞ የተለየ ነው (ኤር 10:14-15):: ሕያው እግዚአብሔር ድምጹን ያሰማል (ኤር 10:13):: የተሰሎንቄ ሰዎችም ዳግመኛ ሲወለዱ ከጣዖቶች ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ብለዋል (1ተሰ 1:9):: አማኞች በሕያው እግዚአብሔር ተስፋ ይኖራሉ (1ጢሞ

4:8-10):: ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ያለና የሚኖር ሕያው አምላክ ነው::

### 2.3.2 እግዚአብሔር መንፈስ ነው

እግዚአብሔር መንፈስ ነው:: ይህም የማንነቱ መግለጫ ነው (ዮሐ.4:24):: መንፈስ የሆነ ሥጋና አጥንት የለውም (ሉቃ.24:39)::[9] እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ[10] የሚታይ ግዙፍ አካል ወይም የሰውነት ክፍል የለውም:: ስለዚህ ማንም ሰው እርሱን አላየውም[11] (ዮሐ 1:18፣ 1ጢሞ 1:17፣ 1ጢሞ 6:15-16)::

9 እግዚአብሔር መንፈስ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋና በደም ተገልጿል (ዕብ 2:14-16):: በእግዚአብሔር (Godhead) ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮትነቱ መንፈስ ነው::

10 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር እንደ ሰው ተገልጾ እንመለከታለን:: እግዚአብሔር ይናገራል (ዘፍ 1:3)፣ ይሰማል (ዘፍ 21:17፣ ዘጸ 16:2)፣ ያያል (ዘፍ 1:4)፣ ያሸታል (1ሳሙ 26:19)፣ ፊት አለው (ዘኁ 6:25፣ መዝ 27:8)፣ ጀርባ አለው (ዘጸ 33:23)፣ እጆች አሉት (መዝ 10:2፣ ኢሳ 14:27)፣ ጣት አለው (ዘዳ 9:10):: በሌላ በኩል ደግሞ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም:: ደግሞም እግዚአብሔር ሰው አይደለም (ሆሴ 11:9)፣ እርሱን በምንም መመሰል አይቻልም (ኢሳ 40:18):: እንግዲያውስ ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከሰው ጋር ለመገናኘትና ራሱን ለማሳወቅ የወደደበት ከሰው ጋር የሚግባባት ሁኔታ ወይም ሰብዓዊ አነጋገር (Anthropomorphism) ነው ማለት ይቻላል::

11እግዚአብሔር እንደተገለጸና ሰዎችም እንዳዩት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ያዕቆብ (ዘፍ 32:30)፣ ሙሴ (ዘጸ 3:6፣ ዘጸ 33:11፣ ዘዳ 34:10)፣ ኢሳይያስ (ኢሳ 6:1) እግዚአብሔርን አይተዋል:: እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ማንም ሰው መንፈስን ሊያይ አይችልም:: «እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ» (ዘኁ 6:25) የሚለው ቡራኬ የበረከት መግለጫ ሲሆን እግዚአብሔር ፊቱን መሰወሩ ደግሞ (መዝ 13:1) የስቃይና የሀዘን ምክንያት ይሆናል:: እግዚአብሔርን እንዳዩት የተነገረላቸው ሰዎች በእርሱነቱ አላዩትም እርሱን አይቶ በሕይወት መኖር አይቻልምና ዘጸ 33:20:: እንዲሁም በዘዳ 4:15-18 ላይ «እግዚአብሔር በኮሬብ በእሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ እንዳትረሱ የተቀረጸውን ምስል የማናቸውንም ነገር... ምሳሌ እንዳታደርጉ» ይላል:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የማይታየው አምላክ ምሳሌ ነው (ቆላ 1:15):: ስለዚህ ያዩት የእግዚአብሔርን ክብር መሆን አለበት:: ጌታ ኢየሱስ ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ስለማየቱ ሲናገር «ክብሩን ስላዬ ኢሳይያስ ይህን አለ፣ ስለ እርሱም ተናገረ» ብሏል:: ክብሩ የእርሱ መገኘት ፣ የሥልጣኑ፣ የኃይሉ መግለጫ ነውና:: (ዘጸ 24:15-17፣ 33:18-22፣ 1ሳሙ 4:21)::



እግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ እንግዲያው ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል[12] ነውና (ዘፍ 1:27) ይህ ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ ብዙ ጊዜ ይነሳል:: ይህ ማለት ግን ሰው መንፈስ ነው፤ ወይንም እግዚአብሔር ሥጋና አጥንት አለው አያሰኝም:: በቆላ 3:10 እና በኤፌ 4:24 መሠረት የሰው እግዚአብሔርን መምሰል በጽድቅ፣ በእውቀትና በቅድስና ነው:: እግዚአብሔር የጠራን የልጁን መልክ እንድንመስል ነው (ሮሜ 8:29):: ይህም የባሕርይ መመሳሰል እንጂ የአካል (የሰውነት) መመሳሰል አይደለም:: በተጨማሪም ሰው እግዚአብሔርን የሚመስለው በፍጥረታት ሁሉ ላይ ሥልጣን በመቀበሉ ነው (ዘፍ 1:26-27)::

### 2.3.3 እግዚአብሔር እኔነት አለው (Personal Being)

እግዚአብሔር እኔነት አለው:: ስም አለው፣ በዚህም ስም ይጠራል፣ በዚህም ስም ራሱን ለሌሎች ይገልጻል (ዘካ 3:14):: እግዚአብሔር «አካል» (Personality) አለው:: ይህም ማለት እግዚአብሔር የራሱ እኔነት ያለው ነው ማለት እንጂ የሰው ገላ ዓይነት ግዙፍ አካል/ ሰውነት ያለው ነው ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር እኔነት ስላለው ሰዎች ከእርሱ መገለጥን ይቀበላሉ፤ ከእርሱ ጋር ሕብረት ያደርጋሉ፣ ወደ እርሱ ይጸልያሉ:: እርሱ «አንድ ኃይል» አይደለም:: የምናየውም ነገር ሁሉ እግዚአብሔር አይደለም፤ እግዚአብሔር አካል ስላለው ይኖራል፣ ይሰማል፣ ይልካል፣ ይባርካል፣ ወዘተ...:: እግዚአብሔር

12ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር ምሳሌ ወይም መልክ ነው የሚለውን ለመረዳት ወይም ለመተርጎም ከሚቀርቡት አመለካከቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:-

1. ሰው በአካል እግዚአብሔርን ይመስላል፣
2. በአንድ እግዚአብሔር ሦስት አካላት (ሥላሴ) እንዳሉ ሁሉ ሰውም እውቀት፣ ስሜትና ፈቃድ ስላለው በዚህ እግዚአብሔርን ይመስለዋል፣
3. ሰው እግዚአብሔርን የሚመስለው በገዥነቱ (በአስተዳዳሪነቱ) ነው፣
4. እግዚአብሔር በባሕሪው ጻድቅና ቅዱስ በመሆኑ ሰውም የተፈጠረው በዚህ ምሳሌ ነው::
5. «በመልካችን እንደምሳሌያችን» የሚለው ማኅበራዊነትን የሚያመለክት በመሆኑ ሰው የተፈጠረው ለብቻው ለመኖር ሳይሆን በማኅበራዊነት በፍቅር እንዲኖር ነው፣ የሚሉት ዋናዎቹ ናቸው::ሆኖም ጠቅለል ባለ አገላለጽ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ የሚያመለክተው የአካል መመሳሰልን ሳይሆን ሰው በምድር ላይ ገዥ እንዲሆን መደረጉንና የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንዲካፈል ሆኖ መፈጠሩን ነው:: ሰውን ክቡር ፍጥረት የሚያደርገውም በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ነው (ያዕ 3:9)::

ሕያው ስለሆነና እኔነት ስላለው ሰው በእርሱ ይታመናል፣ እርሱን ያውቃል፣ ይወዳል፣ እርሱን ያመልካል፣ ያገለግለዋል::

እግዚአብሔር «የአካል» ወይም የእኔነት መግለጫዎች ማለትም እውቀት፣ ስሜት፣ ፈቃድ አሉት:: እነዚህ የአካል መግለጫዎች በእግዚአብሔር ዘንድ በፍጹምነት ይገኛሉ:: እግዚአብሔር ያውቃል (መዝ 139:1-6)፣ ይሰማዋል (ናሆ 1:2-3)፣ ይፈቅዳል (1ተሰ 4:3,5 እና 18)::

እግዚአብሔር ከአዳም ጋር በኤደን ገነት (ዘፍ 3:9-23) እና ከሙሴ ጋር በሚነደው ቁጥቋጦ (ዘጻ 3:1-4፣17) የተነጋገረው እኔነት ወይም አካል እንዳለው ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው:: እግዚአብሔር እኔነት ስላለው ሰውን ወዳጅ ያደርጋል፣ ከሰው መካከል ወዳጅ ነበረውና (ኢሳ 41:8፣ ያዕ 2:23)::

### 2.3.4 <u>እግዚአብሔር ፍቅር ነው</u>

እግዚአብሔር ሰውን የሚወድድ ብቻ ሳይሆን ራሱ ፍቅር ነው:: ፍቅር ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ብቻ አይደለም፣ የባሕርያቱ ሁሉ ማጠቃለያ የእርሱነቱ መግለጫ ነው (ዮሐ 4:8 እና 16):: ፍቅር በሥላሴ መካከል ላለው ተዛምዶና አንድነት መግለጫ ነው:: «አብ ወልድን ይወዳልና» (ዮሐ 5:20፣ 17:24):: ወልድም አብን ይወድዳል ዮሐ 14:31::

### 2.3.5 <u>እግዚአብሔር ብርሃን ነው</u>

«እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም» (1ዮሐ 1:5):: እርሱ «የብርሃናት አባት» ነው (ያዕ 1:17):: ዘማሪው እግዚአብሔርን «ብርሃንን እንደ ልብስ ለበስህ» (መዝ 104:2) ይለዋል::

ጨለማ የኃጢአትና የሞት ምሳሌ ሲሆን ብርሃን የጨለማ ተቃራኒ ነው:: ብርሃን የቅድስና፣ የመልካምነት፣ የሕይወት መግለጫ ነው:: በእግዚአብሔር ዘንድ ጨለማ (ኃጢአት) የለም:: «የእስራኤልም ብርሃን እንደ እሳት ቅዱሱም እንደ ነበልባል ይሆናል» (ኢሳ 10:17):: ብርሃን የሆነ እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠራው «ወደሚደነቅ ብርሃኑ» (1ጴጥ 2:9) ነው:: ብርሃን የሆነ እግዚአብሔር የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን በማይኖርበት በዘላለም ውስጥ ጌታ አምላክ ለሕዝቡ ያበራላቸዋል (ራእ 22:5)::



እንግዲህ እግዚአብሔር ይታወቅ ዘንድ የሚወድ አምላክ ስለሆነ ራሱን ገልጦአል:: ራሱንም በመግለጡ ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ ይችላል:: እግዚአብሔርን ማወቅ ከአእምሮ እውቀት እጅግ ያለፈ ነው:: እግዚአብሔርን ማወቅ ማንነቱን ተገንዝቦ፣ በእርሱ በማመንና ለእርሱ በመገዛት መኖር ነውና::

የእግዚአብሔር ማንነት ከሚታወቅባቸው መንገዶች አንዱ በስሞቹ ነው:: የእግዚአብሔር ስሞች ማንነቱን ይገልጻሉ:: ይህን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን::

# ምዕራፍ 3. የእግዚአብሔር ስሞች

ስም መለያ፣ መጠሪያና የማንነት መግለጫ ነው:: በተለይ በዕብራውያን ዘንድ ለአንድ ሰው ስም ሲሰጠው ባለስሙ ወደፊት እንዲሆን የሚፈለገውን ወይም የወላጆቹን ታሪክና የወደፊት ተስፋ እንዲገልጽ ተደርጐ ይሰየማል:: እግዚአብሔርም የሰዎችን ሕይወት ወይም ባሕርይ ለመለወጥ ወይም ልዩ ተስፋ እንደገባላቸው ምልክት እንዲሆን ስም የተቀየረላቸው አሉ:: የአብርሃም (ዘፍ 17:5)፣ የሣራ (ዘፍ 17:15-16)፣ የያዕቆብ (ዘፍ 32:27-29)፣ የጴጥሮስ (ማር 3:16) ስም የተቀየረላቸው ነው::

የእግዚአብሔር ስም የእርሱን ማንነት ወይም ባሕርይውን ያመለክታል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው የእግዚአብሔርን ስም መጥራት እርሱን ማምለክ ነው (ዘፍ 21:33):: ጌታ ባስተማረው ጸሎት ውስጥ «ስምህ ይቀደስ» (ማቴ 6:9) ብለን ስንጸልይ የእግዚአብሔርን ስም ሰዎች ሁሉ ያከብሩት ዘንድ[13] እና በስሙ ውስጥ የተገለጸውን ባሕርዩን ይረዱ ዘንድ መለመናችን ነው:: በሰው ዘንድ እንኳ ቢሆን የአባቱ ወይንም የራሱ ስም ባልሆነ ቦታና ሁኔታ ሲጠራበት ደስ የሚለው ማን ነው?

እግዚአብሔር ስለ መስዋዕት የሰጠውን ሥርዓት አለመጠበቅ ስሙን ማርከስ ነው (ዘሌ 22:2፣32):: ካህናቱ በስሙ ያገለግላሉ (ዘዳ 21:5):: እግዚአብሔር ስለ ስሙ የሰጠውን ተስፋ ይጠብቃል (1ሳሙ 12:22):: ዘማሪው «አቤቱ ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ» ይላል (መዝ 8:1):: ሙሴም በመዝሙር እንዲህ ይላል:-

> የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁና፣ ለአምላካችን ታላቅነትን ስጡ::
> እርሱ አምላክ ነው ሥራውም ፍጹም ነው፤
> መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፣

---

13ስሙን በከንቱ መጥራት እርሱን አለማክበር ነው (ዘጸ 20:7):: የእግዚአብሔርን ስም የማናከብረው የእርሱን ማንነት የማያከብሩና የማይገልጹ ቃላትን ከስሙ ጋር አያይዘን ስንናገር እንዲሁም የእርሱ ሆነን ሳለ በተግባራችን ግን ስንክደው ነው:: የእግዚአብሔር ቃል «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» ይላልና (ማቴ 5:16)::

የታመነ አምላክ፣ ክፋትም የሌለበት፣
እርሱ እውነተኛና ቅን ነው (ዘዳ 32:3-4) ይላል።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን የሚታወቅባቸውና የሚጠራባቸው ማንነቱን የሚገልጹ ስሞች አሉት። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚለው ስም እንደ ዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ የተለያየ ባይሆንም በዕብራይስጡ መሠረት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የሚጠራባቸው ሦስት ዋና ስሞች አሉት።[14] እነርሱም ኤሎሂም፣ ያህዌና አዶናይ ናቸው።[15]

## 3.1 <u>የብሉይ ኪዳን ስሞች</u>

### 3.1.1 <u>ኤል/ኤሎሂም (ELOHIM)</u>

ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን 2,570 ጊዜ ያህል የተገለጸ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2,310 ጊዜ ያህል ለእውነተኛው አምላክ ማለትም ለሕያው እግዚአብሔር ውሏል። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጀመሪያው ቁጥር ላይ ተገልጿአል፤ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» (ዘፍ 1:1) ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ በዘፍ 35:2,4፣ ዘጸ 12:12፣ 18:11 እና በመሳሰሉት ቦታዎች ኤል የሚለው ቃል ሌሎች አማልክትን ያመለክታል።

ኤል[16]/ ኤሎሂም ማለት ታላቅ፣ ኃያል፣ አምላክ ማለት ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ቃሉ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ሲሆን

---

14 የእግዚአብሔር ስም የእርሱን ማንነት፣ ባሕርይና ሥራ የሚያመለክት ሲሆን ለሰዎች መጠሪያ ወይም መታወቂያነት የሚውሉ መግለጫዎች ለእግዚአብሔርም ውለዋል። እግዚአብሔር ተዋጊ፣ (ዘጸ.15:3)፣ ፈዋሽ (ዘጸ.15:26)፣ እረኛ (መዝ.23:1)፣ ባል (ኢሳ 54:5)፣ ታዳጊ (ኢሳ 33:22) ተብሏል።

15አዲሱ መደበኛ ትርጉም ሦስቱን መሠረታዊያን የእግዚአብሔር ስሞች ለመለየት ያደረገውን ጥረት በመጽሐፉ መቅድም ገጽ VI ላይ ይመልከቱ።

16«ኤል» ከሰውና ከቦታ ጋር ተያይዞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጿል። ለምሳሌ ኤልሳዕ (እግዚአብሔር ደህንነት ነው)፣ ኤልሳቤጥ (እግዚአብሔር መሐላዬ ነው)፣ ኤልያስ (እግዚአብሔር አምላክ ነው)፣ ኤልያቄም (እግዚአብሔር ያስነሳል)፣ ዳንኤል (እግዚአብሔር ፈራጅ ነው)፣ ሚካኤል (እንደ እግዚአብሔር ማን ነው?)፣ ቤቴል (የእግዚአብሔር ቤት)፣ ወዘተ።



በእግዚአብሔር ስምነት ሁልጊዜም የሚያያይዘው ከነጠላ ቁጥር ግሥ (አንቀጽ) ጋር ነው። ይህም <u>በብዙነት አንድነትን ያመለክታል</u>። ይህ የእግዚአብሔር ስም የእርሱን ማንነት ወይንም ባሕርይ ማለትም ሁሉን ገዥነቱን፣ የመፍጠር ሥራውን፣ ፈራጅነቱን እንደሚከተለው ይገልጻል።

<u>ሁሉን ገዥነቱን ይገልጻል</u>

«የምድር ሁሉ አምላክ» (ኢሳ 54:5)፣ «የሥጋ ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር» (ኤር 32፣27)፣ «የሰማይ አምላክ» (ነህ 2:4)፣ «የአማልክት አምላክ» (ዘዳ 10:17)፤ የሚሉትና ሌሎች ተመሳሳይ ጥቅሶች ኤሎሂም የሁሉም የበላይና ገዥ መሆኑን ያመለክታሉ።

<u>የመፍጠር ሥራውን ያሳያል</u>

ኤሎሂም ሁሉን ነገር የፈጠረ አምላክ ነው። «በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» (ዘፍ 1:1)። «ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር» (ኢሳ 45:18)፤ «ባሕሩንና የብሱን የፈጠረውን የሰማይን አምላክ እግዚአብሔርን» (ዮና 1:9)። በእነዚህ ጥቅሶች ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ስም ኤሎሂም የሚለው ነው።

<u>ፈራጅነቱን ያመለክታል</u>

ኤሎሂም የእግዚአብሔርን ፈራጅነትም ያመለክታል። «እግዚአብሔር ፈራጅ ነው» (መዝ 50:6)፣ «በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ» (መዝ 58:11) በሚለው የተገለጸው ስም ኤሎሂም ነው።

«ኤሎሂም» ወይም «ኤል» ከተሰኘው ስም ጋር በመያያዝ እግዚአብሔር የሚጠራባቸው ሌሎች ስሞችም አሉት።

ሀ) <u>ኤል ሻዳይ (El-Shadai)</u>

ኤል ሻዳይ ማለት ሁሉን ቻይ ማለት ሲሆን እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱ መጽናናት በመስጠት የበረከት ሁሉ ምንጭ መሆኑን ያመለክታል። እግዚአብሔር በፍጹም ሥልጣኑ ሁሉን በመቆጣጠር ለእኛ በረከትን ይሰጣል። ዘፍ 17:1፣ ዘፍ 28:3፣ ዘፍ 35:11።

### ሰ) <u>ኤል ኤልዩን (El-Elyon)</u>

ልዑል እግዚአብሔር፣ ከፍ ያለ አምላክ ማለት ነው:: የእግዚአብሔርን ኃይል፣ ገዥነት፣ ታላቅነት ያመለክታል:: ዘፍ 14:9፣18-19፣ ዳን 7:18፣ መዝ 50:14::

### ሐ) <u>ኤል ዖለም (El-Olam)</u>

የዘላለም አምላክ ማለት ሲሆን አለመለወጡንና ኃይሉ የማይደክም መሆኑን ያመለክታል:: ዘፍ 21:23፣33፣ መዝ 100:5፣ መዝ.103:17፣ ኢሳ.40:28::

### መ) <u>ኤል ሮኢ (El-Roi)</u>

ኤል ሮኢ ማለት የሚያይ እግዚአብሔር ማለት ነው:: ዘፍ 16:13::

### 3.1.2 <u>ያህዌ (YHWH/YAHWEH)</u>

ይህ ስም በብሉይ ኪዳን 5,321 ጊዜ ተጽፏል:: ያህዌ ማለት ነጻ፣ ራሱ በራሱ የሚኖር፣ እንዲኖር ሌላ ኃይል ወይም ምክንያት የማያስፈልገው ዘላለማዊ አምላክ ማለት ነው:: የዚህ ስም ትርጉም ግልጽ የሆነው ለሙሴ ነው (ዘጸ.6:3):: እግዚአብሔር ራሱን የገለጸው «ያለና የሚኖር» ብሎ ነው (ዘጸ 3:14)::

ያህዌ የሚለው የእግዚአብሔር ስም የሚያመለክተው:-

- እግዚአብሔር ራሱ በራሱ አሁንና ወደፊት የሚኖር መሆኑን
- እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መገኘቱን (ዘጸ 3:12)
- ሕዝቡን ከባርነት በማውጣት ቃል ኪዳኑን መጠበቁን (ዘፍ 12:1-3፣ 15፣ 17፣ 26:2-5፣ 28:13-15፣ ዘጸ 6:6) ነው::

ኤሎሂምና አዶናይ የተሰኙት የእግዚአብሔር ስሞች በዕብራይስጥ ቋንቋ ከእውነተኛው አምላክ ሌላ ለሌሎችም አማልክት ወይም ሰዎች መጠሪያነት ውለዋል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ <u>ለእግዚአብሔር ብቻ መጠሪያ የዋለው ስም ያህዌ የተሰኘው ነው</u>::

እግዚአብሔር ይህን ስሙንና ማንነቱን ለሙሴ እንዲህ ብሎ አውጆአል::



እግዚአብሔር [Yahweh] በደመናው ውስጥ ወረደ፣ በዚያም ከእርሱ ጋር ቆመ፣ የእግዚአብሔርንም ስም [Yahweh] አወጀ:: እግዚአብሔርም [Yahweh] በፊቱ አልፎ:- እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር [Yahweh! Yahweh] መሐሪ፣ ሞገስ ያለው፣ ታጋሽም፣ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት፣ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ፣ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል፣ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ፣ የአባቶችንም ኃጢአት በልጆች እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድም በልጅ ልጆች የሚያመጣ አምላክ ነው ሲል አወጀ (ዘጸ 34:5-7)::

በጥቅሱ ውስጥ የገባው የእንግሊዝኛ ቃል በዕብራይስጡ ሲጻፍ ያህዌን እንደሚያመለክት ለመግለጽ የተጨመረ ነው::

ይህ የእግዚአብሔር ስም የእርሱን ማንነት ይገልጻል፣ ማንነቱ በባሕርይው ይገለጻልና:: በባሕርያቱ መካከል ቅራኔ የለም:: መሐሪና ታጋሽ የሆነው እግዚአብሔር በደለኛውን ግን በበደሉና በኃጢአቱ ንስሐ ካልገባ በስተቀር አያነጻም::

አይሁድ ይህ ያህዌ የሚለው ስም ሊጠራ የማይቻል፣ የከበረ፣[17] የተለየ ስም አድርገው በመቁጠራቸው ስሙ ባለበት ቦታ ሁሉ «አዶናይ» የሚለውን ስም በመተካት ያነብቡ ነበር:: ከዚህ ስም ጅሆባ /ዮሖዋ የሚለው ስም ተገኘ::

---

17 አይሁድ ለእግዚአብሔር ስም አክብሮት አላቸው:: በእኛ ዘንድ ግን የእግዚአብሔርን ስም በመጻፍ ረገድ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየታየ ያለ ጉልህ ስህተት አለ:: የእግዚአብሔር ስም በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ በግልጽ መታወቅ ያለበትና ሲጻፍም የሚያሻማ ትርጉም ያለው መሆን ይገባዋል:: በተለይ በመጽሐፍት፣ በልዩ ልዩ ለሕዝብ በሚቀርቡ ጽሑፎችና ማስታወቂያዎች ላይ ሙሉ ስሙን «እግዚአብሔር» ብሎ መጻፍ አግባብ ነው:: ያለዚያ በአሁኑ ዘመን እየታየ ያለው አሳጥሮ ለመጻፍ መሞከር ማለትም እግዚ፣ እግ/ር፣ እግዚአ፣ እ/ር፣ እ^ር፣ እዝ/ር፣ እግ/ሔር ብሎ መጻፍ የተለያየ አነባበብ ያለውና አሳሳችም ስለሚሆን ወንጌልን ለሌሎች ለማስተላለፍ እንቅፋት ይሆናል::

እንዲህ ዓይነቱ አሳጥሮ መጻፍ በሁሉም አንባቢ ዘንድ ግልጽ ካለመሆኑም በላይ የእግዚአብሔርን ስም በአክብሮት ባለመጥራታችን ወይም ባለመጻፋችን ቅሬታ የሚያድርባቸውም ክፍሎች ይኖራሉ:: ብዙ ጊዜ በአጭር የተጻፉት ሲነበቡም በአጭሩ ማለትም የተጻፉት ፊደሎች ብቻ እየሆነ መምጣቱ ደግሞ የማሳጠሩን ስህተትነት አጉልቶ ያሳያል:: አሳጥሮ የሚጻፈው ለማያምኑ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ማስተዋወቂያ በሚሆኑ በፖስተሮች፣ በትራክቶች በመጽሔቶች ወዘተ ሳይቀር መሆኑ ይህ የማሳጠሩን ስህተትነት እጥፍ ድርብ ያደርገዋል:: ስለዚህ ይህ አጻጻፍ አሳጥሮ መጻፉ ትርጉሙን በአንባቢው እጅ የተተወ ያደርገዋልና ሙሉ ስሙን «እግዚአብሔር» ብሎ መጻፍ በሁሉም ዘንድ እንዲለመድ/እንዲዘወተር ጸሐፊው አጥብቆ ለማሳሰብ ይወድዳል::

ያህዌ በሚለው የእግዚአብሔር ስም መሠረትነት ሌሎች የእግዚአብሔር መጠሪያዎች አሉ። እነዚህ ስሞች ከአንዳንድ ሁኔታዎች ወይም ከተፈጸሙ ድርጊቶች ጋር በተያያዘ መንገድ እግዚአብሔር የተጠራባቸው ናቸው። እነርሱም:-

| | | |
|---|---|---|
| ሀ) | ያህዌ ይርኤ | እግዚአብሔር ያያል (ዘፍ 22:14)። |
| ለ) | ያህዌ ንሲ | እግዚአብሔር ዓላማዬ (ዘጸ 17:15)። |
| ሐ) | ያህዌ ሻሎም | እግዚአብሔር ሰላም (መሳ 6:24)። |
| መ) | ያህዌ ሳቦት | የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ በተለይ በጦርነት ጊዜ የእስራኤል የጦር መሪና ጠባቂ መሆኑን ያመለክታል (1ሳሙ 17:45)። |
| ሠ) | ያህዌ ማካደሽ | የሚቀድስ እግዚአብሔር (ዘጸ 31:13) |
| ረ) | ያህዌ ሮይ | እግዚአብሔር እረኛዬ (መዝ 23:1) |
| ሰ) | ያህዌ ስድኩኑ | እግዚአብሔር ጽድቃችን (ኤር 23:6) |
| ሸ) | ያህዌ ሻማሕ | እግዚአብሔር በዚያ አለ (ሕዝ 48:35) |
| ቀ) | ያህዌ ኤሎሂም እስራኤል | የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር (መሳ 5:3፣ ኢሳ 17:6) |

### 3.1.3 አዶናይ (ADONAI)

አዶናይ ማለት ጌታ፣ ባለቤት፣ በሁሉ ላይ የሚገዛ ማለት ሲሆን እግዚአብሔር የሰው ሁሉ ጌታ፣ ባለቤት መሆኑን ያመለክታል። አዶናይ የሚለው መጠሪያ ለእግዚአብሔር ሲውል ብዙ ጊዜ ኤሎሂም ከተሰኘው ስም ጋር ተያይዞ ይገኛል። ይህም በሕዝቡ ላይ ጌታ ወይም ገዥ የሆነው እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል (ዘፍ 19:2፣ 40:1፣ 1ሳሙ 1:15፣ ኢያ 5:14፣ ኢሳ 6:8-11)።

## 3.2 የአዲስ ኪዳን ስሞች

አዲስ ኪዳን በመጀመሪያ በግሪክ እንደመጻፉ መጠን የአዲስ ኪዳን ስሞች መሠረት የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዚህም መሠረት በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ስሞች የሚከተሉት ናቸው።

### 3.2.1 ቲዎስ (Theos)

ይህ በዕብራይስጡ ኤሎሂም ከሚለው ጋር ይመሳሰላል።



### 3.2.2 ጌታ (Lord / Kyrios/ Kurios)

ይህ ስም በአዲስ ኪዳን 717 ጊዜ የተጻፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 210 ጊዜ የተገለጸው በሉቃስ ወንጌል ነው። ይህም ጌታ (Owner, Master, Lord) የሚለውን ፍቺ ይዟል።

### 3.2.3 አባት (Father)

ይህ የእግዚአብሔር ስም በብሉይ ኪዳንም የነበረ ሲሆን (እግዚአብሔር የእስራኤላውያን አባት ነው)። እግዚአብሔር ይበልጥ በዚህ ስም የተጠራው በአዲስ ኪዳን ነው። ስሙ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት / አስገኝነትን ያመለክታል።

«አባት» የሚለው መጠሪያ በብሉይ ኪዳን 15 ጊዜ የተጻፈ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን 245 ጊዜ ተገልጿል። እግዚአብሔር እንደ አባትነቱ ለልጆቹ ጸጋና ሰላም ይሰጣል (ዘዳ 32:6፣ ኢሳ 63:16፣ 1ቆሮ 8:6፣ ኤፌ 3:14፣ ዕብ 12:9፣ ያዕ 1:17)።

የእግዚአብሔርን ማንነት በስሞቹ ማወቅ እንደሚቻል በዚህ ምዕራፍ ተመልክተናል። በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ ማንነቱ በባሕርያቱ ጭምር እንደሚታወቅ እናያለን።

# ምዕራፍ 4. <u>የእግዚአብሔር ባሕርያት</u>

የእግዚአብሔር ባሕርያት የእርሱን ማንነት መግለጫዎች ናቸው:: የእግዚአብሔር ባሕርይና እርሱነቱ (ማንነቱ) በአንድ ላይ የሚታዩ ሲሆኑ ባሕሪዎቹ እርሱነቱን ያሳያሉ፣ እርሱነቱ ደግሞ በባሕሪው ይገለጻል:: የእግዚአብሔር ባሕርያት የዘላለም ባሕርያት ናቸው፤ አይጨምሩም፣ አይቀንሱም::

የእግዚአብሔር ባሕርያት ሁሉም እኩል ናቸው:: አንደኛው ባሕርይው ከሌላኛው ባሕርይ ከፍ ብሎ የሚታይ አይሆንም:: ሁሉም ባሕርያት በስምምነት ይገኛሉ:: ለምሳሌ ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑ ነው:: እንዲሁም እግዚአብሔር ፈራጅ ነው:: ፍቅር መሆኑ እንዳይፈርድ አይከለክለውም፣ በኃጢአት ላይ በጽድቅ እንዲፈርድ እንጂ:: ስለሆነም በአንዳንዶች ዘንድ እንደሚባለው «እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ በማንም ላይ አይፈርድም፣ ምክንያቱም በፍቅር ውስጥ ፍርድ የለም» ብሎ ማሰብ የእግዚአብሔርን ማንነት/ ባሕርይ አለማወቅ ነው:: ለእግዚአብሔር «ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው» (መዝ 97:2)::

የእግዚአብሔር ባሕርያት ቁጥር ብዙ በመሆኑ ትክክለኛ ቁጥራቸው ግን አይታወቅም::18 በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ጐልተው የሚታዩት ናቸው::

---

18 Wayne Grudem in his book: <u>Systematic Theology: An Introduction to Biblical Doctrine</u>, 1994, Zondrevan Publishing House, Grand Rapids, pp 161-179, 186–187, for instance presents God's attributes as follows.

- **Incommunicable:-** 1. Independence 2. Unchageableness 3. Eternity 4. Omnipresence 5. Unity
- **Communicable:-**
  - A. Attributes describing God's Being (1. Spirituality 2. Invisibility)
  - B. Mental attributes (3. knowledge or omniscience 4. Wisdom, 5. Truthfulness (and faithfulness)
  - C. Moral attributes (6. Goodness 7. Love 8. Mercy (grace, patience) 9. Holiness 10. Peace (or order) 11. Righteousness (or justice) 12. Jealousy 13. Wrath
  - D. Attributes of purpose (14. will 15. freedom 16. Omnipotence (or power and sovereignity)
  - E. "Summary" attributes (17. perfection 18. Blessedness 19. Beauty 20. Glory)

የእግዚአብሔርን ባሕርያት ቀለል ባለ መንገድ ለመረዳት እንዲቻል የስነ መለኮት አስተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የማይተላለፉ ባሕርያትና የሚተላለፉ ባሕርያት ብለው በሁለት ዋና ክፍሎች ይከፍሏቸዋል::[19] በዚህ መጽሐፍም ይህን አከፋፈል እንጠቀማለን::[20]

## 4.1 የማይተላለፉ ባሕርያት

የማይተላለፉ ባሕርያት ተብለው የሚጠሩት የእግዚአብሔር ባሕርያት ከእግዚአብሔር ወደ ፍጥረታቱ (መላእክትና ሰው) የማይተላለፉና የእግዚአብሔር ብቻ የሆኑ ናቸው:: እነዚህ ባሕርያት በሰው ዘንድ የማይገኙ በመሆናቸው ብዙውን ጊዜ ለማገናዘብ አዳጋች ይሆናሉ::

የእግዚአብሔር የማይተላለፉ ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው::

4.1.1 እራስ በራስ መኖር (Independence / Self existence)
4.1.2 አለመለወጥ (Unchangeableness / Immutability)
4.1.3 አለመወሰን (Infinity / Eternity)

---

19ይህ አከፋፈል የእግዚአብሔርን ባሕርያት ለመረዳት የሚያግዝ ቢሆንም የእግዚአብሔርን ባሕርያት እንደዚህ መክፈል ግን ችግር ይኖረዋል:: የሚተላለፉ የተባሉት ባሕርያት በሙሉ ከእግዚአብሔር ወደሰው የሚተላለፉ አይደሉምና:: ለምሳሌ ሰዎች አዋቂዎች ቢሆኑም የእግዚአብሔርን ያህል እውቀት ፈጽሞ ሊኖራቸው አይችልም:: ከእውቀት ከፍላን እናውቃለንና (1ቆሮ 13:12) ተብሏል:: እንዲሁም የማይተላለፉ የተሰኙት ባሕርያትም ፈጽሞ የማይተላለፉ አይደሉም:: ጌታን የተቀበለ ሰው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም በሕይወት እንደሚኖር ያውቃል:: ከዚህም የተነሣ አንዳንዶች የማይተላለፉ ባሕርያት:- እግዚአብሔር ለሰው በጥቂቱ የሚያካፍላቸው ባሕርያት (Incommunicable attributes:- attributes of God that are less shared by us) እና የሚተላለፉ ባሕርያት:- እግዚአብሔር ለሰው በብዛት የሚያካፍላቸው ባሕርያት (communicable attributes:- attributes of God that are more shared with us) በሚል ይገልጿቸዋል::

20የእግዚአብሔር ባሕርያት አከፋፈል እዚህ ከተመለከተው ለየት ባለ ሁኔታ ሊሆን ይችላል:: ይህም:-
ሀ. በፍጥረቱ ዘንድ የማይገኙ ባሕርያት:- ሁሉን ቻይነቱ፣ አለመለወጡ፣ አለመወሰኑ፣ አለመከፍፈሉ፤
ለ. እርሱ በፈጠራቸው በፍጥረቱ ዘንድ በተወሰነ መጠን የሚገኙ ባሕርያት:- እውቀት፣ ጥበብ፣ ፍቅር፣ ቅድስና፣ ጽድቅ፣ ታማኝነት፣ ሥልጣን በሚል፣ ወይንም ደግሞ ክፍፍል ሳይደረግ በአንድ ላይ በመዘርዘር ነው::



### 4.1.1 እግዚአብሔር ራሱ በራሱ የሚኖር ነው

እግዚአብሔር ያልተፈጠረ ፈጣሪ፣ ከማናቸውም ነገር ነጻ ሆኖ በራሱ የሚኖር አምላክ ነው:: እርሱ ያደረገውንና የሚያደርገውን ሁሉ እንዲያከናውን ከእርሱ ውጪ የሆነ ማንም አልመራውም፣ አልረዳውም አልመከረውም:: ሁሉንም እንደራሱ ፈቃድና ዕቅድ አድርጓል:: እግዚአብሔር በእርሱነቱ፣ በፈቃዱ፣ በሥልጣኑ፣ በሃሳቡ፣ በዓላማው ነጻ ነው (መዝ 33:11፣ 115:3፣ ዳን 4:35፣ ዮሐ 5:26፣ ሮሜ 11:33-34)::

እግዚአብሔር ራሱ በራሱ ለዘላለም የሚኖር አምላክ ስለሆነ ራሱን በራሱ ጠርቷል:: «እኔ ነኝ» (ዘጸ 3:14) የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው:: የእግዚአብሔር ማንነት የሚወሰነው በራሱ በእግዚአብሔር ነው:: ሌላውም ፍጥረት ሁሉ በእርሱ የተፈጠረ ነው:: ዳዊት «ተራሮች ሳይወለዱ፣ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ» ብሏል (መዝ 90:2):: እንዲሁም ሐዋርያው ዮሐንስ «ጌታችንና አምለካችን ሆይ፣ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና፣ ተፈጥረውማልና ክብር፣ ውዳሴ፣ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል» (ራእ 4:11) እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን የሚያኖሩትን ሽማግሌዎች ተመልክቷል::

እግዚአብሔር ራሱ በራሱ የሚኖር ለመኖርም ምንም የማያስፈልገው ነጻ አምላክ ነው:: እርሱ ከፍጥረቱ ምንም አይፈልግም:: ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ሲያስረዳ «ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ  እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤ እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና፣ አንዳች እንደሚጐድለው በሰው እጅ አይገለገልም» ይላል (ሐዋ 17:24-25):: ጌታ እግዚአብሔር ስለራሱ ለኢዮብ ሲናገር «እመልስለትስ ዘንድ መጀመሪያ የሰጠኝ ማን ነው? ከሰማይ ሁሉ በታች ያለው ገንዘቤ ነው» (ኢዮ 41:3) ብሎታል:: እንዲሁም:- በመዝ 50:10-12

የምድረ በዳ አራዊት ሁሉ
በሺህ ተራራዎች ያሉ እንስሶችም የእኔ ናቸው::
የሰማይን አዕዋፍ ሁሉ አውቃለሁ፣
የምድረ በዳ አራዊትም በእኔ ዘንድ ናቸው::
ብራብም ለአንተ አልነግርህም፣
ዓለምና ሞላው የእኔ ነው፣ ብሏል::

እግዚአብሔር ምንም የማያስፈልገውና ከዘላለም ራሱ በራሱ የሚኖር አምላክ ሆኖ ሳለ ለእርሱ ክብር እንዲሆን ሰውን ፈጥሯል:: እግዚአብሔር በኢሳይያስ « ... በስሜ የተጠራውን፣ ለክብሬም የፈጠርሁትንና፣ የሠራሁትን ያደረግሁትን ...» (ኢሳ 43:7) ይላል:: ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል «ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ» (ኤፌ 1:12) ነው::

## 4.1.2 <u>እግዚአብሔር አይለወጥም</u>

እግዚአብሔር በእርሱነቱ፣ በተስፋው፣ በዕቅዱ፣ ወዘተ... አይለወጥም:: በእራሱ ላይ አንዳች ነገር አይጨምርም፣ አይሻሻልም፣ አይማርም፣ አይመራመርም:: መለወጥ ለተሻለ ወይም ወደ ክፉ ነገር ነው:: እግዚአብሔር ግን ፍጹም አምላክ በመሆኑ ወደየትኛውም አይለወጥም:: ሰዎች፣ ሁኔታዎች፣ ጊዜያት ይለዋወጣሉ:: እግዚአብሔር ግን በእርሱነቱ፣ በባሕርይው አይለወጥም:: «እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም ...» (ሚል 3:6) ያለ እግዚአብሔር በእርሱነቱ አይለወጥም፣ ቃሉ አይለወጥም፣ ፈቃዱ አይቀየርም (ዘዳ 3:6፣ ኢሳ 41:4 እና 48:12፣ ሮሜ 1:23፣ ዕብ 1:11 እና 12)::

### ሀ) <u>እግዚአብሔር እርሱነቱን ሊለውጥ አይችልም</u>

እግዚአብሔር አንድ አምላክ በሦስት አካላት ተገልጾ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራል:: ይህ በአንድነት ሦስትነት የማይለወጥ እርሱነቱ ነው:: እርሱነቱ ስለማይለወጥ ባሕርይውም አይለወጥም:: እርሱ ያልነበረበት ጊዜ አልነበረም፣ ለወደፊትም የማይኖርበት ጊዜ አይኖርም:: እግዚአብሔር አላደገም ወይም አልሸመገለም:: ማንነቱ የሚለወጠው ወይንም በማንነቱ ላይ ዕድገት ወይም ለውጥ የሚያመጣ ማናቸውም ውጫዊ ተፅዕኖ የሌለበት ጌታ ነው::

ይህ ወሰን የሌለው፣ ራሱ በራሱ የሚኖር እግዚአብሔር ወደየትም ሊቀየር አይችልም::21 በራሱ ላይ የሚጨምረው ወይም የሚቀንሰው

21የፕሮሰስ ቲዎሎጂ ተከታዮች የእግዚአብሔርን አለመለወጥ ይቃወማሉ::
«Process theology:- a theological position that says; process and change are essential aspects of genuine existence, and that therefore God must be changing overtime also, just like everything else that exists. In fact, Charles Hartshorne, the father of process theology, would say that God is continually adding to himself all the experiences that happen anywhere in the universe, and thus God is continually changing. ...[Process theologians



ባሕርይ የለውም:: እርሱ አሁን ካለበት ፍጹም ጽድቅ የበለጠ ጻድቅ ሊሆን አይችልም:: ለሰው ያለው ፍቅር አይለወጥም:: የእርሱ ኃይል፣ ጥበብ፣ ቅድስና አይለወጥም::

እግዚአብሔር የፈጠራቸው ትልቅም ሆኑ ትንሽ ነገሮች ሁሉ ይለወጣሉ፣ ለሚኖሩበትም ዘመን ዳርቻ አላቸው:: እግዚአብሔር ግን ስለ እራሱ «እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» ብሏል (ሚል 3:6):: ዳዊትም በመዝሙር እንዲህ ይላል:-

> አቤቱ፣ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፣
> ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው::
> እነርሱ ይጠፋሉ፣ አንተ ግን ትኖራለህ፣
> ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፣
> እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፣ ይለወጡማል::
> አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣
> ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም (መዝ 102:25-27)::

እንዲሁም የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ የሆነው እግዚአብሔር በመልካምነቱ አይለወጥም:: መጽሐፍ ቅዱስ በያዕ 1:17 «በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ» ይላል::22

think that] As we act, and the universe changes, God is truely affected by these actions and the being of God changes- God becomes something other than what he was>> Wayne Grudem, <u>Ibid</u> p.166
ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አይመራመርም፣ እውቀት አይጨምርም፣ ያወቀውን አይረሳም፣ እንደ ሰው አይደነቅም፣ አስቸኳይ መፍትሔ የሚያስፈልገው ድንገተኛ ነገር ገጥሞት አያውቅም፣ አይገጥመውምም:: እግዚአብሔር አይለወጥም:: ስለሆነም ይህ ፕሮሰስ ቲዎሎጅ (process theology) በጣም የተሳሳተና ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ትምህርት ሲሆን ሰዎች በምድራዊ አስተሳሰብና እውቀት ስለ ዘላለማዊው እግዚአብሔር ማንነትና ባሕርይ ለመረዳት የሞከሩበት መላምት ነው:: የእግዚአብሔርን ማንነትና ባሕርይ መረዳት የሚቻለው ራሱ እግዚአብሔር ስለራሱ የገለጸውን በእምነት በመቀበል ነው:: እግዚአብሔር ስለ ራሱ የተናገረው ደግሞ «እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» (ሚል 3:6) በማለት ነው::

22 በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ... «በጐ ስጦታና ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ፣ በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ ከመዞር የተነሣ የሚያርፍ ጥላም የለም» ይላል::

### ለ) እግዚአብሔር ቃሉን (ተስፋውን) አይለውጥም

ሰው በቃሉ ይወላውላል፣ አንድ ጊዜ የተናገረውን ይለውጣል፣ ይሸራል:: የእግዚአብሔር ቃል ግን የጸና ነው (መዝ 119:60፣ ማቴ 5:18፣ ዮሐ 10:36):: እግዚአብሔር ከሰው የተለዬና ፍጹም ስለሆነ አይዋሽም፣ ቃሉንም አይለውጥም (ዘኁ.23:19):: ስለሆነም እርሱ የገባውን ተስፋ ይፈጽማል (ሰቆ 3:22-23፣ 1ዮሐ 1:9)::

እግዚአብሔር ያቀደውን የሚፈጽም ምክሩም የጸና አምላክ ነው:: «የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል፣» (መዝ 33:11):: እንዲሁም እግዚአብሔር በኢሳይያስ 46:9-11 «... እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም:: በመጀመሪያ መጨረሻውን፣ ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ ... ተናግሬአለሁ እፈጽምማለሁ አስቤአለሁ አደርግማለሁ» ብሏል::

### ሐ) እግዚአብሔር ፈቃዱን አይቀይርም

ሰው ሀሳቡን የሚለውጠው እውቀት የሚጐድለውና የወደፊቱን የማያውቅ በመሆኑ ነው:: ሰው በሀሳቡ ተለዋዋጭ በመሆኑ እንደሚዞሩ ከዋክብት (ይሁዳ 13)፣ እረፍት እንደሌለውና በማዕበል እንደሚታወክ ባሕር ነው (ኢሳ 57:20):: ሰው ዛሬ «ሆሣዕና[23] ለዳዊት ልጅ» (ማቴ 21:2) ቢል ነገ ደግሞ «አስወግደው» (ማር 15:13) ሊል ይችላል:: እግዚአብሔር ግን ስለ ማንነቱ ስለ ፍጹም ባሕሪው ፈቃዱን አይቀይርም (መዝ 33:11፣ ዕብ 6:17):: እግዚአብሔር ሁልጊዜ ኃጢአትን ይጠላል:: ኃጢአተኛውን ግን ይወዳል (1ሳሙ 15:11፣ ኤር 26:13)::

እግዚአብሔር በእርሱነቱ፣ በባሕርይው የማይለወጥ ከሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር እንደተጸጸተ፣ እንዳዘነ፣ ሊያደርግ ያሰበውን እንደተወ፣ የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች አሉ (ዘጸ.32:14፣ ዘፍ.6:6፣ 1ሳሙ.15:10፣ ኢሳ.38:1-6፣ ዮና.3:10):: እነዚህ

---

23 ሆሣዕና ማለት «አሁን አድን» ማለት ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ 1972 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ በሴንትራል ማተሚያ ቤት:: The word hosanna is of Hebrew origin which means "Oh save!". But the use of the term in other places such as Mt 21:15 "Hosanna to the son of David" is used to express joy, welcome and to ascribe praise to Jesus the Christ.



ከእግዚአብሔር አለመለወጥ ጋር እንዴት ነው የሚታዩት? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ስለሚችል ጥቂት ምላሽ መስጠት ተገቢ ይሆናል::

እግዚአብሔር የማይለወጥ ሲሆን እርሱ ግን በሰው ታሪክ ውስጥ የሚሆነው ለውጥ ሁሉ ይነካዋል:: ሰዎች በምናደርጋቸው የተሳሳቱ ውሳኔዎች፣ በምንፈጽማቸው ኃጢአቶች እግዚአብሔር ያዝናል:: እግዚአብሔር በሕዝቡ ሁኔታ ስሜቱ ይጎዳል ያዝናል (ዘፍ 6:5-6፣ መዝ 78:40-41፣ ኢሳ 63:7-10፣ ኢሳ 54:9-10፣ ሆሴ 13:6-7):: እግዚአብሔር የሃዘኑን ጥልቀት ሲገልጽ «እስከ መቼ ...?» ብሎ ይናገራል (ዘኁ 14:11፣ ኤር 4:14 እና 13:27፣ ሆሴ 6:4 እና 8:5):: ስለሆነም የተለወጠው እግዚአብሔር ሳይሆን ሁኔታዎቹ ናቸው::

እግዚአብሔር በባሕርይው መሐሪና ይቅር ባይ በመሆኑ በንስሐ ወደ እርሱ ለሚቀርቡት ምሕረትን ይሰጣል:: ስለዚህ ለውጥ ያለው በሰው ዘንድ ነው:: ሰው ራሱን አዋርዶ በንስሐ ሲቀርብ ይቅር ማለት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው:: አንዱ በአንድ ስፍራ «እግዚአብሔር ለተለያዩ ሁኔታዎች የተለያየ ስሜት ይሰማዋል፣ እርምጃም ይወስዳል» እንዳለው ነው:: ("God acts and feels differently in response to different situations").

በአጠቃላይ የእኛ መጥፎ ምርጫ እኛን ይጐዳናል፣ እግዚአብሔርንም ያሳዝነዋል:: ስለዚህ የእግዚአብሔር አለመለወጥ በማንነቱ ላይ የተመሠረተ የባሕርይ የእግዚአብሔርን ጽናት/ ተመሳሳይነት ("Moral Consistency") ያመለክታል:: ሰዎች ሲለዋወጡ እግዚአብሔር እንደ ባሕርይው መልስ ይሰጣልና:: ዳዊት በመዝ 18:24-26:-

> እግዚአብሔር እንደ ጽድቄ፣
> እንደ እጄም ንጽህና በዓይኖቼ ፊት መለሰልኝ፣
> ከቸር ሰው ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ፣
> ከቅን ሰው ጋር ቅን ሆነህ ትገኛለህ፣
> ከንጹሕ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ፣
> ከጠማማ ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ፣ ይላል::

በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር መንፈስ ሆኖ ሳለ (ዮሐ 4:24) በመጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደ ሰው ዐይን፣ ጆሮ፣ ልብ፣ ... እንዳለው (ዘዳ 5:15፣ 2ዜና 16:9) አድርጎ ይናገራል:: ይህን አገላለጽ በቀጥታ በመውሰድ እግዚአብሔርን እንደ ሰው አስመስሎ ለመግለጽ ቢሞከር የሥነ መለኮት ግንዛቤና የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ችግር ያመጣል:: ይኸው እግዚአብሔር በሌላ ቦታ ደግሞ ላባና ክንፍ

እንዳለው (መዝ 91:4)፣ የሚያጠፋ እሳት እንደሆነ (ዕብ 12:29) ተገልጿል:: እንዲህ ዓይነት ሰው ደግሞ እንደሌለ ይታወቃል::

እንግዲህ እግዚአብሔር ፍጹም የማይለወጥ አምላክ ሆኖ እያለ እንደተጸጸተ፣ ያሰበውንም እንደተወ የሚናገረው ይህን ዓይነት አገላለጽ ሰው ሊረዳው በሚችለው በሰው ዓይነት አነጋገር (Anthropomorphism) የተነገረ ነው ማለት ነው:: ይህ ዓይነት አገላለጽ እግዚአብሔርን የተለወጠ ያስመስለዋል፣ የተለወጡት ግን ሰውና ሁኔታዎች ናቸው:: በዘኍ 23:19፣ 1ሳሙ 15:29፣ ሮሜ 11:29፣ እንደምናነበው እግዚአብሔር አይጸጸትም፣ እንደ ሰውም ሀሳቡን አይቀይርም (ዘኍ 23:19)::[24]

## 4.1.3 እግዚአብሔር ወሰን የለውም

እግዚአብሔር የጊዜ፣ የቦታ፣ ወዘተ ... ወሰኖች ሁሉ የማይዙት (የማይገዙት) ወሰን የሌለውና ሊወሰን የማይችል አምላክ ነው:: እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የለውም:: እርሱ በጊዜ አይወሰንም፣ ሊያደርግ የሚፈልገውን ግን በጊዜው ያደርጋል:: የእግዚአብሔርን አለመወሰን በዘላለማዊነቱና በሁሉም ቦታ በመገኘቱ መረዳት ይቻላል::

### ሀ) ዘላለማዊነቱ

ዘላለማዊነት እጅግ በጣም ረጅም ዘመን አይደለም፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ጊዜ እንጂ:: እግዚአብሔር ከጊዜ በላይ ነው፣ በጊዜ ሊለካ አይችልም፣ ጊዜን የፈጠረ እርሱ ነውና!! እርሱ ለዘላለም ያው ነው:: እርሱ አያድግም፣ አይሸመግልም፣ በባሕርይው መለወጥ የለም (መዝ 102:12፣ ዘፍ 21:39፣ ኤፌ 3:21፣ 1ጢሞ 6:16)::

---

[24] In this respect Wayne Grudem explains: "These can be understood as expressions of God's present displeasure toward the sinfulness of man... imply that God's previous action led to events that in the short term, caused him sorrow, but that nonetheless in the long term would ultimately achieve his good purposes. This is some what analogous to a human father who allows his child to embark on a course he knows will bring much sorrow, both to the parent and to the child, but who allows it nonetheless because he knows that greater long term good will come from it." Ibid p.165.



የእግዚአብሔር «የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም» (ኢዮ 36:26):: እርሱ ከሁሉ ነገር በፊት የነበረ ከሁሉም ነገር በኃላ የሚኖር አልፋና ኦሜጋ ነው (ራእ 1:8):: እግዚአብሔር ሺህ ዓመትን እንደ ትናንት፣ ሌሊቱን በትጋት ለተወሰነ ጊዜ እንደሚጠብቅ ሰው ያየዋል (መዝ 90:4):: በእርሱ ፊት «አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፣ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን» ነው (2ጴጥ 3:8)::

እግዚአብሔር በጊዜ የማይወሰን ዘላለማዊ አምላክ ሆኖ ሳለ በምድር ላይ ሀሳቡን የሚያከናውነው በጊዜ ውስጥ ነው:: ልጁን የላከው «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ» ነው (ገላ 4:4):: ከጥንት ጀምሮ የተናገረ አምላክ «በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን» (ዕብ 1:1-2):: እርሱ የጊዜ ጌታ ነው::

### ለ) በቦታ አለመወሰኑ / በሁሉም ቦታ መገኘቱ

እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ ይገኛል፣ በማናቸውም ቦታ የሚደረገውን ሁሉ ያውቃል:: እርሱ በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ የሚገኘው በሙሉ በእርሱነቱ (with his whole Being) ነው:: እግዚአብሔር በቦታ ሊወሰን፣ ሊያዝ የማይችል ከቦታ በላይ የሆነ አምላክ ነው (1ነገ 8:27):: እርሱ ከፍ ባለ ቦታ ይኖራል (ኢሳ 57:15):: ሰማይ ዙፋኑ ነው ምድርም የእግሩ መረገጫ (ማቴ 5:34፣ ኢሳ 66:1):: እርሱ በሰማይም ሆኖ ወደ ምድር ይመለከታል (ኢሳ 63:15):: በሰማያት የሚኖር እግዚአብሔር (ማቴ.6፣9) ወደ ምድርም ይወርዳል (ዘፍ 11:5):: በሲና ምድረ በዳ የነበረውን የማደሪያውን ድንኳን እና ሰሎሞን ያሠራውን ቤተ መቅደስ ክብሩ ሞልቶታል (ዘጸ 40:34፣ 1ነገ 8:11):: እንዲሁም 2ነገ 7:2፣ ኢዮ 22:12-14፣ ምሳ 15:3፣ ኢሳ 66:1፣ ራእ 14:10፣ ሐዋ 7:48-49፣ 17:27-28፣ ገላ 2:20 ይመልከቱ::

እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ የሚገኝ ላልመሰላቸው ሰዎች እግዚአብሔር ራሱ በኤርምያስ በኩል እንዲህ ብሏል:: «ሰው በስውር ሲሸሽግ፣ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የምላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር» (ኤር 23:24):: ስለሆነም ከእግዚአብሔር መሰወር ወይም ማምለጥ አይቻልም (መዝ 139:7-10)::

እግዚአብሔርን ምንም ቦታ ሊይዘው አይችልም፣ በሁሉም ቦታ ሁልጊዜ ይገኛል:: ይህ ማለት ግን ሁሉ ነገር እግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ፈጣሪ ከፍጥረቱ የተለየ ነው:: በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ሲፈጥር

እርሱ ግን ከፈጠረው ነገር የተለየ መሆኑን ያሳየናል::[25] እግዚአብሔር ከዘላለም አምላክ ነው:: ፍጥረት ሁሉ ግን ከተወሰነ ጊዜ ጀምሮ የሚኖር ነው::

እግዚአብሔርን በቦታ ለክቶ ወይም መጥኖ መግለጽ አይቻልም:: ትልቅ በሆነ ነገር ልንገምተው ብንሞክር እርሱ ከዚያም በላይ ነው:: ሊመጠን የማይቻል እጅግ ታላቅ ነው ብለን ብንገልጸው በእያንዳንዱ ቦታ ይገኛል (መዝ 139:7-10)፣ በሰውም ውስጥ ይኖራል (1ቆሮ 6:19-20):: ይህን ደግሞ በማሰብ ትንሽ እንደሆነ ቢመስለን ሰሎሞን «እነሆ፣ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም» (1ነገ 8:27) እንዳለ እርሱ እጅግ ታላቅ ነው:: እንግዲህ እግዚአብሔርን በምንም መመሰልና መግለጽ አይቻልም (ዘጸ 20:4-6)::

እግዚአብሔር በቦታ የተወሰነ ባለመሆኑ በሁሉም ቦታ ይገኛል:: ሆኖም በተለያዬ ቦታ የሚገኘው በተለያየ ሁኔታ ወይም ለተለያየ ዓላማ ነው:: ጌታ በሕዝቡ መካከል የሚያድረው ለመባረክ ነው (ራእ 21:3-4):: ጌታ ኢየሱስ «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን»:: ብሏል (ዮሐ 14:23):: ይህም ኅብረት ለማድረግ ነው (ራእ 3:20):: «የጌታ መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ» (2ቆሮ 3:17):: እግዚአብሔር በሰማይ በልዩ ሁኔታ ክብሩ ተገልጾ ይገኛል (ራእ 4)::

እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ስላለ በየትኛውም ቦታ ወደ እርሱ የሚደረገውን ጸሎት ይሰማል፣ አምልኮን ይቀበላል:: ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር የማይገኝበት የቦታ ክልል ሊኖር አይችልም:: ሰው እንደ ዮሴፍ በእስር ቤት (ዘፍ 29)፣ እንደ ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ (ዳን 6)፣ እንደ ነህምያ በቤተ መንግሥት (ነህ 2)፣ እንደ እስራኤላውያን በምድረ በዳና በባሕር ላይ (መዝ 107:4-9፣ 24-30)፣ እንደ ዮናስ በዓሳ ሆድ ውስጥ፣ እንደነጳውሎስ በማዕበል በሚታወክ መርከብ ላይ (ሐዋ 27)፣ ወዘተ... ቢሆን በዚያ ቦታ እግዚአብሔር አለ:: ከእግዚአብሔርም ፊት

---

25"God is present everywhere in His creation, but that He is also distinct from His creation. How can this be? The analogy of a sponge is not perfect, but it is helpful. Water is present everywhere in the sponge, but the water is still completely distinct from the sponge. Now this analogy breaks down at very small points within the sponge, where we could say that there is sponge at one point and not water, or water and not sponge. Yet this is because the analogy is dealing with two materials that have spatial characterstics and dimensions, while God does not." Ibid p.153.



በምንም መንገድ ቢሆን መደበቅ አይቻልም፣ ከእርሱም ፊት እርቆ መሰደድ ወይንም በሌላ አገር ጥገኝነት መጠየቅ አይቻልም::

ጌታ በአሞጽ በኩል እንዲህ ብሏል:-

> ... የሚሸሽም አያመልጥም፣ የሚያመልጥም አይድንም:: ወደ ሲኦል ቢወርዱ እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች፣ ወደ ሰማይም ቢወጡ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ፣ በቀርሜሎስም ራስ ውስጥ ቢሸሽጉ ፈልጌ ከዚያ አወጣቸዋለሁ፤ በጥልቅ ባሕርም ውስጥ ከዓይኔ ቢደበቁ ከዚያ እባቡን አዝዛለሁ፣ እርሱም ይነድፋቸዋል፣ በጠላቶቻቸው ፊት ተማርከው ቢሄዱ ከዚያ ሰይፍን አዝዛለሁ፣ እርሱም ይገድላቸዋል፣... (አሞጽ 9:1-4)::

ስለዚህ ከእግዚአብሔር የምንደብቀው ነገር ወይም ከእርሱ የምንሸሸግበት ቦታ የለም::

## 4.2 <u>የሚተላለፉ ባሕርያት</u>

የሚተላለፉ የእግዚአብሔር ባሕርያት ተብለው የሚጠሩት ባሕርያት ኀሊና ያላቸው ፍጥረታት (ማለት ሰውና መላእክት) ከእግዚአብሔር ጋር በተወሰነ መጠን የሚካፈሏቸው ናቸው:: እነዚህ ባሕርያት በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ይበልጥ እየታዩ ሲመጡ ያ ሰው የጌታን መልክ እየመሰለ ማደጉን ያመለክታሉ (2ቆሮ 3:18)::

የእግዚአብሔር የሆነና ወደ ሰው ሊተላለፉ የሚችሉትን እነዚህን ባሕርያት በሦስት በመክፈል እንደሚከተለው መመደብ ይቻላል::

### 4.2.1 <u>የማወቅ ባሕርያት</u>

ሀ. <u>እውቀት</u>

እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገርና ሁኔታ በዘላለማዊ እውቀት ያውቀዋል:: በሰማይ፣ በምድር፣ ከምድር በታች ያለውን ዝርዝር ነገር ሁሉ ያውቃል:: እርሱ አይማርም ወይም በሂደት ውስጥ የሚረዳው ነገር የለም:: ስለ ሁሉም ነገር ሁሉም መረጃ አለው:: ሰው ግን እውቀትን የሚያገኘው በማየት፣ በመስማት፣ በማንበብ፣ በማጥናት፣ በመመራመር፣ ወዘተ ... ነው:: የእግዚአብሔር እውቀት ፍጹም ነው::

ቃየል ወንድሙን ቢገድል (ዘፍ 4:9)፣ ሣራ ተደብቃ በልቧ ብትስቅ (ዘፍ 18:12-15)፣ አካን እርምን ወስዶ ቢደብቅ (ኢያ 7:11፣ 22-24)፣ ዳዊት የሠራውን ኃጢአት ሊደብቅ ቢጥር (1ሳሙ 12:7) እግዚአብሔር ግን ሁሉንም ያውቃል::[26] እግዚአብሔር አንድን ነገር ከሌላው የበለጠ ወይንም ያነሰ አያውቅም፣ ሁሉንም ነገር ምንም ሳይቀር ያውቃል:: እውቀቱ ከዘላለም ነው (ሐዋ 15:18፣ 1ሳሙ 2:3፣ መዝ 94:9፣ መዝ 147:5፣ ኢሳ 29:15፣ ዳን 2:22፣ ዕብ 4:13፣ 1ዮሐ 3:20)::

- እግዚአብሔር ያለፈውን ሁሉ ያውቃል:: (ሐዋ 15:18፣ 1ዮሐ 3:20)::
- እግዚአብሔር ያሁኑን በሙሉ ያውቃል
  - ተፈጥሮን በሙሉ ያውቃል:: የከዋክብትን ቁጥር ያውቃል፣ በስምም ይጠራቸዋል:: (ዘፍ 15:5፣ መዝ 147:4-5፣ ኢሳ 40:26)::
  - ሰውን በሙሉ ያውቃል፣የሰውን መንገድ ያውቃል (መዝ 119፣ 168፣ 139:3፣ ኢዮ 24:23፣ ምሳ 25:21፣ ዕብ 4:13)::
  - የሰውን ቃል ያውቃል:: (መዝ 19:14፣ ሉቃ 11:17፣ 1ቆሮ 3:20)::
  - የሰውን ሃሣብ ያውቃል (መዝ 139:2፣ ሉቃ 11:17፣ 1ቆሮ 3:20፣ ሕዝ 11:5)::
  - የሰውን ፍላጐት ያውቃል (ሐዋ 1:24፣ ሮሜ 8:27)::
  - ትንንሽና ዝርዝር ጉዳዮች ያውቃል (ማቴ 10:29-30)::

26 በእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ላይ ሰዎች የሚያነሷቸው ጥርጣሬዎች አሉ:: ለምሳሌ "Objection to the biblical teaching about God's omniscience has been brought from Jeremiah 7:31, 19:5 and 31:35, where God refers to the horrible practices of parents who burn to death their own children in the sacrificial fires of the pagan god, Baal, and says, "which I didnot command nor did it come into my mind" (Jer.7:31). Does this mean that before the time of Jeremiah God had never thought of the possibility that parents would sacrifice their own children? Centainly not, for that very practice had occurred a century earlier in the reigns of Ahaz (2 Kings 16:3) and Hoshea (2Kings 17:17) and God himself had forbidden the practice eight hundred years earlier under Moses (Lev.18:21). The verses in Jeremiah are probably better translated quite literally, "nor did it enter into my heart"... giving the sense, "nor did I wish for it, desire it, think of it in a positive way". Ibid p.192. ስለሆነም እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል::



- ሊሆን ያለውንና የወደፊቱን በሙሉ ያውቃል (ኢሳ 41:21፣ 42:9፣ 46:10፣ 48:5-7):: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉና ጊዜያቸውን ጠብቀው የተፈጸሙ ትንቢቶች ሁሉ እግዚአብሔር የወደፊቱን እንደሚያውቅ ማስረጃዎች ናቸው (ሚኪ 5:2):: እርሱ የተናገራቸው ሁሉ ይፈጸማሉ (ሉቃ 24:44):: እግዚአብሔር ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን እኩል ያውቃል:: ስለሆነም እግዚአብሔር ታሪክንና የእኛንም ሕይወት ይቆጣጠራል::[27]

እግዚአብሔር አንድ ሁኔታ ባይፈጸም እንኳን ሊፈጸም የሚችለውን ያውቃል:: በ1ሳሙ 23:11-13 የሚከተለውን ቃል እናገኛለን::

> ዳዊትም:- የእስራኤል አምላክ አቤቱ፣ ... የቅዒላ ሰዎች በእጁ አሳልፈው ይሰጡኛልን? ባሪያህስ እንደ ሰማ ሳኦል በውኑ ይወርዳልን? የእስራኤል አምላክ አቤቱ፣ እንድትነግረኝ እለምንሃለሁ አለ:: እግዚአብሔርንም:- ይወርዳል ... አሳልፈው ይሰጡአችኋል ብሎ ተናገረ:: ዳዊትና ... ሰዎችም ተነስተው ከቅዒላ ወጡ፣ መሄድም ወደሚችሉበት ሄዱ:: ሳኦልም ዳዊት ከቅዒላ እንደሸሸ ሰማ፤ ስለዚህም ከመውጣት ቀረ::

እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል:: የእግዚአብሔር እውቀት የማንኛውም እውቀት መሠረት ነው:: እውቀት ሁሉ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ነው:: ሌላውን እውቀት በትክክል መረዳትና መተርጐም የሚቻለው ከእግዚአብሔር እውቀት አንጻር ሲታይ ብቻ ነው::

27እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የሚያውቅ ከሆነ ሰው ነፃ ፈቃድ አለው ወይ? የሚል ጥያቄ ብዙ ጊዜ ይነሳል:: አንዳንድ የስነ መለኮት አስተማሪዎችም «እግዚአብሔር የወደፊቱን ሁሉንም ነገር አያውቅም - ያልተከናወኑ ነገሮችን በእርግጠኝነት የሚያውቀው ሲከናወኑ ነው» ብለው የሚናገሩ አሉ፡ ይህ አስተሳሰብ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: Grudem commenting on the subject says: «... Augustine said that God has given us "reasonable self-determination"... our choices and decisions are "reasonable". [in that] we think about what to do, consciously decide what we will do, and then we follow the course of action that we have chosen... we have "self determination"... affirming that our choices really do determine what will happen. It is not as if events occur regardless of what we decide or do, but rather that they occur because of what we decide and do." Ibid pp.192-193. ከዚህ ሀሳብ ጋር ለተዛመደ ማብራሪያ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ በአባሪነት የተያያዘውን ይመልከቱ::

እግዚአብሔር የማይመጠን እውቀት አለው፣ ሁሉንም ያውቃል (ዘዳ 2:7፣ 1ሳሙ 16:7፣ 1ዜና 28:9,17፣ መዝ 139:1-4፣ ሮሜ 11:33)::

### ለ. <u>ጥበብ</u>

ጥበብ ማለት በአጭር ቃል እውቀትን በሥራ ላይ (በተግባር) በትክክል ማዋል ነው:: ሰው ያወቀውን ነገር እንኳን በትክክል ለማከናወን ይሳነዋል:: በእግዚአብሔር ዘንድ ግን መሳሳት የለም፣ ሁሉንም በጥበብ ያደርጋል::

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል:: ደግሞም ዓላማውን ለመፈጸም ይህን እውቀት ትክክል (ፍጹም) በሆነ ሁኔታ ለማከናወን ጥበብ አለው:: ይህንም የሚያደርገው ለራሱ ክብር ነው:: እግዚአብሔር ተፈጥሮን በየዓይነቱ መፍጠሩ (መዝ 104:24፣ 1ቆሮ 15:41)፣ የተፈጠረው ሁሉ ውብና መልካም መሆኑ (መክ.3:11)፣ ፍጥረቱም ሁሉ በዓላማ መፈጠሩ (ምሳ 30:24-28)፣ ፍጥረትን እየተንከባከበ ማኖሩ (ኢዮ38፣ መዝ 104) የእግዚአብሔርን ጥበብ ያሳያል (ኢሳ 40:13-14፣ ሮሜ 11:33፣ ቆላ 1:16)::

እግዚአብሔር ሁልጊዜ መልካምን ነገር ይመርጣል፣ በጥበቡ ያደርጋል:: «በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል አለ» (ኢዮ 12:13):: ዳዊትም «ሁሉን በጥበብ አደረግህ» ብሏል (መዝ 104:24):: ለጥበቡ ወሰን የለውም (ሮሜ 11:33)::

የእግዚአብሔር ጥበብ በማዳን ሥራው ተገልጿል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል የዓለም ጥበብ ሞኝነት (1ቆሮ 1:18-20) ሲሆን «የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው» (1ቆሮ 1:24):: እግዚአብሔር አስቀድሞ ያሰበውና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የፈጸመው ሥራ «ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፣» ነው (ኤፌ 3:10-11):: በቤተ ክርስቲያን በኩል የተገለጠው የእግዚአብሔር ጥበብ ከተለያየ ወገንና ቋንቋ የሆነውን ልዩ ልዩ ሕዝብ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ የማድረግ ምሥጢር ነው:: ይህም ለአለቆችና ሥልጣናት (ለሰይጣንና ለመላእክቱ) ጭምር ይታወቅ ዘንድ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አንዱ ተግባሯ እግዚአብሔር በሚያስደንቅ ጥበቡ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለሕዝቡ የሰጠውን አንድነት መጠበቅና ስለዚህም በቃልና በኑሮ መመስከር ነው::



የእግዚአብሔር ጥበብ በልጆቹ ላይ የሚደርሰውን ነገር ሁሉ ለመልካም በመለወጥና የልጁን መልክ እየመሰልን እንድናድግ በማድረግ ይገለጻል (ሮሜ 8:28-29):: ሰዎች በክርስቲያኖች ላይ ክፉ ለማድረግ እንኳ ቢነሳሱ «ከበላተኛ ውስጥ መብል፣ ከብርቱም ውስጥ ጥፍጥ» (መሳ 14:14) የሚያወጣ አምላክ ሁኔታውን ለእራሳችንና ለሌሎችም ጥቅም እንዲሆን በጥበቡ ያደርገዋል:: ዮሴፍ «እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው» (ዘፍ 50:20) እንዳለው እግዚአብሔር ክፉ የሆነውን ነገር ለመልካም ማድረግ ይቻለዋል::

የእግዚአብሔር ጥበብ ከእርሱ ወደ ሰው የሚተላለፍ ነው (ያዕ 1:5):: ጥበበኛው አምላክ የሰጠው ቃል የሚያነበውንና የሚኖርበትን ሰው ጥበበኛ ያደርጋል:: ዳዊት እንዳለው «የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስን ይመልሳል፤ የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው፤ ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል» (መዝ 19:7):: ሙሴም እስራኤላውያንን «... አምላኬ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ሥርዓትንና ፍርድን አስተማርኋችሁ:: ጠብቁአት አድርጓትም፤ ይህችን ሥርዓት ሁሉ ሰምተው:- በእውነት ይህ ታላቅ ሕዝብ ጠቢብና አስተዋይ ሕዝብ ነው በሚሉ በአሕዛብ ፊት ጥበባችሁና ማስተዋላችሁ ይህ ነው፤» (ዘዳ 4:5-6)::

እግዚአብሔርን በማክበርና በመፍራት የሚኖር ሰው ጥበበኛ ሰው ነው (ምሳ 9:10):: ጥበብ የምትገኘው በትሕትና መንገድ ነው (ምሳ 11:2፣ ያዕ 3:13)::

እንግዲህ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው «ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን» (ሮሜ 16:27)::

### ሐ. <u>እውነተኛነት/ ታማኝነት</u>

#### ሐ.1 <u>እውነተኛነት</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ነው:: እርሱም ብቻ እውነተኛና ታማኝ ነው:: እርሱ ሊዋሽ አይችልም:: እርሱ የሚናገረው ሁሉ እውነት ነው:: እርሱ ስለ ሰው መልካም የሆነውን ነገር ብቻ አይናገርም፣ ባለመታዘዝ ምክንያት የሚከተለውንም ውጤት በመግለጽ ያስጠነቅቃል (1ሳሙ 15:29፣ ዘጸ

4:6፣ ዘኅ 23:19፣ ዘዳ 32:4፣ መዝ 96:5፣ መዝ 97:7፣ ኤር 10:5,10፣ ዮሐ 17:3፣ ሮሜ 3:4፣ 1ተሰ 1:9፣ ቲቶ 1:2፣ ዕብ 6:18)።

እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ በመሆኑ ቃሉ ሁሉ እውነት ነው። ጌታ ኢየሱስ ወደ አብ ሲጸልይ በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ 17:17) ብሏል። ሊዋሽ የማይችልና (ዕብ 6:18) «የማይዋሽ እግዚአብሔር» (ቲቶ 1:2) የተናገረው ቃል ነው። ስለሆነም ሌላው ነገር ሁሉ ትክክለኛነቱ የሚለካው እውነት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ነው። በቃሉ ሲለካ ቀልሎ የተገኘ ወይም ሚዛን ያልደፋ ነገር ሁሉ ውሸት ነው። መዋሸት ደግሞ የሰይጣን ዓይነተኛ ባሕርይ ነው። ሰይጣን «ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነው» (ዮሐ 8:44)።

ውሸት የአሮጌው ሰው ባሕርይ በመሆኑ ክርስቲያን አዲሱን ሰው የለበሰ ስለሆነ ውሸትን ማስወገድ ይገባዋል (ምሳ 4:24፣ ኤፌ 4:25፣ ቆላ 3:9-10)። ይህን የሚያደርግ ሰው እግዚአብሔርን በማወቅና በመምሰል ያድጋል።

### ሐ.2 <u>ታማኝነት</u>

የእግዚአብሔር እውነተኛነት የሚገለጸው በታማኝነቱ ነው። እግዚአብሔር የተናገረውን የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ወራትን በማፈራረቅ የሰውን ዘር ለመመገብ የገባውን ቃል (ዘፍ 8:22) እስካሁን ጠብቋል። በየዓመቱ የሰው ልጅ የሚሰበስበው አዝመራና የሚበላው ምግብ ለእግዚአብሔር ታማኝነት ምስክር ነው (ዘዳ 7:9፣ ዘኅ 23:19፣ 1ነገ 8:56፣ መዝ 36:5፣ መዝ 89:8፣ ሰቆ 3:23፣ 1ቆሮ 1:9፣ 1ተሰ 5:24፣ 2ጢሞ 2:13፣ ዕብ 10:23)።

እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ይጠብቃል። ለአዳም (ዘፍ.3:15፣ ገላ.4:4)፣ ለአብርሃም (ዘፍ.15:13፣ ዘዳ.2:24)፣ ለሙሴ (ዘጸ 3:12.21፣ 4:12፣ 33:14)፣ ለኢያሱ (ኢያ 1:1-5፣ 23:14)፣ ለዳዊት (1ነገ 8:56፣ 2ሳሙ 7:8-16) የተናገረውን በጊዜው ፈጽሟል። እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጐ የሚያፍር የለም (1ጴጥ 2:6)። እግዚአብሔር የተናገረውን የሚያደርግ ታማኝ አምላክ በመሆኑ እኛም የባሕርይው ተካፋዮች ቃላችንን ልንጠብቅ ይገባናል (መዝ 61:5፣ 66:13፣ ኢያ 9:16-21)።



## 4.2.2 <u>የሞራል ባሕርያት</u>

### ሀ. <u>የእግዚአብሔር መልካምነት / ቸርነት</u>

እግዚአብሔር በእርሱነቱ መልካም ነው። እርሱ ከሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት መልካም ነው። እርሱ ብቻ መልካም ነው (መዝ 36:9፣ መዝ 145:9፣ 15-16፣ ማር 10:18።)

እግዚአብሔር ቸርነቱን በብዙ መንገዶች ገልጿል። የእግዚአብሔር ቸርነት ሰውን ውብ አድርጐ በመፍጠሩ (መዝ 139:14)፣ ለፍጥረትም ሁሉ ምግባቸውን በመስጠቱ ይታያል (መዝ 145:15-16፣ 136:25፣ ማቴ 6:26-28)። እግዚአብሔር ለኃጢአተኛ ምሕረትን በማድረግ፣ ለኃጥአንና ጻድቃን ዝናብንና (ማቴ 5:45) የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በመስጠት (ማቴ 6:30፣ ሐዋ 14:17) ቸር አምላክነቱን ይገልጻል።

እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው፣ «በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው» (ያዕ 1:17)። የእርሱም ፈቃድ ደስ የሚያሰኝ ነው (ሮሜ 12:2)። «እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም» (መዝ 84:11፣ ማቴ 7:11፣ ሮሜ 8:32)። እግዚአብሔር ልጆቹን የሚቀጣቸው እንኳ ለመልካም ነው (ዕብ 12:10)።

የእግዚአብሔር መልካምነት በፍቅሩ፣ በጸጋው፣ በምሕረቱና በትዕግሥቱ ተገልጿል (ዘጸ 34:6፣ መዝ 103:8፣ ዮና 4:2)።

### ሀ.1 <u>ፍቅር</u>

ፍቅርና መከባበር በሥላሴ አካላት መካከል ያለ የዘላለም ግንኙነትና ኅብረት መግለጫ ነው። ጌታ ኢየሱስ «አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ፣ አብም እንዳዘዘኝ፣ እንዲሁ አደርጋለሁ» (ዮሐ 14:31)፣ እንዲሁም «አባት ሆይ፣ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድከኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ» ብሏል (ዮሐ 17:24)። ደግሞም «አባት ልጁን ይወድዳል» (ዮሐ 3:35)።

ፍቅር ማለት ለሌላው መልካም የሆነውን መመኘት፣ ማድረግም ማለት ሲሆን እግዚአብሔር ለሰው እራሱን መግለጹና ከሰው ጋር ግንኙነት ማድረጉ ፍቅሩን ያሳያል። እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን አንድያ ልጁን

በመላክ ፍቅሩን ገልጿል (ዮሐ 3:16፣ ገላ2:20፣ ሮሜ 5:8፣ 1ዮሐ 3:1፣ 1ዮሐ 4:8-9፣ 16)::

እንዲሁም እግዚአብሔር ፍቅሩን የሚገልጸው በቸርነቱ (ማቴ 5:45፣ ሐዋ 14:17) በመቅጣቱ[28] (ምሳ 3:12፣ ዕብ 12:6-11፣ ራእ 3:19)፤ በምሕረቱ (ዘዳ 4:31፣ መዝ 145:8-9፣ 2ጴጥ 3:9)፣ ወዘተ... ነው::

የክርስቲያኖች እርስ በርስ መዋደድ ምክንያቱ ወይም ምንጩ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን መውደዱ ነው (ሮሜ 5:8፣ 1ዮሐ 4:11-12፣ 19):: እኛም ከእርሱ በመማር ራስን ለሌላው አሳልፎ የመስጠት ፍቅር እንዲኖረን ጌታ አዘናል (ዮሐ 13:34፣ ፊሊ. 2:4):: እግዚአብሔር ፍቅር ይሰጣል (ሮሜ 5:5)፣ ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ 5:22)::

### ሀ.2 ጸጋ

ምንም ለማይገባው ሰው እንዲሁ (ያለ ምንም ዋጋ) የሚደረግለት መልካም ነገር ጸጋ ይባላል:: እኛ ኃጢአተኞች ሳለን እግዚአብሔር እንዲሁ በጸጋው ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከልን:: ጸጋ ለመልካም ምግባር የሚከፈል ተመጣጣኝ ዋጋ ሳይሆን በኃጢአቱ ንስሐ ለሚገባ ሰው እንዲሁ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው (ሮሜ 3:24፣ 11:6፣ 2ቆሮ 8:9፣ ኤፌ 2:8፣ ቲቶ 2:11፣ 3:4-7)::

እግዚአብሔር «የጸጋ ሁሉ አምላክ» ነው (1ጴጥ 5:10):: ደህንነት የሚገኘው በሥራ ሳይሆን በጸጋ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰዎች ሁሉ እንዲህ ይላል:- «ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል፣ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ:: እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሰሪያ አድርጎ አቆመው፤» (ሮሜ 3:23-25):: ደህንነት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በእግዚአብሔር ጸጋ እንዲሁ የማይገኝ ቢሆን ኖሮ «ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል» (ሮሜ 11:6):: ስለሆነም ጸጋ የእግዚአብሔርን መልካምነት ያሳያል::

---

28እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ በመጨረሻ ሁሉንም ሰው ያድናል የሚል (Universalism) የተሳሳተ አስተሳሰብ ያላቸው አሉ:: ነገር ግን የእግዚአብሔር አንዱ ባሕርይ ከሌላው ተለይቶ (በልጦ ወይም አንሶ) አይታይም፣ ወይም አይቃረንምና እርሱ ፍቅር መሆኑ ከቅድስናው፣ ከጽድቁና ከፈራጅነቱ ጋር አብሮ መታየት አለበት::



### ሀ.3 ምሕረት

ምሕረት ለበደሉና ለተጣሉት (ለውድቀት) የእግዚአብሔር መልካምነት ነው:: ምሕረት የሚያስፈልገው የበደለና ኃጢአትን ያደረገ ነው:: ሰው ሁሉ ደግሞ ኃጢአተኛ ነው:: እግዚአብሔር ግን ምሕረቱ የበዛ ርኅሩኅ አምላክ ነው:: የእግዚአብሔርን ማንነት የተረዳው ዳዊት ጋድን:- «እጅግ ተጨንቄአለሁ፣ ምሕረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሔር እጅ እንውደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ አለው» (2ሳሙ 24:14):: የእግዚአብሔር ምሕረቱ ለዘላለም ነው (መዝ 136:1)፣ ማለዳ ማለዳም አዲስ ነው (ሰቆ 3:22፣ ዘዳ 5:10፣ 2ነገ 3:6፣ መዝ 5:7-10፣ ነህ 9:31፣ 2ቆሮ 1:3)፣ የታመሙትን በመፈወስም ይገለጻል (ማቴ 9:25):: እኛም ለበደሉን ምሕረትን በማድረግ እግዚአብሔርን እንድንመስል ቃሉ ያዛል (ማቴ 5:7)::

### ሀ.4 ትዕግሥት

እግዚአብሔር «የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ» ነው (ሮሜ 15:5):: ትዕግሥት እግዚአብሔር አምላክ ለኃጢአተኞችና ለአመጸኞች ቁጣውን በማዘግየትና ለንስሐ ጊዜ በመስጠት የሚያሳየው መልካምነቱ ነው:: እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ፣ የትዕግሥት ባለጠጋ ነው (ዘጸ 4:6፣ ዮና 4:2፣ ሮሜ 2:4):: እኛም የዚህ ባሕሪይ ተካፋዮች እንሆናለን::

«... ትዕግሥትን ልበሱ፣ እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ» ተብሎ እንደተጻፈ (ቆላ 3:13) አንዳችን ለሌላው በሚኖረን ትዕግሥት የእግዚአብሔርን መልካምነት እንገልጻለን (ዘኁ 14:18፣ ናሆ 1:3፣ ሮሜ 9:22፣ 1ጴጥ 3:20፣ 2ጴጥ 3:9፣ 15)::

### ለ. ቅድስና

መቀደስ ማለት ከክፉ መለየትና መልካም /ጽድቅ የሆነውን ማድረግ ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ቅድስና የእርሱን መለየትና ንጽሕናውን ያመለክታል:: እግዚአብሔር ከኃጢአትና ክፉ ከሆነ ነገር ሁሉ ፈጽሞ የተለየ ነው:: እግዚአብሔር በቅድስናው የሚመስለው የለም:: እርሱ ቅዱስ ነው (መዝ 103:1፣ ራእ 15:4):: በዙፋኑ ፊት ሱራፌል ሁልጊዜ «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ» ይላሉ (ኢሳ 6:3)::

እግዚአብሔር በሁሉም ባሕርያቱ ፍጹም በመሆኑ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል:: ስሙም ቅዱስ ነው:: የእርሱም ቃል ቅዱስ ነው፣ (ዮሐ 17:17):: የእግዚአብሔር ዙፋን ቅዱስ ነው (መዝ 47:8)፣ መቅደሱ ቅዱስ ነው፣ (2ጢሞ 2:20)፣ ለእርሱ የተለዩት ዕቃዎች ሁሉ የተቀደሱ ናቸው (ዘጸ 30:22-29):: ለቅድስናውም የሚዘምሩ መዘምራንን መርጧል (2ዜና 20:21፣ ዘሌ.27:28፣ 1ሳሙ 2:2፣ ዘካ 14:20-21፣ መዝ 99:9፣ ዘጸ 15:11፣ መዝ 105:42፣ ኢሳ 57:15፣ 6:3-5)::

ሙሴ (ዘጸ 33:18-23)፣ ኢሳይያስ (ኢሳ 1:1-50)፣ ዮሐንስ (ራእ 4:8-11) የእግዚአብሔርን ቅድስና በራእይ ተረድተዋል:: የእግዚአብሔር ቅድስና በሕጉ ተገልጿል:: የእርሱ ሕግ ቅዱስ ነው (ሮሜ 7:12):: የእግዚአብሔር ቅድስና በሥራው፣ (መዝ 145:17):: በደለኞችን በመቅጣት አሳይቶአል:: ናዳብና አብዩድ (ዘሌ 10:1-3) ቆሬ፣ ዳታንና አቤሮን (ዘኁ 16:4-12፣ 31-33)፣ ዖዝያ (2ዜና 26:16-21) ተቀጥተዋል::

የእግዚአብሔር ቅድስና ኃጢአትን በመስቀል ላይ በመቅጣት ተገልጿል:: ኃጢአተኛ ሰው የኃጢአት ይቅርታ የሚያገኘው የኃጢአትን ዋጋ በከፈለለት ቅዱስ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው:: ያለ ደም መፍሰስ ይቅርታ የለም (ዕብ 9:22):: እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ሰው ሁሉ ሊፈራውና ሊያከብረው ይገባል (መዝ 89:7፣ 99):: ሰው በቅድስና እግዚአብሔርን ሲመስል (1ጴጥ 1:15-16) እግዚአብሔርን ያከብራል:: ክርስቲያን ሁሉ እግዚአብሔርን በመምሰል በቅድስና እንዲኖር ይጠበቅበታል (ዘሌ 11:44-45፣ 19:2፣ 20:7፣ ማቴ 5:48፣ 2ቆሮ 6:14፣ 1ጴጥ 1:16፣ ሉቃ 5:8፣ ኤፌ 5:27፣ ዕብ 12:10)::

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ሲጠራ «የተቀደሰ ሕዝብ» እንዲሆኑለት ነው (ዘጸ 19:6):: በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲስ ኪዳንም እያንዳንዱ ክርስቲያን የተጠራው «በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን» ነው (ኤፌ 4:21):: እንዲህ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን በቅድስና ታድጋለች:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ቤተ ክርስቲያንን ... አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለራሱ ሊያቀርብ ፈለገ» (ኤፌ 5:25-27)::



ሐ. <u>ጽድቅ</u>

ጽድቅ ማለት ትክክል፣ ያልተዛነፈ፣ ስህተት የሌለበት ሃሳብ ወይም ተግባር ማለት ነው:: እግዚአብሔር በሃሳቡ፣ በመንገዱ በሥራው ሁሉ ጻድቅ ነው:: የእግዚአብሔር ጽድቅ የእርሱን ጻድቅ ፈራጅነት ያሳያል:: የእግዚአብሔር ጽድቅ በሕጉ፣ በቃሉ ተገልጿል (መዝ 19:7-9):: እርሱ የሚያዝዘው ሁሉ ትክክል ነው:: እርሱም የሚሠራው ሁሉ እራሱ በሰጠው ሕግ መሠረት ነው:: እርሱ ለኃጢአት ተገቢውን ዋጋ ወይም ቅጣት ባይሰጥ ኖሮ ጻድቅ ባልሆነም ነበር (ዘፍ 18:25፣ 1ነገ 8:32፣ ዳን 9:7፣ ዕዝ 19:15፣ መዝ 116:5፣ 119:137፣ ሶፎ 3:5፣ ኤር 9:24፣ 2ጢሞ 4:8)::

እግዚአብሔር በኃጢአት የሚቆጣና ፈራጅም ነው:: እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል (መዝ 11:5፣ ዕብ 1:13):: እግዚአብሔር ፈጽሞ ስህተት የማይሠራ አምላክ ነው:: ሁሉን በማወቁ የመምረጥ ችግር የለበትም፣ ቅዱስ በመሆኑ ኃጢአትን አያደርግም፣ እርሱ ጻድቅ ፈራጅ በመሆኑ የተሳሳተ ፍርድ የለውም:: አብርሃም «የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» (ዘፍ 18:25) እንዳለ እግዚአብሔር በቅን ይፈርዳል:: እግዚአብሔር መንግሥቱን የሚያስተዳድረውና የሚፈርደው በቃሉ መሠረት ነው::

እግዚአብሔር ለዘላለም ጻድቅ በመሆኑ የነገሮች ሁሉ ትክክለኛነት መለኪያ እሱ ራሱ ነው:: እግዚአብሔር ስለራሱ ሲናገር «እኔ እግዚአብሔር ጽድቅን እናገራለሁ ቅንንም አወራለሁ» (ኢሳ 45:19) ይላል:: እንዲሁም ሙሴ «እርሱ አምላክ ነው፣ ሥራውም ፍጹም ነው፤ መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤ የታመነ አምላክ፣ ክፋትም የሌለበት፣ እርሱ እውነተኛና ቅን ነው» ብሏል (ዘዳ 32:4)::

እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ ስለ ሥራው የሚጠይቀው ወይም የሚከስሰው የለም:: እግዚአብሔር ኢዮብን «ጻድቅ ትሆን ዘንድ በእኔ ትፈርዳለህን?» ብሎ ሲጠይቀው የኢዮብ መልስ «ራሴን እንቃለሁ» የሚል ነበር (ኢዮ40:8፣ 42:6)::

እግዚአብሔር «የሁሉም ዳኛ» ነው (ዕብ 12:33):: «ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው» (መዝ 97:2): እግዚአብሔር ቅን ፈራጅነቱን ከሚገልጽባቸው መንገዶች መካከል ጥቂቶቹ:-

- ጻድቃንን በመጠበቅ (ዘፍ 18:24-26፣ መዝ 6:11-13፣ 2ጴጥ 2:7-8፣ 1ሳሙ 17:37፣ ሐዋ 27:21-25) ብድራታቸውን በመክፈል፣ አክሊልን በመስጠት፤ (መዝ 7:9-11፣ ማቴ 5:6፣

13:45፣ ዮሐ 14:2-3፣ ሮሜ 14:10፣ 1ቆሮ 3:12-15፣ 2ቆሮ 5:10፣ 2ጢሞ 4:8)፣

- ኃጥአንን በመቅጣት (መዝ 7:11-17፣ 11:6፣ ማቴ 25:46፣ ዘጸ 9:27)፣ ትዕቢተኞችን በማዋረድ (ዳን 4:28-33፣ ሐዋ 12:20-23)፣
- አማልክትን በመቅጣት (ዘጸ 12:12)፣

እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነና እንደተናገረው እንዲሁ የሚያደርግ በመሆኑ ልንታመንበት ይገባል:: ከእርሱ ጋር ኅብረትና አንድነት ብንጀምር ቃሉን ይጠብቃል፣ አይከዳም::

### 4.2.3 የሁሉ የበላይ/ ገዥ፣ ሁሉን ቻይ

እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ፍጹም ገዥ / ንጉሥ ነው:: እርሱ እንደወደደ ለመግዛት ሥልጣን አለው:: እርሱ ብቻ ንጉሥ ነው:: በጽድቅ ይገዛል:: «ሁሉን ቻይ» የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 56 ጊዜ ያህል የሚገኝ ሲሆን በሁሉም ቦታ የዋለው ለእግዚአብሔር ነው:: ሁሉ ነገር በፊቱ ኢምንት ነው (ዘፍ 14:19፣ ዘጸ 6:3፣ ዘዳ 18:11፣ ዘፍ 17:1፣ ነህ 9:6፣ ማቴ 19:26፣ ሐዋ 17:24-26፣ 2ቆሮ 6:18፣ ራእ 19:6)::

እግዚአብሔር ሀሳቡንና ፈቃዱን ለመፈጸም ሙሉ ሥልጣን አለው:: ኤርምያስ ሲጸልይ «አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ: እነሆ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፣ ከአንተም የሚያቅት ነገር የለም... ስምህ ታላቅና ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው:: በምክር ታላቅ በሥራም ብርቱ ነህ» እንዳለ (ኤር 32:17-19) እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ አምላክ ነው (ማቴ 19:26፣ 2ቆሮ 6:18፣ ኤፌ 3:20):: እግዚአብሔር ካየነውና ከሰማነው ነገር ሁሉ በላይ ሊያደርግ ይቻለዋል:: አንድን ሕዝብ አጥፍቶ ሌላ ማስነሳት ይቻለዋል (ዘጸ 32:10)::

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ በመሆኑ ለፈቃዱና ለክብሩ ሲያስፈልግ የተፈጥሮንም ሕግጋት ይለውጣል፣ ይሽራል:: እስራኤላውያን ባሕር ተከፍሎ በደረቅ ምድር እንዲሻገሩ (ዘጸ 14:21-22)፣ ኢያሱ ድል እስኪያደርግ ድረስ ፀሐይ እንድትቆም (ኢያ 10:12-13)፣ አብርሃምና ሣራ በምውት ሥጋቸው ይስሐቅን እንዲወልዱ (ሮሜ 4:16-21)፣ መሬት ተከፍታ አመጸኞችን እንድትውጥ (ዘኁ 16)፣ ቁራ ኤልያስን እንዲመግብ (1ነገ 17)፣ ብረት በውኃ ላይ እንዲንሳፈፍ



(2ነገ.6:5)፣ ወዘተ በማድረግ እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ አሳይቶአል::

እግዚአብሔር በባሕር ማዕበል ላይ ይረግጣል (ኢዮ 9:8)፣ በሰማይ ክበብ ላይ ይራመዳል (ኢዩ 22:14)፣ በነፋስ ክንፍ ይሄዳል (መዝ 104:3):: እግዚአብሔር ምንም ነገር ለማድረግ እውቀቱ፣ ፈቃዱ፣ ኃይሉና ሥልጣኑ አለው:: እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ሁሉ የወደደውን ያደርጋል (መዝ 135:6):: የንጉሥ ልብ በእግዚአብሔር እጅ ነው (ምሳ 20:1):: እግዚአብሔር ነጻ ነው:: ማንም ስለ ምንም ነገር አያስገድደውም፣ እንደወደደ ያደርጋል፣ የሚከለክለውም የለም (ኤፌ 1:5፣9፣ ፊሊ 2:13)::

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ቢሆንም ከባሕርዩ ውጪ የሆነ ወይም የሚቃረን ነገር አያደርግም:: ለምሳሌ እግዚአብሔር «ራሱን ሊክድ አይችልም» (2ጢሞ 2:13)፣ አይዋሽም (ቲቶ 1:2፣ ዕብ 6:18)፣ «በክፉ አይፈተንም» (ያዕ 1:13)::

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነቱን፣ ሁሉን ገዥነቱን ከገለጸባቸው መንገዶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-

- በመፍጠር ተግባሩ:- መዝ 33:4-9፣ ኢሳ 40:12-17
- በተፈጥሮ ሥርዓት ላይ:- መዝ 107:25-29፣ ማቴ 8:24-27
- በሰው ላይ:- ዘጸ 5:2፣ 12:30-31፣ ዳን 4:30-37
- በሰይጣን ላይ:- ኢዮ 1:10-12፣ 2:6፣ ሉቃ31-32:: (እግዚአብሔር የቀጣቸው መላእክት እንደሌሉች የብርሃን መላእክት የነበሩ ናቸው (2ጴጥ 2:5)::

እግዚአብሔር እጅግ ኃያል አምላክ ነው:: ነቢዩ ናሆም እንዳለው:-

> «እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ፣ ኃይሉም ታላቅ ነው፣ ...
> እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው፣
> ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው:: ባሕሩንም ይገሥጻታል፣ ያደርቃትማል፣
> ወንዞችንም ሁሉ ያደርቃል ... በቁጣው ፊት የሚቆም ማን ነው? ...
> እግዚአብሔር መልካም ነው፣ በመከራም ቀን መሸሸጊያ ነው፤ በእርሱ
> የሚታመኑትንም ያውቃል» (ናሆ 1:3-7)::

የእግዚአብሔር ባሕርያት በዚህ ምዕራፍ ከተገለጹት በላይ ናቸው፣ ከሰው መረዳት ያለፈ ነው:: ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ የእግዚአብሔርን ባሕርያት፣ ባሕርያቱ ምን ማለት እንደሆኑና እያንዳንዱ ባሕርይ ለአማኙ የሚሰጠውን ትርጉም ጠቀለል ባለ መልኩ ለማመልከት ተሞክሯል::

## ሠንጠረዥ 1
## የእግዚአብሔር ባሕርያት

| ባሕርይ | ባሕርይው እንዴት እንደተገለጸ/ምን ማለት እንደሆነ | ለአማኙ የሚሰጠው ትርጉም |
| --- | --- | --- |
| ሁሉን ቻይ ነው | . አንድን ነገር ከምንም በቃሉ ፈጥሯል ዘፍ.1፣ መዝ.33:6-9፣ ኢሳ .44:24::<br>. የፈጠረውን ያቆማል፣ ይንከባከባል፣ ዕብ.1:3<br>. ሙታንን ያስነሣል ዮሐ.5:28-29፣ ሮሜ 4:17<br>. የሚሣነው ነገር የለም:: ሥልጣን አለው:: ዘፍ.18:14፣ ሉቃ.1:17፣ መዝ.14:3<br>. በዲያቢሎስና በሠራዊቱ ላይ ሥልጣን አለው:: | . በኃይሉ ደህንነታችንን ይጠብቃል 1ጴጥ.3:15<br>. በኃይሉ ችሎት ያበረታናል ፊሊ.4:13፣ ኤፌ.6:10፣ ኢሳ.40:29<br>. ከምንለምነውና ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ያደርጋል ኤፌ.3:10 |
| ሁሉም ቦታ አለ | . በሰማይ ኤር. 23:23፣ ኢሳ.66:1፣ ሐዋ.7:48-49<br>. በምድር መዝ.139:7-12<br>. በሲኦል መዝ.139:8<br>. በአማኞች 1ቆሮ.3:16 | . ከእያንዳንዳችን ጋር ነው ሐዋ.17:27<br>. መደበቂያ የለንም መዝ.139:7-12<br>. ስንጠራው ይሰማናል:: ኤር.23:23 |
| ሁሉን ያውቃል | . አይማርም፣ አይመራመርም ኢሳ.40:13<br>. በሰው ልብ ያለውን ያውቃል ሕዝ.11:5፣ 1ቆሮ.2:3<br>. የከዋክብትን ቁጥር ያውቃል / በስም ይጠራቸዋል:: መዝ.147:4<br>. ሁሉን በጥበብ አድርጓል:: ሮሜ 16:27፣ መዝ.147:5፣ መዝ.104:24<br>. ሁሉን ለራስ ክብር እንዲሆን አድርጓል:: ሮሜ 1:16 | . እግዚአብሔር እኔን ያውቀኛል<br>. የሚያስፈልገኝን ሁሉ ያውቃል ዮሐ.2:25፣ ማቴ.6:25<br>. ጥበብን ይሰጣል:: ያዕ.1:5፣ 1ነገ.3:9 |
| አይለወጥም | . እግዚአብሔር ያው እግዚአብሔር ነው:: መዝ.102:25-27<br>. ሰማይና ምድር ይጠፋሉ:: እርሱ ግን ያው እርሱ ነው:: መዝ.102:25<br>. መለዋወጥ በእርሱ ዘንድ የለም:: ያዕ.1:17፣ ሚል.3:6<br>. ፈቃዱ አይለወጥም:: ዕብ.6:17 | . ተስፋችን የተደላደለ፣ የተረጋገጠ ነው:: 2ጢሞ.2:13<br>. የጀመረውን መልካም ሥራ ይፈጽማል ፊሊ.1:6<br>. የሰጠውን አደራ ይጠብቃል 2ጢሞ.1:12 |
| ዘላለማዊ ነው | . መጀመሪያና መጨረሻ የለውም:: ከጊዜ ውጭ ነው::<br>. ራሱ በራሱ ያለና የሚኖር ነው:: አይሞትም::1ጢሞ.6:16 2ጴጥ.7:8<br>. ዓለምን /ጊዜን የፈጠረ፣ ዓለምን የሚያጠፋ ነው::<br>. የዘላለም ገዥ፣ የዘመናት ንጉሥ ነው:: 1ጢሞ.1:17፣ ኤር.10:10-12፣ ኢሳ.7:15 | . ስናምን የዘላለምን ሕይወት ጀምረናል:: ቆላ.1:27<br>ዮሐ.1:13 3:3 ሮሜ 6:25፣ 1ዮሐ.5:12<br>. ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም እንኖራለን ዮሐ.10:10 |
| ፍቅር ነው | . ዓለሙን / ሰውን ወድዷል ዮሐ.3:16፣ ሮሜ 5:8-10፣ ኤር.31:3፣ 1ዮሐ.13:1<br>. እግዚአብሔር እንዲሁ በጸጋው ወዶናል ኤፌ.1:6-7፣ 2:8፣ ቲቶ 2:11፣ 3:4-7<br>. በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ስለወደደን ሕይወት ሰጠን ኤፌ.2:4፣ 1ጴጥ.1:3፣ ማቴ.12:7፣ ሆሴ.6:6<br>. ለንስሐ ጊዜ በመስጠት፣ በመታገሡ ፍቅሩን ገልጾአል 2ጴጥ.3:9፣ ሮሜ 2:4 | . ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በመታዘዝ እንገልጻለን፣ ዮሐ.14:15፣ 1ዮሐ.3:22-23<br>. ወንድማችንን እንድንወድ ታዘናል፣ ማቴ. 5:43-48፣ ቆላ.3:14<br>. እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ጸጋ ይሰጣል ዕብ.4:16<br>. ምሕረት እንድናደርግ ትዕግሥተኛ እንድንሆን ታዘናል ማቴ.5:7፣ሉቃ.6:36፣ ዕብ.5:11፣ ማቴ.5:45 |
| ቅዱስ ነው | . የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ ነው፣ ሕዝ.36:20፣ ኢሳ.57:15 ሉቃ.1:50<br>. ከአማልክት ሁሉ በቅድስናው የከበረ ነው፣ ዘጸ.15:11<br>. ከፍጥረት ሁሉ እርሱን የሚመስል የለም፣ ኢሳ.40:25<br>. እግዚአብሔር ብቻ ቅዱስ ነው፣ ዕብ.1:12-13 | . በክርስቶስ የሆነ ቅዱስ ነው፣ 1ቆሮ.1:2፣ 10<br>. በእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ ቅዱስ መሆን አለበት ትዕዛዝ ነው፣ ኤፌ.4:24፣ 1ጴጥ.1:15-16<br>. በመከራ የቅድስናው ተካፋዩች እንሆናለን ዕብ.12:10 |
| ጻድቅ ነው | . ኃጢአትን ይጠላል፣<br>. ኃጢአትን ይቀጣል፣<br>. ፍርዱ በቅንነት፣ በጽድቅ ነው:: መዝ.19:8፣ 1ጴጥ.1:17፣ ሮሜ 2:11፣ ሐዋ. 10:34<br>. እግዚአብሔር ብቻ ጻድቅ ነው:: ዕብ.9:15፣ ሮሜ 3:11-18 | . ኃጢአትን መናዘዝና መተው አለብን<br>. የክርስቶስ ጽድቅ ጽድቃችን ነው:: |



# ምዕራፍ 5. ሥላሴ

## የእግዚአብሔር በአንድነት ሦስትነት ፣ በሦስትነት አንድነት

እግዚአብሔር በሦስት አካላት ተገልጾ የሚኖር አንድ አምላክ መሆኑን በግልጽ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል:: ይህ በክርስትና እምነት መሠረታዊ ትምህርት ነው:: ሌላው የክርስትና ትምህርት ሁሉ በዚህ እውነት ላይ የተመሠረተ ነው:: በታሪክም ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ይህንን እውነት አምናና ተቀብላ ስታስተምረው ቆይታለች::

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ አምላክ መሆኑን፣ በዚህ አንድ አምላክ ሦስት አካላት (ሥላሴ)[29] እንዳሉ፣ ሦስት አማልክት ሳይሆኑ አንድ አምላክ ብቻ እንደሆነ፣ እርስ በርሳቸው በዘላለማዊነት፣ በባሕርይ፣ በሥልጣን፣ የማይበላለጡና እኩል መሆናቸውን ያረጋግጣል::

ስለ እግዚአብሔር ማንነት ሲገለጽ «አካል» (Person) የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ዓይነት ሥጋ መልበስን ወይንም የሰውን ዓይነት ቁመና መያዝን ሳይሆን የአካል መለያ ባሕርያት ማለትም እውቀት፣ ፈቃድ፣ ስሜት፣ (intellect, will, emotion) እንዳሉት ለማሳየት ነው:: ይሁን እንጂ አካል የሚለው ቃል የሥላሴን ሕልውና በበቂ ሁኔታ ሊገልጽ አይችልም፤ ምክንያቱም አካል (Person) የሚለው ቃል ለሰው ሲውል የተለያዩና አንድ ያልሆኑ ሰዎችን ስለሚያመለክት ነው:: በእግዚአብሔር ዘንድ ግን በሥላሴነት አንድነት ደግሞ አለ:: ስለ ሥላሴ ትምህርት በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን::

---

29 የሥላሴን ሦስትነት ለመግለጽ አካል የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በ451 ዓ.ም ኬልቄዶን ከተደረገው ስብሰባ በኋላ ነው:: ስለ ቃሉ አጠቃቀም ግሩደም ሲገልጽ " Because of the existence of three persons in one God is something beyond our understanding, Christian theology has come to use the word Person to speak of the differences in relationship, not because we fully understand what is meant by the word Person when referring to the Trinity, but rather so that we might say something instead of saying nothing at all". Ibid. P.255.

## 5.1 የሥላሴ ትምህርት በታሪክ ውስጥ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸውን የሥላሴ ትምህርት መልክ ባለው ሁኔታ ያቀነባበረው ጠርጠሊያኖስ[30] የተባለው ሰው ነው:: ሥላሴ (Trinity) የሚለውንም ቃል በመጀመሪያ በሦስት አካል የሚኖረውን አንድ አምላክ ለመግለጽ የተጠቀመው እርሱ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ሰው በአብና በወልድ መካከል ስላለው ግንኙነት/ ዝምድና ሲናገር «ወልድ ከአብ ያንሳል» በማለት የበታችነት ስህተት (Error of Subordination) አስተምሯል::

ኦርየገን[31] የተባለው ሰው ደግሞ ከጠርጤሊያኖስ ትምህርት በመነሳትና ከእርሱ ጋር በተመሳሰለ ሁኔታ «ወልድ ከአብ ያንሳል፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከወልድ ያንሳል» ብሎ ስህተት አስተምሮ ነበር:: በ270 ዓ.ም በሊቢያ የተወለደው አሪዮስ[32] ከዚህ በመነሳት «ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ፍጡር ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በወልድ የተፈጠረ ነው» ሲል የሥላሴን እምነት የሚክድ የስህተት ትምህርት አስፋፋ:: በአሪዮስ ትምህርት መሠረት አምላክ የሆነው አብ ብቻ ነው ማለት ነው::

---

[30] Tertullian was the first theologian... to use the word Trinity, and the one who coined the well-known Latin formulation tres personae, una substantia ("three persons, one substance"). Stanley J. Grenz 1994' Theology for the community of God. Carlisle: The paternoster press, pp.79-80.

[31] Grudem explains that: "Subordination held that the Son was eternal (not created) and divine but still not equal to the Father in being or attributes; the Son was inferior or "Subordinate in being to God the Father". The early church father Origen (185-254 A.D) advocated a form of subordination by holding that the Son was inferior to the Father in being, and that the Son eternally derives his being from the Father". Wayne Grudem. Ibid. p.245

[32] "Arius who was a bishop of Alexandria, "taught that God the Son was at one point created by God the Father, and that before that time the Son did not exist nor did the Holy Spirit, but the Father only. Thus though the Son is a heavenly being who existed before the rest of creation and who is far greater than all the rest of creation, he is still not equal to the Father in all his attributes". Ibid..p.245



እንደነዚህ ዓይነት አስተሳሰቦች በታሪክ ውስጥ ብቅ በማለታቸው 318 የሚሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በ325 ዓ.ም. በኒቂያ (በትንሿ የእስያ ከተማ) ባደረጉት ስብሰባ ወልድ አምላክ እንደሆነ፣ እንደ አብ ዘላለማዊ መሆኑንና ከአብ ጋር እኩል መለኮታዊ ባሕሪ እንዳለው አረጋገጡ::[33] በዚህም የአሪዮስን ትምህርት አወገዙ:: ከ297-373 ዓ.ም የኖረው አትናቴዎስ[34] የሥላሴን እምነት አጥርቶ በመግለጽና የአሪዮስን ትምህርት በመቃወም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የታወቀ ሰው ሲሆን በስሙም የተሰየመ የክርስትና የእምነት መግለጫ አለ::[35]

---

[33] ስለ ጌታ ኢየሱስ ማንነት የኒቂያ ጉባዔ የሃይማኖት (Nicene Creed) መግለጫ የሚከተለው ነው::

«እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን፣ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፣ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፣ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ የሆነ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ ሁሉ በእርሱ በሆነ፣ ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ ደኅንነታችንም ከሰማይ በወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ሥጋ ነሥቶ ሰው በሆነ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ በተሰቀለ፣ መከራ በተቀበለ፣ በሞተ፣ በተቀበረም፣ በቅዱሳት መጽሐፍትም እንደተጻፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፣ ወደ ሰማይም በወጣ፣ በአብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር በሚመጣ፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ በሌለው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ»:: የመካነ ኢየሱስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ስብሐት ለአምላክ፣ 1975 ዓ.ም. የተባበሩት ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ::

[34] Athanasius "was only twenty-nine years when he came to the council of Nicea in AD 325, became Bishop of Alexandria in 328... by his untiring efforts " almost single handedly Athanasius saved the church from pagan intellectualism." Grudem. Ibid.

"Athanasius argued persuasively that the deity of the Son is necessitated by soteriology. If Jesus is not fully God we do not truely receive salvation, for in salvation we participate in the divine nature:.. [Likewise on the deity of the Spirit] Athansius showed that the deity of the Spirit is necesitated by soteriology. If the spirit who enters our hearts as believers is not the actual spirit of God, then we have no true community with God: "If we are made sharers of the divine nature through our partaking of the spirit it would be only a madman who would say that the spirit is of created nature and not of the nature of God." Stanley J. Grenz, Ibid. pp 76-77

[35] The Athanasian Creed on the Doctrine of the Trinity goes as follows:-
...We worship one God in Trinity, the Trinity in Unity; neither confounding the Persons, nor dividing the Substance [Essence]. For there is one Person of the Father, another of the Son, and another of the Holy Ghost.

የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት፣ በአንድነት-ሦስትነት (ሥላሴ) እምነት በመቃወም በተለይም ደግሞ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት በመካድ በታሪክ ውስጥ ብዙ የኑፋቄ ትምህርቶች ተነስተዋል። ከእነዚህ የስህተት ትምህርቶች መካከል ዋና ናቸው ተብለው የሚታወቁትንና በትምህርቶቹ ላይ የቀደሙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔዎች ያጸኗቸው እምነቶች በሚቀጥሉት ሠንጠረዦች በአጭሩ ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 2

<u>በጥናት ቤተ ክርስቲያን በሥላሴ እምነት ላይ የተነሱ ኑፋቄዎች</u> [36]

| ተራ ቁጥ | ኑፋቄው | መሪዎቹ | ትምህርቱ/ እምነቱ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሞናርክያኒዝም[37] | ቴዎዶጦስ | ኢየሱስ ሲጠመቅ ክርስቶስ ሆነ፣ ከሞቱ በኋላ የአብ ልጅ ሆነ። (Adopted) |
| 2 | ሳቤልያኒዝም[38] | አውሳብዮስ | አንዱ እግዚአብሔር ራሱን በሦስት መንገዶች (ሞድ) ገልጿል።[39] |
| 3 | አሪያኒዝም | አሪዮስ | ክርስቶስ የመጀመሪያው ፍጡር ነው። |
| 4 | ከፊል አሪያኒዝም | ጎርጎሪዮስ | የክርስቶስ ማንነት እንደ አብ ነው ሆኖም ከአብ ያንሳል (Subordinate to the Father) |
| 5 | ማሊዶንያኒዝም | መቅዶንዮስ | መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ነው። |
| 6 | አፖሊንያኒዝም | አቡሊናርየስ | ክርስቶስ የሰው ነፍስ አልነበረውም። በቃል (Logos) ተተክቷል። |
| 7 | ንስትሮንያኒዝም | ንስጥሮስ | ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው አይደለም። ቃል (Logos) በኢየሱስ ሲያድር ክርስቶስ እግዚአብሔርን የያዘ ሰው (God-bearing man) ሆነ |
| 8 | ኢዮትክያኒዝም | አውጣኬን | የክርስቶስ ሰብእና በቃል (Logos) ተለውጧል። ክርስቶስ ሰው አይደለም። |
| 9 | ሞኖፊትዝም | ሳዊሮስ | ክርስቶስ አንድ ባሕርይ አለው። |
| 10 | ሞኖቴሊዝም | ቴዎዶስዮስ | ክርስቶስ የሰው ፈቃድ አልነበረውም፣ የመለኮት ፈቃድ ብቻ እንጂ። |

Adapted from Robert C. Walton, 1986, <u>Chronological and Background charts of church histroy.</u> Zondervan publishing house, Grand Rapids.

But the Godhead of the Father, of the Son, and of the Holy Ghost is all one, the Glory equal, the Majesty co-eternal. Such as the Father is, such is the Son, such is the Holy Ghost. The Father eternal, the Son eternal, and the Holy Ghost eternal. And yet they are not three eternals, but one eternal. ... So the Father is God, the Son is God, and the Holy Ghost is God. And yet they are not three Gods, but one God... the Unity in Trinity and the Trinity in Unity is to be worshipped.

[36] ስለ ኑፋቄዎች ምንነት ተጨማሪ ማብራሪያ በቀደሙት ገጾችና ከዚህ በታች የቀረቡትን የግርጌ ማስታዎሻዎች ይመልከቱ።

[37] Monarchianism is another term for modalism and "... this teaching not only says that God revealed himself in different "Modes" but it also says that there is only one supreme ruler ("Monarch") in the universe and that is God himself, who consists of only one person." <u>Ibid</u>. p.242. With regard to the Lord Jesus Christ it takes "the view that Jesus lived as an ordinary man until his baptism, but then God "adopted" Jesus as his "Son" and conferred on him supernatural powers. Adoptionists would not hold that Christ existed before he was born as a man, but only as an exalted man whom God called his "Son" in a unique sense." <u>Ibid</u> .p. 245.

[38] Sabellianism which is named after the teacher named Sabellius who lived in Rome in the early third century A.D. taught that "God is not really three distinct persons but only one person who appears to people in different "modes" at different times. For example, in the Old Testament God appeared as "Father". Throughout the Gospels, this same divine person, appeared as "the Son" as seen in the human life and ministry of Jesus. After Pentecost this same person then revealed himself as the "Spirit active in the church." Wayne Grudem <u>Ibid</u>. 242.

[39] Grenz refers to such kind of belief as "sequential divine expressions" Stanley Grenz, <u>Ibid</u> .p. 74. On the other hand church history tells us that during about this time "The three theologians known as the Cappadocian fathers-Basil, Gregory of Nyssa, and Gregory of Nazianzus- formulated the trinitarian doctrine. They used two Greek words "Ousia" (essence) and hypostasis ("center of consciousness" or "independent reality"). They declared that God is one <u>Ousia</u> but three <u>hypostaseis</u>. The three "independent realities share the same will, nature and essence (that is, the one ousia). Yet each has special properties or activities" Grenz. <u>Ibid</u> .p. 77-78.

ሠንጠረዥ 3

**በጥንት ቤተ ክርስቲያን ስለ ሥላሴ ትምህርት የተደረጉ ጉባኤዎችና ውሣኔዎች**[40]

| ተራ ቁጥር | ስብሰባው የተደረገበት ቦታ | ዓ.ም | የተሰብሳቢዎች ብዛት | ዋና ውሣኔዎች |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኒቂያ | 325 | 318 | ቻ ወልድ ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ (same substance/essence with the Father) መሆኑን አወጀ<br>ቻ አሪዮስን አወገዘ[41] |
| 2 | ቁስጥንጥንያ | 381 | 150 | ቻ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት አጸና/ተቀበለ<br>ቻ የመቅዶንዮስን ትምህርት አወገዘ |
| 3 | ኤፌሶን | 431 | 200 | ቻ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑን አጸና<br>ቻ የንስጥሮስን ትምህርት አወገዘ |
| 4 | ኬልቄዶን | 451 | 630 | ቻ የክርስቶስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርያት የማይደባለቁ፣ የማይለወጡ፣ የማይከፋፈሉ፣ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አጸና 42<br>ቻ የአውጣኬንን ትምህርት አወገዘ |

40 Adapted from: Robert C. Walton, Ibid.

41 'In repudiation of the teaching of Arius, the Nicene Creed insisted that Christ was "of the same substance as the Father.' The dispute with Arius concerned two words... homoosious ("of the same nature") and homoiousios ("of a similar nature") ... homo meaning "same" and homoi meaning "similar". Arius was happy to say that Christ was a supernatural heavenly being and that he was created by God before the creation of the rest of the universe and even that he was "similar" to God in his nature. The difference between the two words was only one letter the Greek letter iota [i] and some have criticized the church for allowing a doctrinal dispute on a single letter... But... the iota [i] did mark the difference between biblical christianity with a true doctrine of the Trinity and a heresy that did not accept the full deity of Christ and therefore was nontrinitarian and ultimately destructive to the whole Christian faith". Wayne Grudem, Ibid. pp. 244-245.

42 The Chalcedon council declared that:- "The one and the same Christ, Son, Lord, Only begotten to be acknowledged in two natures, without confusion, without change, without division, without separation; the distinction of the natures being in no way abolished because of the union, but rather the characteristic property of each one being preserved, and concurring into one person & one being." The Dictionary of Theology, IVP, 1994, P.138 (emphasis mine).



## 5.2 እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው

«እስራኤል ሆይ፣ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» (ዘዳ 6:4) የሚለውን ቃል እስራኤላውያን በየቀኑ የሚናገሩት ወይም የሚያውጁት (Shema) ነው:: እግዚአብሔር በቁጥር አንድ ነው:: አንድ አምላክ ብቻ አለን (ዘዳ 4:39):: እግዚአብሔር በባሕሪው፣ በመለኮትነቱ፣ በእርሱነቱ አንድ ነው:: ዘጸ 20:2-4፣ ዘዳ 6:6፣ ኢሳ 43:10፣ 1ቆሮ 8:4፣ 1ጢሞ 2:5፣ ኤፌ 4:6፣ ዮሐ 10:30፣ ማር 12:29-30፣ ያዕ 2:19 ይመልከቱ::

በዕብራይስጥ ቋንቋ አንድ የሚለው ቃል የሚገለጸው በሁለት ቃላት ነው:: አንደኛው ኢካድ (Echad) ሲሆን ሌላው ያክድ (Yacheed) ነው:: ኢካድ የሚለው በኅብረት አንድነትን (Compound Unity) ሲያመለክት ያክድ የሚለው ደግሞ አንድ ነጠላን (One and only one) ያመለክታል:: በዘዳ 6:4 «...አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» የሚለው የተገለጸው ኢካድ በሚለው ቃል ነው::

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ቃል ኪዳን አስቦ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ምድር ካወጣ በኃላ በሲና ምድረ በዳ በሙሴ በኩል ለእስራኤል የሰጠው የመጀመሪያ ሕግ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» (ዘጸ 20:3) የሚል ነው:: የእስራኤላውያን ከግብጽ ምድር መውጣት ዋና ዓላማም አምላካቸው እግዚአብሔር መሆኑን እንዲመሰክሩና ሁሉም ይህን አንድ አምላክ እንዲያመልኩ ነው:: ግብጻውያንም ሆኑ በከነዓንና አካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ብዙ አማልክት ይከተሉ የነበሩ ናቸው:: ለምሳሌ «ሞልክ» ለአሞናውያን (1ነገ 11:7)፣ «በዓል» ለከነዓናውያን (መሳ 2:13፣ 6:25)፣ «ቤልና ሜሮዳክ» ለባቢሎናውያን (ኤር 50:2፣ 51:44)፣ ወዘተ... አማልክቶቻቸው ነበሩ:: እግዚአብሔር ግን ከአማልክት ሁሉ በላይ የሆነ እውነተኛ አምላክ ነው (2ዜና 2:5):: «... ከአንተ በቀር አምላክ የለምና አንተ ታላቅ ነህ» (2ሳሙ 7:22)::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል ብዙ አማልክት ቢኖሩም እውነተኛው አምላክ ግን አንድ እግዚአብሔር ነው (1ቆሮ 8:6):: ሰይጣን ከአማልክት መካከል አንደኛውና የሌሎች ሁሉ «የበላይ ጠባቂ» ነው:: አድራሜሌክና አነሜሌክ (2ነገ 17:31)፣ ዳጎን (መሳ 16:23)፣ የሰማይ ንግሥት (ኤር 7:18፣ 44:17-19፣ 25)፣ ዲዮስቆሮስ (ሐዋ 28:11)፣ ሌሎች ጣዖታትና አማልክት ቢኖሩም «እግዚአብሔር ታላቅ

ምስጋናውም ብዙና፤ በአማልክትም ሁሉ ላይ የተፈራ ነው:: የአሕዛብ አማልክት ሁሉ ጣዖታት ናቸው፤ እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ» (1ዜና 16:25-26) ተብሎ እንደተጻፈ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስም እንዳለው «በእጅ የተሠሩ አማልክት አይደሉም» (ሐዋ 19:26):: ጣዖታትንና አማልክትን የሚያመልኩም ከአጋንንት ጋር ማኅበርተኞች የሆኑ ናቸው (1ቆሮ 10:21):: ሰዎች ሰይጣንንም ሆነ ሌሎችን አማልክት ቢያመልኩ፣ ቢገዙላቸውም ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለምና «በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች» ሆነውላቸዋል ማለት ነው (ገላ 4:8)::

እግዚአብሔር ስለራሱ እንዲህ ይላል:: «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፣ ምስጋናየንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም» (ኢሳ 42:8):: እንዲሁም በነቢዩ በኢዩኤል በኩል «እኔም አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደሆንሁ፣ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ታውቃላችሁ፣ ሕዝቤም ለዘላለም አያፍርም» (ኢዩ 2:27) ብሏል::

ሙሴና የእስራኤል ልጆች የኤርትራን ባሕር በተሻገሩና አሳዳጆቻቸውን ውኃው በከደናቸው ጊዜ ለእግዚአብሔር እንዲህ ብለው ዘመሩ:-

> አቤቱ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
> በምስጋና የተፈራህ፣ ድንቅንም የምታደርግ፣
> በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? (ዘጸ 15:11)

አዎን:- እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም:: አንባቢ ሆይ «እንግዲህ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር አምላክ እንደ ሆነ፣ ሌላም እንደሌለ ዛሬ እወቅ፣ በልብህም ያዝ» (ዘዳ 4:39)::

## 5.3 ሥላሴ:- በአንድነት - ሦስትነት

ሥላሴ (Trinity ወይም Triunity) የሚለው መጠሪያ አንድ አምላክ እግዚአብሔር በሦስት አካላት መኖሩንና በሦስትነት - አንድነት "three-in-oneness" የሚገልጽ ቃል ነው:: የሥላሴ ሦስትነት በስም (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) እና በአካል ነው::

ሥላሴ የሚለው ቃል እንደ አንድ ቃል (እንደ ጥሬ ቃል) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም:: የሥላሴ ትምህርት ግን በብሉይ ኪዳንና



በአዲስ ኪዳን በግልጽ ይገኛል:: ይህንን እንደሚከተለው እንመለከታለን::

### 5.3.1 በብሉይ ኪዳን

እግዚአብሔር ለዘላለም በሥላሴ የሚኖር አንድ አምላክ ስለሆነ የሥላሴ ትምህርት በብሉይና በአዲስ ኪዳን ተገልጾ ይገኛል:: ይህ የሥላሴ ትምህርት ከብሉይ ኪዳን ይልቅ በአዲስ ኪዳን ይበልጥ እንደተገለጸ ወይም ደምቆ እንደወጣ እንረዳለን::

ብሉይ ኪዳን ስለ ሥላሴ የሚያስተምረውን በሚከተለው ሁኔታ መመልከት ይቻላል::

#### ሀ. እግዚአብሔር በብዙ ቁጥር ተገልጾአል

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በብዙ ቁጥር (ወይም በብዙ አካላት) ተገልጾ ይታያል:: ከእነዚህም መካከል «እግዚአብሔር አለ:- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» (ዘፍ 1:26)፣ «እግዚአብሔር አምላክም አለ:- እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» (ዘፍ 3:22)፣ «እግዚአብሔርም አለ:- ... ኑ:-እንውረድ፣... ቋንቋቸውንም በዚያ እንደባልቀው» (ዘፍ 11:6-7)፣ «የጌታንም ድምጽ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ» (ኢሳ 6:8) የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው::[43]

አንዳንዶች እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ቁጥር የሚናገረው ለምሳሌ በኢትዮጵያ ቀደም ሲል የነበሩት ነገሥታት አንድ ሰው ሆነው እያለ ራሳቸውን «እኛ» ወይም «ግርማዊነታችን» እያሉ ይጠሩ እንደነበሩት እግዚአብሔር ራሱን በአክብሮት ለመጥራት የዋለ አገላለጽ ነው ብለው ያስባሉ:: ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንም መሪ፣ ንጉሥ ወይም ንጉሠ ነገሥት ራሱን በብዙ ቁጥር የሚጠራ አልነበረም:: ፈርዖን፣ አርጤክስስ፣ ናቡከደነፆር፣ ቂሮስ፣ ሄሮድስ፣ ወዘተ... ሁሉም ራሳቸውን የሚጠሩት በነጠላ ቁጥር ነው:: ስለሆነም በብሉይ ኪዳን የምናየው የብዙ ቁጥር አገላለጽ እግዚአብሔር ራሱን በአክብሮት ሲጠራ ነው ብሎ ማሰብ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን

---

43 እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በብዙ ቁጥር (ማለትም ከአንድ በላይ በሆኑ አካላት) የተገለጸ መሆኑን የሚያሳዩ ሆነው ሳለ ጥቅሶቹን በመረዳት ላይ ግን የተለያየ አመለካከት ያላቸው እንዳሉ ይታወቃል::

በቀጥታ ማንበብ ሳይሆን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ሀሳብ መጨመር ይሆናል::

ስለ ብዙ ቁጥር አጠራር ሌላው አመለካከት ደግሞ እግዚአብሔር በብዙ ቁጥር የሚናገረው መላእክትን ወይም የሰማይ ሠራዊትን (Divine Council) ከራሱ ጋር ደምሮ ነው የሚል ነው:: ሆኖም እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር «በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» ባለበት ጊዜ መላእክትን ማማከሩ እንደማይሆን ለማንም ግልጽ ነው:: እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር መላእክትን አልተጠቀመም ወይም ሰው በመላእክት ምሳሌ አልተፈጠረምና:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው (ዮሐ 1:3፣ ቆላ 1:15፣ ዕብ 1:2-3)::

ስለሆነም እነዚህ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የሚያመለክቱት እግዚአብሔር አንድ መሆኑንና በዚህ አንድ እግዚአብሔር ከአንድ በላይ (ወይም ብዙ) አካላት መኖራቸውን ነው::

ለ. ከአንድ በላይ አካላት በአንድ ላይ ተገልጸዋል

በብሉይ ኪዳን በአንድ ጥቅስ ወይም በአንድ ዐረፍተ ነገር ወይም ሀሳብ ውስጥ ከአንድ በላይ የሥላሴ አካላት ተጠቅሰው ይገኛሉ::

ዳዊት በመዝ 45:6-7:-

> «አምላክ ሆይ:- ዙፋንህ ለዘላለም ነው፤
> የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው::
> ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም ጠላህ፤
> ስለዚህ ከባልንጀሮችህ ይልቅ
> እግዚአብሔር አምላክህ የደስታን ዘይት ቀባህ» ይላል::

ይህ በአምላክ የተቀባውና መንግሥቱ ለዘላለም የሆነው አምላክ ማን ነው? ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው አምላክ ተብለው የተጠሩት ሁለት የተለያዩ አካላት ናቸው:: የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ ይህን ክፍል በዕብ 1:8 ላይ በመጥቀስ ዙፋኑ ለዘላለም የሆነውና በአምላክ የተቀባው እንዲሁም አምላክ ተብሎ የተጠራው የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ገልጿል::

በተመሳሳይ መንገድ ዳዊት በመዝ 110:1 «እግዚአብሔር ጌታዬን:- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» ይላል:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ክፍል በመጥቀስ «ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ:- ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው? ብሎ ጠየቃቸው»:: እነርሱም «የዳዊት ልጅ ነው» ብለው ሲመልሱለት «እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል? ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል? አላቸው (ማቴ 22:41-46):: ፈሪሳውያኑም ለዚህ መልስ አልነበራቸውም:: እንግዲያውስ ዳዊት ጌታዬ ያለውና እግዚአብሔር ደግሞ «በቀኜ ተቀመጥ» ያለው ማን ነው? ከአዲስ ኪዳን በግልጽ መገንዘብ እንደምንችለው በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማር 16:19፣ ሐዋ 1:55፣ ዕብ 8:1):: ስለሆነም ዳዊት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔር አንድ አምላክ መሆኑን፣ እንዲሁም ከአንድ በላይ አካላት ማለትም ጠላቶቹ ሁሉ የእግሩ መቀመጫ የሚደረጉለት ጌታ እና ጠላቶቹን ሁሉ የእግሩ መቀመጫ በማድረግ በቀኜ ተቀመጠ የሚለው እግዚአብሔር እንዳሉ ተረድቶ እንደነበር ግልጽ ማስረጃ ነው::

ኢሳይያስ «እነርሱ ግን ዐመፁ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ» (ኢሳ 63:10) ብሎ ሲናገር የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ራሱ እግዚአብሔር የሆነ፣ በአካል ከእግዚአብሔር የተለየ መሆኑን፣ እርሱም የሚመረር ወይም የሚያዝን መሆኑን ከሌሎች ጥቅሶች ጋር በማገናዘብ መረዳት ይቻላል::

እንግዲህ እላይ ከተገለጹትና ከሌሎችም ጥቅሶች (ዘፍ 1:2፣ 2ሳሙ 23:2-3 ነህ 9:20፣ መዝ 139:7፣ ኢሳ 48:16፣ 61:1፣ ሆሴ 1:7፣ ሚል 3:1-2) በብሉይ ኪዳን ከአንድ በላይ የሆኑ የሥላሴ አካላት በአንድ ጊዜ ወይም ሁኔታ አብረው መገለጻቸውን መረዳት ይቻላል::

ሐ. የእግዚአብሔር መልአክ

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መልአክ አንዳንድ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ሌላ ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሔር መልአክ (በእግዚአብሔር እንደተላከ መልእክተኛ) ሆኖ ቀርቧል::

የእግዚአብሔር መልአክ አንዳንድ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ (2ሳሙ 24:16) ሌላም ጊዜ እራሱ እግዚአብሔር (ወይም ከሥላሴ ውስጥ ሁለተኛው አካል) መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን:: የዚህን መልአክ መለኮትነት ለማረጋገጥ የሚከተለውን እንመልከት:: የእግዚአብሔር መልአክ:-

ሐ.1 እግዚአብሔር ተብሏል:: ዘፍ 16:7-13፣ 18፣2፣ 10፣13፣ 22:10-12፣15-18፣ ዘጸ 3:2-6፣14፣ 18፣ መሳ 2:1፣5፣ 6:11፣14፣16
ሐ.2 ሰዎች እግዚአብሔር እንደሆነ አውቀውታል:: ዘፍ 16:9-13፣ መሳ 6:22-24፣ 13:21-23፣ ዘፍ 32:24-30 እና ሆሴ 12:4-6
ሐ.3 እራሱን እግዚአብሔር ብሏል:: ዘፍ 31:11፣ 13፣ ዘጸ 3:2፣6፣14
ሐ.4 አምልኮ ተቀብሏል:: ኢ.ያ 5:14፣ መሳ 2:4
ሐ.5 በመለኮት ሥልጣን ተናግሯል:: መሳ 2:1-3

በሕልም ያዕቆብን የጠራው «የእግዚአብሔር መልአክ» (ዘፍ 31:11) «ለእኔ ስእለት የተሳልህበት የቤቴል እምላክ እኔ ነኝ» (31:13) ይለዋል:: ይህም ያዕቆብ ስእለት የተሳለለት የእግዚአብሔር መልአክ በቤቴል የተገለጠለት እግዚአብሔር ነው (ዘፍ 28:13-22፣ 35:7):: እንዲሁም በሌላ ስፍራ ያዕቆብ «እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ» (ዘፍ 32:30) የሚለውና የታገለው የእግዚአብሔር መልአክ በሌላ ስፍራ ደግሞ «በኃልማሳነቱም ጊዜ ከአምላክ ጋር ታገለ ከመልአኩም ጋር ታግሎ አሸነፈ፣ አልቅሶም ለመነው:: በቤቴልም አገኘው፣ በዚያም ከእኛ ጋር ተነጋገረ:: እርሱም የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው፣ የመታሰቢያው ስም እግዚአብሔር ነው» (ሆሴ 12:4-6) ይላል::

ስለሆነም ይህ የእግዚአብሔር መልአክ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን ለሰው የገለጠበት መንገድ (Theophany) ሲሆን ይህም መልአክ ከሥላሴ ሁለተኛው አካል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠበት (Christophany) ነው ማለት ይቻላል:: በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ጥቅሶች ይህ የእግዚአብሔር መልአክ እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራ ነገር ግን ከእግዚአብሔር (አብ) በአካል የተለየ ሌላ አካል ለመሆኑ ያስረዳሉ::44

### 5.3.2 በአዲስ ኪዳን

የእግዚአብሔር «የባሕርዩ ምሳሌ» (ዕብ 1:3) የሆነውና «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» (ማቴ 1:23) የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመጣ የሥላሴ ትምህርት ከብሉይ ኪዳን ይልቅ በአዲስ ኪዳን የበለጠ ግልጽ ሆኖና ደምቆ እንደሚወጣ የታወቀ ነው:: ይህንም እንደሚከተለው እንመለከታለን::

44 ይህም ሆኖ የእግዚአብሔርን መልአክ ማንነት ለመረዳት ወይም ለመተርጐም ጥንቃቄ ዐውዱን ማጥናትና ማገናዘብ ያስፈልገዋል፣ «ምስጢርነት» አለውና::



በማቴ 3:16-17 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል:: «ኢየሱስም ከተጠመቀ በኃላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፣ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፣ እነሆም:- ድምፅ ከሰማያት መጥቶ:- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ»:: በዚህ ክፍል ሦስቱም የሥላሴ አካላት በአንድ ላይ ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን:: እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ሲናገርና ኢየሱስን የምወደው ልጄ ብሎ ሲጠራ፣ እግዚአብሔር ወልድ በምድር ላይ በውኃ ተጠምቆ ሲወጣና አብ ስለእርሱ ሲናገርለት፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ መልክ ሲወርድና በእግዚአብሔር ወልድ ላይ ሲመጣ እንመለከታለን::

በተመሳሳይ ሁኔታ በማቴ.28:19 «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ይላል:: በዚህም ክፍል ሦስቱም የሥላሴ አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በአንድነትና በእኩልነት ተገልጸው እንመለከታለን:: እንዲሁም ሥላሴ በአካል ሦስት ሆነው ሳለና በቋንቋ (ሰዋሰው) ሕግ ደግሞ ከአንድ በላይ ለሆኑ ነገሮች የዐረፍተ ነገሩ ማሠሪያ ብዙ ቁጥርን እንዲገልጽ የሚጠበቅ ቢሆንም በዚህ ክፍል የምናገኘው ግን «ስሞች» የሚል ሳይሆን «ስም» የሚለውን ነው:: ይህም ለእግዚአብሔር በሦስትነት - አንድነት ማለትም በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ ለመሆኑ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው::

እንዲሁም በ2ተሰ 2:16-17 «ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የወደደን በጸጋም የዘላለምን መጽናናት በጎንም ተስፋ የሰጠን እግዚአብሔር አባታችን ልባችሁን ያጽናኑት በበጎም ሥራና በቃል ሁሉ ያጽኑአችሁ» ይላል:: በዚህ ክፍል ጌታ ኢየሱስና እግዚአብሔር አብ ከአንድ በላይ የሆነን ስም ወይም ሁኔታን በሚያያይዝ «ና» በተሰኘ መስተጻምር ተያይዘውና በብዙ ቁጥር ተገልጸው ይታያል:: ይህም የሥላሴ አካላት ከአንድ በላይ መሆናቸውን ያስረዳል::

ከዚህም በተጨማሪ የሥላሴ ትምህርት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ግልጽ ሆኖ የቀረበ ለመሆኑ የሚከተሉትን በዝርዝር መመልከት ይጠቅማል::

ሀ. በብሉይ ኪዳን መድኀኒት (አዳኝ) የተሰኘው እግዚአብሔር (ያህዌ) ነው:: በአዲስ ኪዳን ይህ ስያሜ ለኢየሱስ ክርስቶስም ሆኖአል (መዝ 78:35፣ ኢሳ 41:14፣ ማቴ 1:21፣ ሉቃ 1:76-79፣ 2:17፣ ቲቶ 2:13-14)::

ለ. በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች (አማኞች) ልብ የሚኖረው ያህዌ ነው:: በአዲስ ኪዳን በክርስቲያኖች ውስጥ የሚያድረው መንፈስ ቅዱስ ነው (መዝ 74:2፣ 135:21፣ ኢዩ 3:17-21፣ ዘካ 2:10-11፣ ሐዋ 2:33፣ ሮሜ 8:9፣11፣ 1ቆሮ 3:16፣ ገላ 4:6፣ ኤፌ 2:22፣ ያዕ 4:5፣ ዘፍ 16:7-11 እና 13፣ 32:23 እና ሆሴ.12:4፣ ዘጸ 3:2-15፣ 13:21 እና 14:19፣ ዘኁ 20:16፣ ዘፍ 19:1,21፣ 31:11፣13፣ መሳ 6:12-16፣ 2:1-5)::

ሐ. በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር አብ ልጁን ልኳል ዮሐ 3:16፣ ገላ 4:4፣ ዕብ 1:6፣ 1ዮሐ 4:9::

መ. እግዚአብሔር አብና ወልድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ልከዋል ዮሐ 14:26፣ ዮሐ 15:26፣ 16:17፣ ገላ 4:6::

ሠ. አብ ለወልድ ተናግሯል ማር 1:11፣ ሉቃ 3:22::

ረ. ወልድ ከአብ ጋር ሲነጋገር ኅብረት አድርጓል ማቴ 11:25-26፣ 26:39፣ ዮሐ 11:41፣ 12:27-28::

ሰ. በአማኞች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል ሮሜ 8:26::

የእግዚአብሔርን በአንድነት-ሦስትነት እና በሦስትነት-አንድነት ለማገናዘብ እንዲረዳ በመለኮት፣ በባሕሪና በሥራ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል::



## ሠንጠረዥ 4
## እግዚአብሔር
## በአንድነት - ሦስትነት፣ በሦስትነት -አንድነት

| ሥላሴ | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| ስም:- እግዚአብሔር/አምላክ | ዮሐ 3:16 ሐዋ 3:13 ሮሜ 1:7 | ዮሐ 1:1፣ ዕብ 1:8፣ ቆላ.2:9፣ ዮሐ 20:28፣ ሮሜ 9:5፣ ቲቶ 2:13፣ 1 ዮሐ 5:20 | ሐዋ 5:3-9 2ቆሮ 3:17 |
| ባሕርያት:-ዘላለማዊ ነው | መዝ 90:2 | ሚክ 5:2፣ ራእ 1:18 | ዕብ 9:14 |
| ሁሉን ቻይ ነው | ዘፍ 17:1፣ ዮሐ 5:21 | ዮሐ 6:44፣ ዮሐ 5:21 1ጢሞ 6:15 | ዘካ 4:6፣ ሐዋ 1:8፣ሮሜ 15:19፣ |
| አይለወጥም | ያዕ 1:17 | ዮሐ 8:58፣ ዕብ 13:8 | ዮሐ 14:16 ኢሳ 11:2 1ቆሮ 2:11 |
| ሁሉን ያውቃል | ኤር 17:10፣ ማቴ 6:8 10:29-30፣ ሐዋ 1:24 | ዮሐ 2:25፣ 18:4 ራእ 2:23 | |
| ሁሉም ቦታ አለ | ኤር 23:24 | ማቴ 18:20፣ 28:20 | መዝ139:7 |
| ቅዱስ ነው | ራእ 15:4 | ሐዋ 3:14፣ ራእ 3:7 | «ቅዱስ መንፈስ» |
| እውነት ነው | ዮሐ 7:28፣ 17:3 | ዮሐ 14:6፣ ራእ 3:7 | ኢሳ 63:10 ዮሐ 14:16፣1ዮሐ 5:7 ነህ 9:20 |
| ቸር ነው | ሮሜ 2:4፣ ናሆ 1:7 | | |
| ሥራዎች:- በመፍጠር | መዝ.102:25 | ቆላ.1:16፣ ዕብ.1:2-3 | ዘፍ.1:2 |
| በመስቀል ሞት | መዝ.22:15፣ ሮሜ 8:32 ዮሐ.3:16 | ዮሐ.10:17-18 ገላ.2:20 | ዕብ.9:14 |
| በክርስቶስ ትንሣኤ | ሐዋ.2:24 | ዮሐ.10:18 | |
| ሕይወት በመስጠት | ዮሐ.5:21 | ዮሐ.5:21 | 2ቆሮ.3:6 |

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንዳየነው እግዚአብሔር በሦስት አካላት ተገልጾ የሚኖር አንድ አምላክ ነው:: እንዲሁም ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንዳየነው እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ ነው:: ይህ በአንድነት-ሦስትነት የሆነው የእግዚአብሔር ማንነት ዓለም ሳይፈጠር (ዮሐ 17:5፣ 24) ከዘላለም ነው::

የሥላሴ ትምህርት በክርስትና እምነት መሠረታዊ ነው:: ያለ ሥላሴ የእምነት መሠረትነት ክርስትና የሚባል እምነት የለም:: የስህተት

ትምህርት የመጀመሪያውና ዋናው የችግር ምልክቱ ስለ ሥላሴ ያለው አስተምህሮ የተሳሳተ ወይም የተዛባ ሆኖ መገኘቱ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች እንደሚሉት" Christianity stands or falls with the confession of the deity of Christ and of the Trinity"[45] "Understanding God as triune is a non-negotiable dimension of the gospel"[46] "Every type of heresy is, in the last analysis an attack upon the Trinity.[47]

ሰው ሌላውን ምድራዊ እውቀት በሚረዳበት አስተሳሰብና ችሎታ የሥላሴን እውነት በትንታኔ፣ በስሌት ወይም በቀመር ሊገነዘበው የሚችለው አይደለም:: ሰው በምድር ላይ ያየው፣ የሰማው ወይም የተለማመደው እንዲህ ዓይነት ሕልውና ስለሌለ ሥላሴን በምሳሌም ቢሆን ሊገልጸው አይችልም:: ስለሆነም እግዚአብሔር አንድ አምላክ በሦስት አካላት ተገልጾ ይኖራል የሚለው የሥላሴ ትምህርት ከሰው መረዳት በላይ የሆነ ምስጢር ነው:: ይህን ዘላለማዊ እውነት ሙሉ በሙሉ ለማገናዘብ ለሰው ልጅ ከችሎታው በላይና ምስጢር ቢሆንበትም ከዚህ በላይ በዝርዝር እንዳየነው የሥላሴ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የተጻፈ እውነት ነው:: ይህን የተገለጸውንና የተጻፈውን እውነት በማመን በሕይወት እንኖራለን፣ ለልጆቻችንም እናስተምራለን:: የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል «ሚስጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፣ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለም ለልጆቻችን ነው» (ዘዳ 29:29)::

ስለ ምስጢረ ሥላሴ አንዱ እንዳለው:-

"Try to explain it, you will lose your mind.
Try to deny it, you will lose your soul"

ወደ አማርኛ ሲተረጐም:-
«ልታስተነትነው ብትሞክር አእምሮህን ታጣለህ፣
ልትክደው ብትሞክር ሕይወትህን ታጣለህ»

---

45 Wayne Grudem. Ibid .P.281

46 Stanley Grenz. Ibid .P. 70

47 Cornelius Van Til, An introduction to systematic theology, 1974, Phillipsburg: Presbyterian and reformed publishing Co., P.223.



ስለዚህ አንባቢ ሆይ እግዚአብሔር በቃሉ የገለጠውን እውነት «ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን» (ዮሐ.20:27)::

## 5.4 የሥላሴ ትምህርት መግለጫ

ምንም እንኳ የሥላሴን ትምህርት ሙሉ በሙሉ ለመገንዘብ ከአእምሮ በላይና ምስጢር የሆነ ቢሆንም እግዚአብሔር በረዳንና በገለጠልን መጠን በሰው አቅም ለመረዳት ይቻል ዘንድ በሦስት ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው በማጠቃለል እንመለከታለን::

1. እግዚአብሔር ሦስት አካል ነው (እግዚአብሔር በሦስት አካላት ይኖራል)
2. እያንዳንዱ የሥላሴ አካል እግዚአብሔር ነው
3. እግዚአብሔር አንድ ነው::

### 5.4.1 እግዚአብሔር በሦስት አካላት ይኖራል

አካል የሚለው ቃል ስለ እግዚአብሔር ማንነት በበቂ ሁኔታ ለመግለጽ የማይችል ቃል መሆኑ ቢታወቅም ስለ ሥላሴ ማንነት ሲገለጽ «የዓለመ ግዘፍ አካልን» የሚያመለክት ሳይሆን «የዓለመ መንፈስ አካልን» የሚገልጽ ነው:: አቶ መሠረት ስብሐት ለአብ፣ ሥላሴ በተዋሕዶ በተሰኘው መጽሐፋቸው ይህን ሲገልጹ:-

> *በጣም ልም ከሆነ ብናኝና በጣም ረቂቅ ከሆነ ትናኝ እጅግ በጣም ረቂቅ ከሆነ አየር ጀምሮ፣ የመጨረሻ ጥጥርነትና ጉልህነት እስካለው ውፍረት ደንዳናነትም ድረስ፣ በዚያ በሚገኝበት ዐቅምና ብቃት እንደየመጠኑ እንደየመልኩ ተወስኖ መኖሩ እንደሚታወቅ ሁሉ፣ በዓለመ ግዘፍ «አካል» ተብሎ ይሰየማል:: በሌላም አገላለጽ በሰማይ ያለው የሚዳሰስና የሚገሠሥ የሚቋጠርና በአምስት ሕዋሳት ተደርሶበት የሚጨበጥ ነገር ሁሉ፣ በዓለመ ግዘፍ እካልነት እንዳለ «ያለ መሆኑ» ይታወቃልና «አካል» በሚል ስያሜ መጠራት ገንዘቡ ነው::48*

በሌላ በኩል ደግሞ አካል ተብሎ ሊጠራ የሚገባው በግዘፍ አካል ላለ ወይም በአምስት ሕዋሳት ብቻ ለሚታወቅ ነገር ብቻ የተወሰነ

---

48 መሠረት ስብሐት ለአብ፣ ሥላሴ በተዋሕዶ፣1988 ዓ.ም፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 165

አለመሆኑንና በዐይን ለማይታይ ነገር ግን በሕያውነት ለሚኖር እንደሚውል ሲገልጹ:- «በዓለመ ነፍስ የሚኖር አካል እኔ የሚል ነባቢ ለባዊ አለሁ ባይ ነው:: ይህም ራሱን ለቻለ ለራሱ ብቁዕ የሆነ ዕውቀት ቀዋሚነት ላለው አለሁ ባይ ቁመና በመሆን ብቻ የተሰጠ ስያሜ ነው»49 ይላሉ::

ይህን ትርጉም በመንተራስ አካል የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ሲውል «እኔነት» ያለው ተብሎ ሊተረጐም ይችላል:: በዚህም መሠረት አብ እኔነት አለው፣ ወልድ እኔነት አለው፣ መንፈስ ቅዱስ እኔነት አለው:: ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ማየት እንችላለን::

በዮሐ.1:1 ላይ «በመጀመሪያው ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ሲል ቃል «እኔነት» ወይም አካል ያለው በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ፣ እራሱ እግዚአብሔር የሆነ ግን ደግሞ ከእግዚአብሔር (አብ) በአካል የተለዬ መሆኑን ማገናዘብ ይቻላል:: ይህ እኔነት ያለው «ቃል» የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ 1:18):: እንዲሁም በዮሐ 14:26 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል::» ሲል አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተገልጸውና እኔነት ኖሯቸው እንመለከታለን::

በሞዳሊዝም እምነት እንደሚታመንበት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ለአንዱ እግዚአብሔር የተለያዩ የመጠሪያ ስሞች ሳይሆኑ እነዚህ ስሞች ሥላሴ በሦስት አካል የሚታወቁባቸው ስሞች ናቸው:: አንድ ሰው ገበሬ፣ ባል እንዲሁም አባት ሊሆን እንደሚችል ሁሉ አንዱ እግዚአብሔርም በሦስት መንገድ ወይም «ሞድ» ሁኔታ ነው የተገለጸው ብለው የሚያስቡ ቢኖሩም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚናገረው ግን እያንዳንዱ የሥላሴ አካል እኔነት ያለው መሆኑን ነው:: «ሥላሴ ግን የአካል፣ የግብር፣ የኩነት ሦስትነት፣ የመለኮት፣ የባሕርይ፣ የህልውና አንድነት አላቸው::»50 ስለሆነም «እነሆም አብ፣ አብ እንደሆነ፣ ወልድም ወልድ እንደሆነ፣ መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ፣ በየአካላቸው ተለይተው፣ በየስማቸው ታውቀው፣

49መሠረት ስብሐት ለአብ፣ ገጽ 170

50 መሠረት ስብሐት ለአብ፣ ገጽ 210



ዘለዓለማዊ በሚሆን ጽንዕ ሳይለወጡና ሳይለዋወጡ፣ ሳይቀያየሩና ሳይዋዋጡ ይኖራሉና ነው::»51

### 5.4.2 እያንዳንዱ የሥላሴ አካል እግዚአብሔር ነው

የእግዚአብሔር ያልተከፈለ፣ ያልተቀነሰ እርሱነት በሙላት ለሥላሴ ለሁሉም እኩል አላቸው:: ስለሆነም አብ:- እግዚአብሔር ነው፤ ወልድ:- እግዚአብሔር ነው፤ መንፈስ ቅዱስ:- እግዚአብሔር ነው:: ሦስቱም የሥላሴ አካላት በመለኮት፣ በባሕርይ፣ በህልውና ፍጹም እኩል በመሆቸው አንደኛው የሥላሴ አካል ከሌላኛው አይበልጥም ወይም አያንስም::

የሥላሴ እምነት እግዚአብሔር በሦስት አካል መኖሩንና እያንዳንዱም አካል እግዚአብሔር መሆኑን ማመን ብቻ ቢሆን ኖሮ እምነቱ ምናልባት ለፍጥረታዊ ሰው አእምሮ እምብዛም ባላስቸገረ ነበር:: ይህ እምነት ግን ሦስት አምላኮችን ማመን (Tritheism) ይሆናል:: በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው እግዚአብሔር ሦስት አምላኮች የሆኑ አይደለም፣ አምላክ አንድ ነውና:: እግዚአብሔር በሦስት አካላት ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖርና እያንዳንዱም የሥላሴ አካል ፍጹም እግዚአብሔር መሆናቸውን ቀደም ሲል በእግዚአብሔር ቃል እንዳረጋገጥን ሁሉ እግዚአብሔር አንድ አምላክ መሆኑ ፍጹም እውነት ነው::

### 5.4.3 እግዚአብሔር አንድ ነው


አንድ የማይከፈል አምላክ አለ:: እግዚአብሔር በቁጥር፣ በባሕርይ አንድ ነው (ዘዳ 6:4):: የሥላሴ አካላት እያንዳንዳቸው ፍጹም እግዚአብሔር የሆኑ ሲሆኑ በአንድ ላይ ተደምረው 1+1+1= 3 እንደሚለው የሂሳብ ስሌት ሦስት እግዚአብሔሮች አይደሉም ያሉት፤ አንድ እግዚአብሔር እንጂ:: (1ነገ 8:60፣ ኢሳ 43:10፣ 44:6-8፣ ማር 12:29-30፣ ኤፌ 4:6፣ ሮሜ 3:30፣ 1ጢሞ 2:5):: እግዚአብሔር አንድ መሆኑን ማመን መልካም ማድረግ ነው (ያዕ 2:19)::

እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል እንዲህ ይላል:- «ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፣ ከእኔም በቀር ማንም የለም:: እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፣ እኔ አምላክ ነኝና፣

51መሠረት ስብሐት ለአብ፣ ገጽ 221

ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትጸኑማላችሁ» (ኢሳ 45:21-22)::

ስለ እግዚአብሔር አንድነት ለመረዳት የሚቀጥለው ስዕላዊ መግለጫ ያግዛል::




ሥዕል 1: በአንድነት ሦስትነት፤ በሦስትነት አንድነት (ሥዕላዊ መግላጫው በበርካታ የሥነ መለኮት መጽሐፍት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ይህ ጸሐፊ መጠነኛ የአቀራረብ መሻሻል በማድረግ እዚህ አቅርቦታል::)

«ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋውም ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን» (1ጢሞ 1:17)::

## 5.5 ስለ ሥላሴ ምሳሌያዊ አገላለጾች

የሥላሴን ምስጢር ቀለል ባለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲቻል ሰዎች በዘመናት ውስጥ የተለያዩ ምሳሌዎችንና መግለጫዎችን ለመጠቀም ሞክረዋል:: ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ::

ሀ. ዛፍ (ሥሩ፣ ግንዱና ቅርንጫፉ)
አንድ ዛፍ - ዛፍ ተብሎ የሚታወቀው ሦስቱ ክፍሎቹ ማለትም ሥር፣ ግንድና ቅርንጫፍ ሲኖሩት ነው:: ሆኖም እያንዳንዱ የዛፍ ክፍል በራሱ ዛፍ ተብሎ አይጠራም:: እንዲሁም



እያንዳንዱ የዛፍ ክፍል የራሱ የሆነ የተለየ ባሕርይ (Property) አለው እንጂ ሦስቱም አንድ ዓይነት ባሕርይ የላቸውም::

ለ. እንቁላል (አስኳሉ፣ ፈሳሹና ቅርፊቱ)
ይህ እላይ በ«ሀ» ስለ ዛፍ በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት የሚታይ ምሳሌ ነው:: ሦስቱ የእንቁላሉ ክፍሎች በአንድነት አንድ እንቁላል ቢሆኑም ክፍሎች በየራሳቸው ግን ሙሉ እንቁላል አይደሉም::

ሐ. ውኃ (ጋዝ ወይም እንፋሎት፣ ፈሳሽ ውኃና በረዶ)
እነዚህ ሦስት ሁኔታዎች አንድ የተወሰነ መጠን ያለው ውኃ በአንድ ጊዜ የሚገኝባቸው ሁኔታዎች አይደሉም::52 ውኃው በረዶ ሆኖ እያለ ያው ውኃ እንፋሎት ሆኖ አይገኝም፣ በረዶ እንጂ:: እንዲሁም ውኃ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሲሆን የሚኖረው ባሕርይ የተለያየ ነው፣ አንድ ዓይነት አይደለም:: ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር በተለያየ «ሞድ» ነው የተገለጸው ለሚለው የሳቤሊየስ አስተሳሰብ መግለጫ ይውላል:: ስለሆነም ይህ የውኃ ምሳሌ ለሥላሴ እምነት ምሳሌ ወይም መግለጫ ሊሆን አይችልም::

መ. አካል (ስሜት፣ፈቃድ፣ እውቀት)
ስሜት፣ ፈቃድና እውቀት በአንድነት የአካል ወይም የእኔነት መግለጫዎች ቢሆኑም የትኛቸውም ለብቻቸው አካልን አይገልጹም፣ ወይም በራሳቸው አካል ተብለው ሊጠሩ አይችሉም:: እንዲሁም ይህን በሚመስል ሁኔታ የሚቀርቡ ሌሎች ምሳሌዎች:-
- ጊዜ (ያለፈ፣ አሁን፣ የወደፊት)
- የአንድ ቁስ አካል (ቁመት፣ወርድ፣ ስፋት) የሚሉ

ቢኖሩም ሁሉም ሥላሴን ሊገልጹ አይችሉም::

ሠ. አባትና ልጅ
በተፈጥሮ አባትና ልጅ የሆኑ ሰዎችን በመውሰድ በሥላሴ አካላት መካከል በከፊል በእግዚአብሔር አብና በወልድ መካከል ላለው

---

52Grudem says " There is a certain atmospheric condition (called the " triple point" by Chemists) at which steam, liquid water and ice can all exist simultaneously, but even then the quantity of water that is steam is not ice or liquid, the quantity that is liquid is not steam or ice, etc." Ibid. P.240

አንድነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል ብለው የሚገልጹ አሉ:: የተፈጥሮ አባትና ልጅ ኅብረት (ወይም አንድነት) ሊኖራቸው ቢችልም እነርሱ ግን ሁለት የተለያዩ ሰዎች ናቸው:: ሁለት እንጂ አንድ መሆን አይችሉም፣ ሁለት እንደሆኑም ይኖራሉ::[53] እግዚአብሔር ግን በሦስት አካል የሚኖር አንድ አምላክ ነው::

ረ. ፀሐይ:- (አካል፣ ሙቀት እና ብርሃን)
ከአንዷ ፀሐይ ሙቀት ይገኛል፣ ብርሃን ወይም ኃይል ይመጣል፣ ፀሐይ አካልም አላት:: የፀሐይ ብርሃን ፀሐይ ይባላል፣ የፀሐይ ሙቀት ፀሐይ ይባላል፣ እንዲሁም የፀሐይ አካል ፀሐይ ይባላል:: ሦስቱም ፀሐይ ተብለው ሲጠሩ ግን አንድ ፀሐይ ነች:: ይሁን እንጂ ለምሳሌ ያህል ፀሐይ በቀንና በሌሊት በሁሉም ቦታ አትገኝም:: ከዚህም በተጨማሪ ምሳሌው ሌሎች ብዙ እንከኖች አሉት::

እንግዲህ በአጠቃላይ እነዚህ ምሳሌዎች የሥላሴን በሦስትነት አንድነት ለመግለጽ ትንሽ ሀሳብ የሚሰጡ ቢመስልም ሁሉም ምሳሌዎች በቂ መግለጫዎች አይደሉም:: እንዲያውም አንዳንዶቹ (ለምሳሌ የውኃው መግለጫ) በምሳሌነቱ የሥላሴን መሠረታዊ ማንነት የሚቃረኑ ናቸው:: በአንድ ጊዜ ሦስቱንም የውኃ ዓይነቶች/ ገጽታዎች ለማግኘት አይቻልም:: በረዶ ከሆነ ፈሳሽ ወይም ተን አይሆንም:: እንዲያውም ይህ ምሳሌ ኢየሱስ በዘመናት ውስጥ በተለያየ ሞድ ተገልጿል ለሚለው የስህተት ትምህርት ቀራቢ ምሳሌ ነው::

እላይ ከተዘረዘሩት ምሳሌዎች የፀሐዩ ምሳሌ በመጠኑም ቢሆን የተሻለ ቢመስልም የእግዚአብሔርን ማንነት ግዑዛን ነገሮች ሊገልጹ አይችሉም:: እግዚአብሔርን ምሳሌ በመስጠት መግለጽ ከባድ በመሆኑ ሥላሴን ለማስረዳት ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት ምሳሌዎች መጠቀም ለስህተት ሊያጋልጥ ይችላል:: ስለሆነም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው::

---

53 ከአባትና ልጅ ምሳሌ ይልቅ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ሁለት ሆነው ሳለ በተቀደሰ ጋብቻ አንድ ሥጋ የመሆን ምስጢር የተሻለ ምሳሌ ይሆናል:: ይህም ቢሆን ግን በሥላሴ አካላት መካከል ያለውን ፍጹም አንድነት በተሟላ ሁኔታ አይገልጽም:: ይህ የባልና የሚስት አንድነት በጋብቻቸው ቀን የሚጀመርና መጨረሻም ያለው ሲሆን እግዚአብሔር አንድ አምላክ በሦስት አካል ያለው ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም ነው::



## 5.6 የሥላሴ ትምህርት ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በሦስት አካል የሚኖር መሆኑን፣ እያንዳንዱ የሥላሴ አካል እግዚአብሔር መሆኑንና እግዚአብሔር አንድ ብቻ እንደሆነ በቀደመው ክፍል በሰፊው ተመልክተናል:: አሁን ደግሞ በሥላሴ አካላት መካከል ያሉትን ልዩነቶች (distinctions) እና የእርስ በርስ ተዛምዶዎች (relationships) እንመለከታለን::

### 5.6.1 ልዩነቶች (Distinctions)

በመለኮታዊ ሕልውና (Divine Being) ውስጥ የሥላሴ አጠራርና አሠራር በተወሰነ ቅደም ተከተል[54] መሠረት ነው:: በመለኮታዊ አጠራር አብዛኛውን ጊዜ አብ ቀዳሚ ነው፣ በኋላም ወልድ፣ በኋላም መንፈስ ቅዱስ:: ይህ ቅደም ተከተል ወይም ተራ በምንም ሁኔታ ከጊዜ ወይም ከክብር ጋር የተያያዘ አይደለም፤ ሁሉም የሥላሴ አካላት እኩል ሥልጣን (ዮሐ.5:21)፤ እኩል ክብር (ዮሐ.5:23) አላቸውና:: ይህ በሥላሴ መካከል ያለው የእርስ በርስ ተዛምዶ ወይም ቅደም ተከተል ለሥላሴ አሠራር (Operational Order) መሠረት ነው:: ይህ የሥላሴ አሠራር ሥርዓት ወይም «ኢኮኖሚካል ትሪኒቲ» የሚያመለክተው እያንዳንዱ የሥላሴ አካል በመፍጠር፣ በመጠበቅ፣ በማዳንና በመለኮታዊ ሥራዎች ውስጥ የሠራውን ነው::

እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በተመለከተ እያንዳንዱ የሥላሴ አካላት የተለያየ ተግባር ወይም የሥራ ክፍፍል ወይም ይበልጥ የሚያተኩሩበት ወይም የሚታወቁበት ተግባር አላቸው:: የሥላሴ አካላት ከፍጥረት ጋር ያላቸው የአሠራር ሥርዓትና እርስ በርሳቸው የሚያደርጉት ግንኙነት "economy[55] of the Trinity" ተብሎ ይታወቃል::

---

54 ይህ ቅደም ተከተል በማቴ 28:19 በሌሎችም ቦታዎች የሚታይ ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎች ለየት ያለ አቀራረብ ይታያል:: በ2ቆሮ 13:14 ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር (አብ) መንፈስ ቅዱስ፣ ይላል:: ይሁዳ 20፣ 21 መንፈስ ቅዱስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር አብ፣ ይላል:: እንዲሁም ሌሎች ጥቅሶች 1ቆሮ 12:4-6፣ ኤፌ 4:4-6፣ 5:18-20፣ 2ተሰ 2:13-14 ይገኛሉ::

55 The use of the term 'economy in this case refers to "ordering of activities", just like "home economics" - meaning the ordering of activities within the household.

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው በሥላሴ መካከል እርስ በርስ ባለው ዘላለማዊ ተዛምዶ ነገር ሁሉ ከአብ ነው፣ (ምንጭ)፣ ይህም የሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1ቆሮ 8:6):: ወደ አብ የምንገባው በመንፈስ ቅዱስ ነው (ኤፌ 2:18):: እንዲሁም በኤፌ 1:3-14 ያለውን ስንመለከት በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ውስጥ ያቀደው አብ ነው (ቁ.3-6)፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነታችንን ሰጠን (ቁ.7-12)፣ መንፈስ ቅዱስ አተመን (ቁ.13-14)::

በመፍጠር ሥራ ውስጥ የመፍጠርን ቃላት እግዚአብሔር አብ ተናገረ (ዘፍ 1:1፣ ራእ 4:11)፣ ይህ የመፍጠር ሥራ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሆነ (ዮሐ 1:3፣ ቆላ.1:16፣ 1ቆሮ 8:6፣ ዕብ 1:2)፣ መንፈስ ቅዱስም በዚህ የመፍጠር ሥራ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ተካፍሏል (ዘፍ 1:2፣ መዝ 33:6፣ 40:13፣ 139:7)::

የአብ ሥራ መምረጥ (1ጴጥ 1:2)፣ ዓለምን መውደድ (ዮሐ 3:16)፣ ወልድን ወደ ዓለም መላክ (ዮሐ 10:36፣ ገላ 4:4)፣ መልካም ስጦታን መስጠት (ያዕ 1:17)፣ ስለ ወልድ መመስከር (ዮሐ 5:31-33) ነው:: የወልድ ሥራ ጉልቶ የታየው መከራ በመቀበል (ማር 8:31)፣ የማዳንን ሥራ በመፈጸም (ዮሐ 6:38፣ ዕብ 10:5-7፣ 1ጴጥ 1:18)፣ ሁሉንም በሥልጣኑ ቃል መደገፍ (ዕብ 1:3) ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ደግሞ በተለይ አዲስ ልደት በመስጠት (ቲቶ 3:5)፣ ኃይልን በማልበስና (ሐዋ.1:8)፣ ጸጋን በመስጠት (1ቆሮ.12:7-11) እንዲሁም በመቀደስ (ገላ.5:22-23) ነው:: ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ የጸሎታችን አድራሻ ለአብ ነው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ እንጸልያለን:: (ዮሐ.14:4፣ ኤፌ.1:6፣ 2:18፣ 6:18)::

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በሥላሴ አካላት መካከል <u>የተግባር መከፋፈል</u> ያለ ሲሆን ይህ ልዩነት የመበላለጥ ሳይሆን በመለኮታዊ ሥራ ውስጥ ያለ የተግባር ትኩረት (distinctions but not inequalities) ነው:: እያንዳንዱ የሥላሴ አካል የሚያከናውነው መለኮታዊ ሥራ ፍጻሜ የሚያገኘው ሌሎችም የሥላሴ አካላት በዚያው ተግባር ላይ በሚያከናውኑት መለኮታዊ ሥራ ነው:: የእግዚአብሔር ሥራ የሥላሴ አካላት ለየብቻቸው የሚሠሯቸው የተለያዩ ሥራዎች አይደሉም:: ሥራው አንድ ሥራ ወይም አንድ ዕቅድ ሆኖ የሥላሴ አካላት ሁሉ የሚካፈሉበት እንጂ::



ስለዚህ በእግዚአብሔር (Godhead) አሠራር ውስጥ አብ የሚያቅድ፣ በወልድ በኩል በመንፈስ ቅዱስ የሚፈጽም ነው ማለት ይቻላል:: (Planner - Mediator - Applier) ሆኖም በአንድ የእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ሁሉም ሥላሴ ተካፋይ ናቸው:: ለምሳሌ በደህንነት ሥራ (ዮሐ 3:6፣ 16፣ ራእ 13:8)::

ስለዚህ በሥላሴ አካላት መካከል የማንነት ወይም የባሕርይ ልዩነት ወይም መበላለጥ የለም:: ሁሉም ፍጹም እኩል ናቸው:: አቶ መሠረት ስብሐት ለአብ ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ የቀደሙ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችን በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ:- «የሰው ባሕርዩ በአካል ቢካፈል፣ በየራሱ ልብ በየራሱ ቃል፣ በየራሱ እስትንፋስ ያለው ሆኖ፣ በየራሱ ልዩ ልዩ ሥራውን ይሠራል:: ሥላሴ ግን አካላቸው የተለየ ሲሆን፣ ባሕርያቸው ተከፍሎ የሌለበት አንድ ነው::»56

በሥላሴ መካከል ባለው ፍጹም የሆነ እኩልነት ውስጥ የተግባር ልዩነት ይስተዋላል:: ይህም አብ ወልድን ይልካል፤ ወልድ አብን በመታዘዝ ይላካል፤ መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ ይላካል:: ይህ በሥላሴ አካላት መካከል የሚታይ የራስን ፈቃድ መተው ወይም ለሌላው ማስገዛት57 በሥላሴ መካከል ለዘላለም ያለ ግንኙነት ነው58 (1ቆሮ 15:28)::

---

56 መሠረት ስብሐት ለአብ፣ ገጽ 280

57 ይህን በሥላሴ አካላት መካከል በፍቅር የራስን ፈቃድ መተው ወይም የራስን ፈቃድ ለሌላው ማስገዛት economic subordination ወይም subordination in role ይባላል:: ይህም "If we do not have ontological equality [equality in being], not all the persons are fully God. But if we do not have economic subordination [different activities or roles] then there is no inherent difference in the way the three persons relate to one another." Wayne Grudem. <u>Ibid</u>. 251. Care should be taken, however, to distinguish between economic subordination and "subordinationism" which holds the view that "the Son or Holy Spirit are inferior in being" to the Father.


58"The only distinctions between the members of the Trinity are in the ways they relate to each other and to the rest of creation. In those relationships they carry out roles that are appropriate to each person." <u>ibid.</u>

## 5.6.2 በሥላሴ መካከል ያለው ተዛምዶ

### ሀ. እያንዳንዱ የሥላሴ አካል ፍጹም አምላክ ነው

እያንዳንዱ የሥላሴ አካል የእግዚአብሔር ማንነትና ባሕርያት በሙላት አሉት:: የእግዚአብሔር ማንነት ለሥላሴ አካላት የተከፋፈለ አይደለም:: ነገር ግን አብ ፍጹም እግዚአብሔር ነው፣ ወልድ ፍጹም እግዚአብሔር ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም እግዚአብሔር ነው:: ይህ ማለት የሥላሴ አካላት ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተወሰነ ድርሻ ወይም ክፍል አላቸው ማለት አይደለም:: ይህን ለመረዳት የሚከተሉትን ሥዕሎች59 እንመልከት::

ሀ.1 የሥላሴ አካላት እያንዳንዳቸው ያላቸው ባሕርይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ክፍልፋይ አይደለም:: ለምሳሌ በሥዕል 2 እንደተመለከተው እያንዳንዱ የሥላሴ አካል የእግዚአብሔር 1/3ኛ አይደለም::





ሥዕል 2

ሀ.2 የእያንዳንዱ የሥላሴ አካላት መታወቂያዎች (personal distinctions) በእግዚአብሔር ማንነት ላይ የተጨመሩ ወይም የተደመሩ አይደሉም (ሥዕል 3)::


59 የሥላሴ ተዛምዶ ለማመልከት በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የተመለከቱት ሥዕሎች ከዋይኔ ግሩደም የተወሰዱ ናቸው:: ibid. pp.252- 255






ሥዕል 3

ሀ.3 የሥላሴ አካላት እንደ «ሞዳሊዝም» እምነት አንዱ እግዚአብሔር ከተለያዬ አቅጣጫ የሚታይበት መንገድ አይደለም (ሥዕል 4)::




ሥዕል 4

### ለ. እግዚአብሔር የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ድምር ውጤት አይደለም


አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በአንድነት ማለትም እግዚአብሔር (Godhead)60 የሦስቱ የሥላሴ አካላት ድምር ውጤት አይደለም:: እግዚአብሔር (Godhead) አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በየራሳቸው ካላቸው ማንነት ወይም ባሕርያት የላቀ ማንነት ወይም የበለጠ

60 The word Godhead - "is a modified form of Godhood. The "hood" is a suffix that means "state, condition, quality or character" as in manhood or statehood. Godhead, therfore, refers to the divine nature, to God in his fulness, his complete Godliness." Donald Cole' 1985, Basic Christian Faith. Westchester, ill, Crossway books, p.61

ባሕርያት የሉትም::61 እያንዳንዱ የሥላሴ አካል ፍጹም እግዚአብሔር በመሆኑ የእግዚአብሔር ማንነት ወይም ባሕርያት በሙላት / በፍጹምነት አሉት::

ሐ. <u>የእግዚአብሔር ማንነት/ ባሕርያት ለሥላሴ አካላት</u> <u>በእኩልነት አላቸው</u>

አንዱ የሥላሴ አካል ሌሎቹ የሥላሴ አካላት የሌላቸው ባሕርይ የሉትም:: አንዱ የሥላሴ አካል ከሌላው የሚለየው ከሌላው ይልቅ ባሉት ተጨማሪ ባሕርያት ወይም የባሕርይ ማነስ አይደለም::




ሥዕል 5

ሥዕል 5 በመጠኑም ቢሆን የእግዚአብሔርን በአንድነት ሦስትነት ለመረዳት ያግዛል:: ይህም:-

- እግዚአብሔር አንድ አምላክ መሆኑ በአንድ ሙሉ ክብ ተገልጿል::
- በዚህ አንድ እግዚአብሔር ሦስት አካላት (ሥላሴዎች) መኖራቸውን አብ (አ)፣ ወልድ (ወ)፣ መንፈስ ቅዱስ (መ) በሚለው ተመልክተናል::
- እያንዳንዱ የሥላሴ አካል እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ያልተከፈለ አንድነት አለው::62 ይህም:-

61 In this regard Bruce Milne quotes Augustine's argument that "in the Trinity two or three persons are not any greater than one of them." Bruce Milne, 1982, <u>Know the Truth</u>. Leicester: Inter Varsity Press, p.61

62Based on Jn 14:10-11, Leon Morris states that there is:- "mutual interpenetration of the Father and the Son. Each is "in" the other". Leon Morris, <u>The new International commentary on the New Testament: The</u>



- አብ:- በክቡ ውስጥ (አ) በሚለው የተመለከተ ሲሆን ይህ አብ ደግሞ በክቡ ውስጥ ያለው ሁሉ እርሱነቱን ይገልጻል::
- ወልድ:- በክቡ ውስጥ (ወ) በሚለው የተገለጸ ሆኖ ሳለ በክቡ ውሰጥ በ«አ» እና በ«መ» የተገለጸው ሁሉ የወልድን ማንነት ይገልጻል::
- መንፈስ ቅዱስ:- በክቡ ውስጥ (መ) በሚለው የተመለከተው ሆኖ እንዲሁም በቀሪው የክብ ክፍል ያለው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን እርሱነት ይገልጻል::

እንግዲህ በአጠቃላይ እግዚአብሔር አንድ አምላክ መሆኑን፣ ይህም አንድ አምላክ ከዘላለም እስከዘላለም በሥላሴ:- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተገልጾ የሚኖር መሆኑን አይተናል:: ይህ እምነት ለፍጥረታዊ ሰው አእምሮ የሚከብድና ሚስጢር የሆነም ነው:: ሰው ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በአእምሮው «ጨምቆ» ሊይዘው የሚችለውን እውቀትና «የሕፃንነትን ትምህርት» (ዕብ 5:12) ይፈልጋል:: ነገር ግን በእምነት ነገር ጤናማ የሆነ ክርስቲያን «ጠንካራ ምግብ» (ዕብ 6:14) በመብላት ወደ ፍጹምነት የሚያድግ በመሆኑ «በእግዚአብሔር እውቀት» (ቆላ 1:10) ማደግ ይጠበቅብናል::

<u>Gospel according to John</u>, 1971, Grand Rapids: WM.B. Eerdmans Publishing Co. p. 664.

# ምዕራፍ 6. የሥላሴ አካላት

## 6.1 አብ

እግዚአብሔር እኔነት ያለው ሕያው አምላክ በመሆኑ ከሰዎች ጋር ግንኙነትና ኅብረት ያደርጋል። ይህ ኅብረት ይበልጥ የሚገለጸው በአባትነቱ ነው። አብ ወይም አባት የሚለው መጠሪያ በሥላሴ አካላት መካከል ለአንደኛው ማለትም ለእግዚአብሔር አብ የሚውል ሲሆን በ4ቱ ወንጌሎች ብቻ 189 ጊዜ ያህል ተገልጾአል። ከዚህ ውስጥ 124 ጊዜ የሚሆነው የተገለጸው በዮሐንስ ወንጌል ነው። አብ ለእግዚአብሔር (Godhead) መጠሪያነት የዋለበትም ጊዜ አለ (ዕብ 12:9፣ ያዕ 1:17)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር አብ አባትነቱ በአራት ዓይነት የተዛምዶ ሁኔታዎች ተገልጾአል።

### 6.1.1 ወልድ ከአብ ጋር ስላለው ተዛምዶ

በእግዚአብሔር አብና ወልድ መካከል ያለው የአባትና ልጅነት ዝምድና ወልድ ከአብ ለዘላለም በመወለድ የሆነ የዘላለም ተዛምዶ ነው። ወልድ የአብ አንድያ ልጅ ነው (ዮሐ 3:16፣ 1ዮሐ 4:9)። በአብና በወልድ መካከል ያለው አባትና ልጅነት እንደ ፍጥረታት በመፈጠር፣ እንደ እስራኤል በቃል ኪዳን ወይም እንደ አማኝ በእምነት የሚገኝ አይደለም። ጌታ ኢየሱስ ስለ አብ ሲናገር ራሱን ከሌሎች ጋር በመደመር አብን «አባታችን» ወይም «አምላካችን» ብሎ አይጠራውም። በዮሐ 20:17 ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም አርጋለሁ፣ እንዲሁም «በሰማያት ያለው አባታችሁ» (ማቴ 7:11) ይላል። እግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ አባትና አምላክ (ኤፌ 1:3) የሚሆነው ለዘላለም በመካከላቸው ባለው የፍቅር ዝምድና በባሕርይው ነው። ሰው አብን ማወቅ የሚችለው ወልድ ሲገልጥለት ብቻ ነው (ማቴ 11:27)፣ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን የተናገረው በልጁ በኩል ነው (ዕብ 1:1-3)።

እንግዲህ በእግዚአብሔር አብና ወልድ መካከል ያለው አባትና ልጅነት በመፈጠር ወይንም እንደ ሰው በሥጋ ፈቃድ ሳይወለድ የእግዚአብሔር የበኩር ልጅ ተብሎ ተጠርቷል። ይህን በመጠኑ ለመረዳት የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ የነጐድጓድ ልጆች ተብለው እንደሚጠሩ በማር 3:17 እናነባለን። ይህም አባታቸው ነጐድጓድ የሚባል ሰው ነው ማለት ሳይሆን «ነጐድጓድ» የእነርሱን ባሕርይ ወይም ጠባይ እንደሚያመለክት

ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ልጅ ተብሎ መጠራቱ ከአብ ጋር ያለውን ዘላለማዊ ዝምድና ለማመልከት እንጂ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ የተፈጠረ ነው ለማለት አይደለም።

በዚህ በአብና በወልድ መካከል ባለው የዘላለም ተዛምዶ አብ ልጁን ልኮታል (ዮሐ 20፡21፣ ገላ 4፡4)፣ አትሞታል (ዮሐ 6፡27)፣ አክብሯል (ዮሐ 8፡57)፣ ወድዷል (ዮሐ.10፡17) አስተምሯል (ዮሐ 8፡28)፣ ሰምቶታል (ዮሐ 11፡41-42)፣ ከሙታን አስነስቶታል (ገላ 1፡1)፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ አድርጎታል (ኤፌ 1፡22)፣ ስለ ልጁ መስክሯል (ዮሐ 8፡180)፣ በልጁ ደስ ተሰኝቷል (ማቴ 3፡17፣ 17፡5)፣ ፍርድን ሁሉ ለልጁ ሰጥቶአል (ዮሐ 5፡22፣ 27)። ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ሲናገር እግዚአብሔር አብ ሁሉን የሚያውቅ (ማቴ 10፡29)፣ ቅዱስ (ዮሐ 17፡11)፣ ጻድቅ (ዮሐ 17፡25)፣ የሚወደድ (ዮሐ 3፡16፣ 17፡23)፣ መሆኑን ገልጿል።

## 6.1.2 <u>አብ የፍጥረት ሁሉ አባት</u>

እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪና አስጀማሪ በመሆኑ የፍጥረት አባት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለማያምኑ የአቴና ሰዎች ሲሰብክ እንደገለጸው «ሁላችን ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ ለፈጠረ አምላክ ዘመዶች63 ነን» ብሏል (ሐዋ 17፡29)። ኢሳይያስም እንዲሁ «አቤቱ፣ አንተ አባታችን ነህ፣ እኛ ጭቃ ነን አንተ ሠሪያችን ነህ፣ እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን» (ኢሳ 64፡8) ብሏል። በሌላም ቦታ እርሱ «የሰው ነፍስ ሁሉ አምላክ» (ዘኁ 16፡22) መሆኑ ተጽሮአል። ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ካለው የተፈጥሮ አባትነት (Creative Fatherhood) በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመዋጀት ወደሚገኝ ልጅነት (Adoptive Fatherhood) ዝምድና ወይም ኅብረት ሊሸጋገር የሚችለው በእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው።

## 6.1.3 <u>እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለው ዝምድና/</u> አብ የእስራኤል ሁሉ አባት

እግዚአብሔር የእስራኤል አባት ነው። እርሱ ሲናገር «እስራኤል የበኩር ልጄ ነው» (ዘጸ 4፡22)፣ «እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፣ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት» ይላል (ሆሴ 11፡1)። ነቢዩ ኢሳይያስም «አብርሃም ባያውቀን እስራኤልም ባይገነዘበን አንተ አባታችን ነህ፤ አቤቱ አንተ አባታችን ነህ፣ ስምህም ከዘላለም

63 (Offesprings/ children)



ታዳጊያችን ነው (ኢሳ 63፡16) ብሏል። ሚልክያስም እንዲሁ «ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን?» (ሚል 2፡10) ይላል።

በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለው የአባትና የልጅነት ዝምድና በቃል ኪዳን ወይም በመመረጥ የተገኘ ነው። ስለዚህ የአባትና ልጅነት ተዛመዶ ሙሴ ሲናገር «እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፣ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ነህና፣ በምድርም ላይ ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ እግዚአብሔር አንተን መርጦአልና ... » (ዘዳ 14፡1-2) ብሏል። እንዲሁም «...የገዛህ አባትህ አይደለምን?» ይላል (ዘዳ 32፡6)። ይህ አባት እንደ አባትነቱ ልጆቹ ያከብሩት ዘንድ ይወድዳል (ሚል 1፡6)።

## 6.1.4 <u>አብ የአማኞች ሁሉ አባት ነው</u>

አብ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግመኛ ለተወለዱት ሁሉ አባት ነው። የእግዚአብሔር ቃል በገላ 3፡26 «በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና» እንደሚል ወደዚህ ቤተሰብነት መግባት የሚቻለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው የማዳን ሥራ በማመን ብቻ ነው። ለእነዚህ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐ 1፡12)። የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ (1ዮሐ 3፡1)።

እግዚአብሔር በፈጣሪነቱ የሁሉም ሰው አባት ቢሆንም ሁሉም ሰው ግን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አይሆንም። የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆነ በመንፈስ የሚመራ፣ አባቱን አባ አባት ብሎ የሚጠራ፣ ልጅነቱን መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሱ የሚመሰክርለትና (ሮሜ 8፡14-16) በዚያው መንፈስ ወደ አብ መግባት የተፈቀደለት (ኤፌ 3፡18) ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ለማመን ስላልወደዱት ሲናገር «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያቢሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ» (ዮሐ 8፡44) እንዳለው እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም። የዚህ ዓለም አምላክ (2ቆሮ 4፡4) አሳባቸውን ያሳወረባቸው ናቸው።

በእግዚአብሔርና በአማኙ መካከል ያለው አባትና ልጅነት በሥጋ አባቶቻችን ከሆኑት ጋር ከሚኖረን ኅብረት ይልቅ የቀረበ ነው። የሰማዩን አባታችንን የሚያስፈልገንን ልንጠይቀው (ማቴ 6፡9-13)፣

በሚያስፈራ ሁኔታ ሁሉ ልንታመንበት (ማቴ 10:28-31) እንችላለን:: ይህንን አባታችንን እንድንመስለው ተጠርተናል (ማቴ 5:43-48)::

አብ ልጆቹን አስቀድሞ አውቋል (ሮሜ 8:29፣ 1ጴጥ 1:2)፣ መርጧል (ኤፌ 1:4) የልጁን መልክ እንዲመስሉ ወስኖአል (ሮሜ 8:29)፣ ይጠብቃቸዋል (ዮሐ 10:29፣ 17:11)፣ ያከብራቸዋል (ዮሐ 12:26)፣ ይባርካቸዋል (ኤፌ 1:3)፣ ይወድዳቸዋል (ዮሐ 14:21፣ 2ተሰ 2:16)፣ እውነትን ይገልጥላቸዋል (ማቴ 11:25፣ 16:17)፣ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል (ማቴ 6:11)፣ ዋጋን ይከፍላቸዋል (ማቴ 6:1)፣ ይቀጣቸዋል (ዕብ 12:5-10)፣ ፍሬ ሲያፈሩም ይከበራል (ዮሐ 15:8)::

## 6.2 ወልድ

ብዙ ሃይማኖቶች አንድ ሁሉን ቻይ አምላክ መኖሩን ያምናሉ:: ክርስትናን ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ[64] እንደሆነ በማወቅና በማመን ላይ የተመሠረተ እምነት መሆኑ ነው:: ይህ የክርስትና እምነት መሠረት ነው:: ክርስትና ክርስቶስ ነውና::

---

64 የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጹም አምላክ፣ ፈጹም ሰው መሆኑን የሚክድ እምነት በታሪክ ውስጥ በተለያየ መንገድ ተገልጿል::

1. Appolonarianism ክርስቶስ በከፊል ሰው በከፊል ደግሞ አምላክ ነው ብሎ የሚያምን ነው:: ክርስቶስ የሰው ሥጋ እና የመለኮት ነፍስ ነበረው ይላሉ:: ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ነፍስ ከሌለው የሰውን ስሜት ሊገነዘብ ባልቻለም ነበር:: «የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት» የተባለውም (ዕብ 2:18) እርሱ ፍጹም ሰው ስለሆነና የሰዎችን ስሜትና መከራ ስለሚረዳ ሩኅሩኅ ጌታ በመሆኑ ነው::

2. Ebionism ይህ አስተሳሰብ ደግሞ የክርስቶስን አምላክነት ይክዳል:: ይህ እምነት ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የሚያንስ ሰው ነው፣ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ የወረደው ለዚህ ነው ብሎ ያምናል::

3. Docetism ይህ አመለካከት ደግሞ የክርስቶስን ስብዕና (ሰው መሆን) የሚክድ ነው:: የሰው ሥጋ ክፉ ስለሆነ ኢየሱስ የሰው ሥጋ አልነበረውም፤ ነገር ግን ሰው የሚመስል መልአክ ነበር ይላሉ:: ይህ የእምነት ዓይነት በሐዋርያትም ዘመን ሳይኖር አልቀረም:: በ1ዮሐ 4:2-3 «... ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፣ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው» ይላል::



ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ለመሆኑ የሚከተሉትን ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማየት ይቻላል::

- ሀ) የዳዊት ልጅ (ማቴ 1:1፣ 16) የአዳም ልጅ (ሉቃ 3:38) ነው::
- ለ) ከእኛ እንደ አንዱ የሆነ፣ የመላእክትን ዘር ሳይሆን የአብርሃምን ዘር የያዘ (ዕብ 2:10-18) ነው::
- ሐ) ራሱን «ሰው» ብሎ የጠራ (ዮሐ 8:40) ነው::
- መ) ሰው መሆኑን ሌሎች የመሰከሩለት (ማር 6:1-6፣ ዮሐ 8:56) ነው::
- ሠ) በሰው መካከል የተመላለሰ እንደ ሰው የበላ፣ የጠጣ ነው::

ጌታ ኢየሱስ የሰውን ሥጋ ቢለብስም ምንም ኃጢአት አላደረገም:: እርሱ በድንግልና የተጸነሰና እስከ መውለጃዋ ቀን ድረስ ወንድ ሳታውቅ ከኖረች ከድንግል ማርያም የተወለደ ነው (ማቴ 1:18-25፣ ሉቃ 1:26-28):: እርሱ ፈጽሞ ኃጢአት አላደረገም (2ቆሮ 5:21፣ ዕብ 4:15፣ 7:26፣ 1ጴጥ 2:22፣ 3:18፣ 1ዮሐ 3:5):: ስለሆነም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጽም ሰው ነው::

ከዚህ ቀጥሎ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ፣ በባሕርዩ፣ በሥራውና አምልኮ በመቀበሉ ፍጹም አምላክ መሆኑን እናስረግጣለን::

### 6.2.1 <u>ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው (የመለኮትስም አለው)</u>

በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረውና ራሱም እግዚአብሔር የሆነው (ዮሐ 1:1) ሥጋ ሆነ (1:14):: ይህ ሥጋ የሆነው ቃል (Logos) መኖር የጀመረበት ጊዜ የለውም፣ እርሱ ከዘላለም ያለ እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ወደ ዓለም የላከው አንድያ ልጅ (3:17) ከሰማይ የመጣ (3:31) በሥጋና ደም ከመካፈሉም በፊት በልጅነት ለዘላለም ያለ ነው:: መጽሐፍ እንደሚል «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ... ልጁን ላከ» (ገላ 4:4):: እንዲሁም በሌላ ስፍራ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና» ይላል (1ዮሐ 4:9)::

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ስለመሆኑና የመለኮት ስም እንዳለው የሚያስተምረውን ቀጥሎ እንመለከታለን::

ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሖዋ (ያህዌ) ነው

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ 10:30)፣ «እኔን ያዬ አብን አይቶአል» (ዮሐ 14:9) በማለት ከአብ ጋር እኩል መሆኑንና በባሕርዩም አንድ መሆኑን ገልጿል:: በተለይ በዮሐ 8:58 የተናገረው ይህን እውነት ያጕላዋል:: ይህ ክፍል «እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው» ይላል:: «እኔ ነበርሁ (I was) አይደለም ያለው «እኔ አለሁ» (I am) እንጂ::

ይህ «እኔ አለሁ» (I am ወይም I am that I am) የጅሆቫ መጠሪያ እንደሆነ በዘጸ 3:14-15 ተገልጾ እናገኘዋለን:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ቃል ሲናገር ምን ማለቱ እንደሆነ የገባቸው አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ:: ጌታ ኢየሱስ አይሁድን ለምን ሊወግሩት እንደሚፈልጉ ሲጠይቃቸው «አይሁድም ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም ስለ ስድብ፣ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስላደረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት» (ዮሐ 10:33):: «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነው» (ዕብ 13:8)::

በተመሳሳይ ሁኔታ በዮሐ 5:18 እንደምናነበው ጌታ ኢየሱስ «ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ:- እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ:- ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር»:: ጊዜውም በደረሰ ጊዜ «እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፣ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓልና» (ዮሐ 19:7) የሚል ክስ አቀረቡበት:: ጌታ ኢየሱስ ግን «እራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓል» ብለው አይሁድ ያቀረቡበትን አላስተባበለም:: እንዲያውም «ሊቀ ካህናቱም አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንህ እንደሆነ እንድትነግረን በሕያው እግዚአብሔር አምልሃለሁ» ባለው ጊዜ (ማቴ 26:63-65) ጌታ ኢየሱስ የሰጠው መልስ «አንተ አልህ»65 ብሎ ነው:: በዚህም ሊቀ ካህናቱ ልብሱን እንደቀደደ እንመለከታለን::

65 «አንተ አልህ» የሚለው አገላለጽ አንተ እንዳልከው ነው ማለት ነው:: ይህ ሐረግ በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «አንተው ራስህ ብለኸዋል» ይላል:: እንዲሁም በNIV "yes it is as you say" ይላል::



ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ተብሎ የሚጠራ ለመሆኑ በመዝ 102:25-27 «አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ...» የተባለው እግዚአብሔር (ያህዌ) በዕብ 1:10-12 ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲውል «ጌታ ሆይ ... አንተ ግን አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም» ተብሏል:: ይህ በዕብ 1:10 ጌታ የተባለው በ1:2፣ 5 እና 8 «ልጅ» የተባለውና በ1:6 «በኩር» የተባለው የእግዚአብሔር መልአክት ሁሉ የሚሰግዱለት (1:6) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እንዲሁም (ዮሐ 20:28፣ ሐዋ 2:36፣ ሮሜ 10:9፣ ፊሊ. 2:11) ይመልከቱ::

ከዚህ በተጨማሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ እንደሆነ እርሱ ከሚጠራበት ስም ማገናዘብ ይቻላል:: ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ከ300 ዓመታት በፊት ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክኛ የተተረጐመው ብሉይ ኪዳን የሰባ ሊቃውንት ትርጉም (ሴፕቱዋጀንት መጽሐፍ) በዕብራይስጡ «ያህዌ» የሚለውን የእግዚአብሔር ስም እና «አዶናይ» የሚለውን የእግዚአብሔር የአክብሮት መጠሪያ በግሪክኛው «ኩሪዮስ» ወይም ጌታ ብሎ ነው የተረጐመው::66 ለምሳሌ በኢዩ 2:31-32 «የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» ይላል:: በሮሜ 10:9-13 ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ «ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ... አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፣ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው፤ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና» በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ መሆኑን ያስረዳል::67 እንዲሁም በ1ጴጥ 3:15 «ጌታን እርሱም ክርስቶስን በልባችሁ ቀድሱት» የሚለው በብሉይ ኪዳን «የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን ቀድሱት» ይላል (ኢሳ 8:13):: በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ስም ለመጠራቱ ሮሜ 9:5፣ ዮሐ.1:1፣ 18:20 እና 28፣ ቲቶ 2:13 ይመልከቱ::

66"When the Old Testament was translated into Greek in the 2nd and 3rd ceturies BC (the Septuagint), the sacred name of God, YHWH, usually rendered Yahweh or Jehovah, was translated by the Greek word kyrios (Lord)". Bruce Milne, Ibid.,p.129.

67"The significance of the title kyrios is found in the fact that Kyrios is the Greek translation of the tetragrammation YHWH, the covenant name for God himself in ruling over the world" George Eldon Ladd, 1993, A Theology of the New Testament (A revised edition), William B.Eprdmans publishing company, Grand Rapids, P.456.

በምድር ላይ ሰዎች ጌታ የሚሏቸው ብዙዎች ናቸው:: አማልክትና ሰዎች ጌታ ተብለው ተጠርተዋል:: ለክርስቲያን ግን « ... ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን» (2ቆሮ 8:5-6)::

ከዚህም ሌላ «ጌታ እግዚአብሔር መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል» (ኢሳ 40:10-11):: ዳዊትም «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝም የለም» ብሏል (መዝ 23:1) እንዲሁም «ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ የእስራኤል ጠባቂ ሆይ» (መዝ 86:1)፣ በሕዝቅኤልም በኩል «እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸዋለሁ፣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር» (ሕዝ 34:15):: ከዚህ በላይ እንዳየነው የበጎች እረኛ እግዚአብሔር (ጅሆቫ) ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር «መልካም እረኛ እኔ ነኝ... የራሴን በጎች አውቃለሁ...» (ዮሐ 10:11-16) ብሏል:: እንዲሁም በዕብ 13:20 «... ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን ...» ተብሏል:: ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ለሚያምኑት የነፍሳቸው እረኛና ጠባቂ ነው (1ጴጥ 2:25)::

ጅሆቫ አልፋና ኦሜጋ የመጀመሪያና የመጨረሻ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም አልፋና ኦሜጋ የመጀመሪያና የመጨረሻ ነው:: የእግዚአብሔር ቃል በኢሳ 44:6 «የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፣ የሚቤዠርም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፣ ከእኔም ሌላ አምላክ የለም» ይላል:: እንዲሁም ኢሳ 48:12 «ያዕቆብ ሆይ፣ የጠራሁህም እስራኤል ሆይ፣ ስማኝ እኔ ነኝ፣ እኔም ፊተኛው ነኝ፣ እኔም ኋለኛው ነኝ»፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ለሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር:- «ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል» በማለት መልእክት ያስተላልፋል (ራእ 2:8):: በተጨማሪም ጌታ ኢየሱስ «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ:: አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ብሏል (ራእ 22:12-13)::

## ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ አምላክ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ከሚያስተምረው መካከል የሚከተሉትን ጥቅሶች ይገኛሉ::

- «ክርስቶስ በሥጋ መጣ፣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው» (ሮሜ 9:5)::



- «... የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን ...» (ቲቶ 2:13)::
- «ስለ ልጁ ግን:- አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል ...» (ዕብ.1:8)::
- «በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ...» (2ጴጥ 1:1)::
- «ያለውና የነበረ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ» (ራእ 1:8)::

መጥምቁ ዮሐንስ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በፊት የመጣ «እነሆ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ» የተባለለት ሰው ነው (ማቴ 11:10፣ ሚል 3:1):: ይህ መንገድን የሚጠርገው ዮሐንስ በነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ሰው ነበር:- «የአዋጅ ነጋሪ ቃል:- የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፣ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ...» (ኢሳ 40:3-5):: በአዲስ ኪዳን እንደምናነበው ይህ መጥምቁ ዮሐንስ መንገድ ጠራጊ ሆኖ በምድረ በዳ የሚዞርለትና በነቢዩ ኢሳይያስ የሚመጣው አምላካችን እግዚአብሔር ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ መስክረዋል (ማቴ 3:3-11፣ ማር 3:1-11 ፣ ሉቃ 3:2-17)::

ከዚህም በተጨማሪ በሐዋ 20:28 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ ...» በማለት ሲናገር እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሆነው ማን ነው? በገዛ ራሱ ደም ቤተ ክርስቲያንን የዋጃት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ይገልጻል:: ማቴ 26:26-28፣ ማር 14:22-24፣ ሉቃ 22:19-21፣ 1ቆሮ 11:23-26 ይመልከቱ::

## ሐ. የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ነው

የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለማሳየት ሦስት ምሳሌዎችን እንመለከታለን::

## ሐ.1 መላእክት

ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔር መላእክት እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል:: «ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል» (ሉቃ 15:10) እንዲሁም ሉቃ 12:8-9፣ ዮሐ 1:51፣ ዕብ 1:16 ይመልከቱ:: እነዚሁ መላእክት ደግሞ የጌታ ኢየሱስ መላእክት እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል:: በማቴ 13:41 ላይ እንደምናነበው «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ...» ይላል:: እንዲሁም በማቴ 16:27 «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና» ተብሎ ተጽፏል:: ማቴ 25:31ንም ይመልከቱ::

## ሐ.2 ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ናት:: ሐዋርያው ጳውሎስ የቀደመ ኑሮውን ሲያስታውስ «የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ» ይላል (1ቆሮ 15:9):: ኤጲስ ቆጶስ «የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?» ተብሏል (1ጢሞ 3:5):: በተጨማሪ 1ቆሮ 2:2፣ 10:32፣ 11:22፣ ገላ 1:13፣ 1ጢሞ 3:15ን ይመልከቱ:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህች የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮስ ሲናገር «በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ» (ማቴ 16:18) አለው:: ሐዋርያው ጳውሎስም ለሮሜ ሰዎች በላከው መልዕክቱ «የክርስቶስ አብያተ ክርስትያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል» ይላል (ሮሜ 16:16):: ከዚህም ሌላ በሐዋ 20:28 ላይ የተገለጸው «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ» የሚለው ቃል ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መሆኗን፣ የዋጃት በገዛ ደሙ መሆኑንና፣ በገዛ ደሙ የዋጃትም ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል::

## ሐ.3 ወንጌል

ወንጌል እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የፈጸመው የማዳን ሥራ ነው:: ወንጌል ከዲያቢሎስና ከኃጢአት እሥራት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው የማዳን ሥራ አማካይነት በእምነት ነፃ የመውጣት የምሥራች ቃል ነው:: ይህ ወንጌል የእግዚአብሔር ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ «ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ» (ሮሜ 1:1)፣ ስለ አገልግሎቱ ሲናገር «ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ» ይላል (ሮሜ 15:16):: የኢየሱስ



ክርስቶስ ወንጌል መሆኑንም መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ይገልጻል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 9:12 ላይ «የክርስቶስን ወንጌል እንዳንከለክል በሁሉ እንታገሣለን» ይላል እንዲሁም በ1ተሰ 3:2 «... ከእኛ ጋርም አብሮ በክርስቶስ ወንጌል የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው» በማለት ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስም እንደሆነ ያስረዳል:: በተጨማሪ ማር 1:1፣ ሮሜ 1:9፣ 2ቆሮ 2:12፣ ገላ 1:7 ይመልከቱ::

## መ. ለአብ የተሰጠው ክብርና የመለኮት መግለጫ ሁሉ ለክርስቶስ ውሏል

በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ላይ በእኩልነት ተጠርተውና ለአብ የተሰጠው ክብርና የመለኮት መግለጫ ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስም ሆኖ እንመለከታለን:: ከዚህ ቀጥሎ ጥቂቶቹን እናያለን::

- ከእግዚአብሔር በቀር ቅዱስ የለም (1ሳሙ 2:2)፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ነው (ሉቃ 1:35፣ ሐዋ 3:14፣ ዕብ 7:26):: የፍጹምነት የመጨረሻው ደረጃ እግዚአብሔር ነው:: ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሰው እንዲሞሉ (ኤፌ 3:19)፣ ወደ ክርስቶስ ሙላት ልክ እንዲደርሱ (ኤፌ 4:13) መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል::
- የምንኖረው በእግዚአብሔር ፊት (ሐዋ.10:33)፣ በክርስቶስ ፊት (1ተሰ 2:19)፣ በእግዚአብሔርና በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ነው (2ጢሞ 4:1)::
- የሚያገለግል እግዚአብሔርን ያገለግላል (1ጢሞ 1:9)፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነው (ሮሜ 1:1፣ ገላ 1:10፣ ቆላ 3:23-24):: የምንታዘዘው እግዚአብሔርን ነው (ሐዋ 5:29)፣ ክርስቶስንም ነው (2ቆሮ 10:5፣ ኤፌ 6:5)::
- እግዚአብሔር ያጽናናል (2ቆሮ 1:3-5)፣ ክርስቶስ ያጽናናል (ፊሊ 2:1)፣ ክርስቶስና እግዚአብሔር አባታችን ያጽናኑናል (2ተሰ 2:16-17)::
- በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሰዎችን «ምስክሮቼ ናችሁ» ይላል (ኢሳ 43:10):: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ ሥልጣን ደቀ መዛሙርቱን «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» አላቸው (ሐዋ 1:8)::

- ክርስቲያኖች ቅዱስ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ (1ቆሮ 3:16-18)፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚኖርባቸው (2ቆሮ 13:5፣ ገላ 2:20)፣ መንፈስ ቅዱስ የሚኖርባቸው ናቸው (1ቆሮ 6:19-20)::

### 6.2.2 የመለኮት ባሕርይ አለው/ ከሥላሴ አንዱ አካል ነው

የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርያት ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስም ባሕርያት መሆናቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን::

#### ሀ. በሁሉ ቦታ መገኘት

እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ አለ:: እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ እንዳለ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በሁሉም ቦታ አለ:: ስለሆነም ከእያንዳንዳችን ጋር አለ፣ ይጠብቀናል፣ ይመራናል፣ በማናቸውም ቦታ ሆነን የምናደርገውን ሁሉ ያያል (ማቴ 18:20፣ 28:20 እና ኤፌ 1:22-23):: ለተጨማሪ ማስረጃዎች ዮሐ 3:13፣ ኤፌ 4:10፣ ራእ 3:20፣ 2ቆሮ 13:5፣ ገላ 2:20፣ ኤፌ 3:17፣ ቆላ.1:27 ይመልከቱ::

#### ለ. ሁሉን ማወቅ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ያውቃል:: እውቀቱ ፍጹም እውቀት ነው፣ «የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነው» (ቆላ 2:2-3):: እርሱ ኩላሊትንና ልብን ይመረምራል (ራእ 2:23) ተጨማሪ ጥቅሶች:- ዮሐ 6:64፣ 3:1፣11፣ 18:4፣ 19:28፣ 1ቆሮ 1:30::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጻፎች ልብ ምን እንዳለ ያውቃል (ማቴ 9:4):: የሰውን ልብ ሁሉ ያውቃል (ማር 2:8፣ ዮሐ 1:48፣ ሐዋ 1:24)፣ በየትኛው በባሕር ውስጥ ዓሣዎች በጥልቁ በኩል (ሉቃ 5:4-6)፣ በየትኛው አቅጣጫ (ዮሐ 21:6-11) እንዳሉ ያውቃል:: የትኛው ዓሣ ገንዘብ እንዳለበት ያውቃል68 (ማቴ 17:27)፣ አብን ያውቃል፣ (ዮሐ 17:25)፣ ሁሉን ነገር ያውቃል (ዮሐ 16:30)::

#### ሐ. ሁሉን ቻይነት

68 ይህ ክፍል የጌታ ኢየሱስን ሁሉን ማወቅ የሚያሳየውን ያህል ሁሉን ቻይነቱንም ያሳያል:: ዓሣ የት እንዳለ እንደሚያውቅ በዓሣ ውስጥ ገንዘብ እንዲኖር ማድረግም ይቻለዋል::



እግዚአብሔር ኤልሻዳይ (ሁሉን ቻይ) ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ ነው:: እግዚአብሔር የሚያደርገውን ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደርጋል (ዮሐ 5:19):: እርሱ መላእክትና ሥልጣናት ሁሉ የሚገዙለት (1ጴጥ 3:22)፣ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር የእርሱ የሆነ (ማቴ 28:18)፣ በአለቅነትና በሥልጣናት ላይ ራስ የሆነ (ቆላ 2:10፣ ኤፌ 1:19-21) ታላቅ አምላክ ነው::

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተፈጥሮ ላይ (ማር 4:35-41፣ ሉቃ 8:25)፣ አጋንንትን በማስወጣት (ማር 1:29-34)፣ ወደ እርሱ የሚመጡትን በማዳንና (ዕብ 7:25) የዘላለም ሕይወት በመስጠት (ዮሐ 17:2)፣ የተሰጠውን አደራ በመጠበቅ (2ጢሞ 1:2) ሁሉን ቻይነቱ ተገልጿል::

#### መ. ዘላለማዊነት

እግዚአብሔር የሌለበት ጊዜ አልነበረም፣ ወደፊትም እርሱ የማይኖርበት ጊዜ የለም:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መጀመሪያ የለውም መጨረሻም የለውም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል «እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፣ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» (1ዮሐ 5:20):: ተጨማሪ ጥቅሶች ኢሳ 9:6፣ ሚኪ 5:2፣ ዮሐ 1:1-2፣ ዮሐ 8:58፣ 17:5፣ ራእ 1:8፣ 22:13::

#### ሠ. አለመለወጥ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰብዓዊነቱ እንደ ሰው ሁሉ በአካሉ አድጓል (ሉቃ 2:52):: በመለኮትነቱ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ያው ነው:: የሚጨመር፣ የሚቀነስ ነገር የለውም:: አይለወጥም:: «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው» (ዕብ 13:8):: አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተነገረውን (መዝ 102:2) እግዚአብሔር አብ አንተ ግን አንተ ነህ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም» ያለው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው (ዕብ 1:12):: ስለዚህ እርሱ እስከዘላለም እንደሚወደን ልንታመንበት እና የገባውንም ተስፋ እንደሚጠብቅ እርግጠኛ ልንሆን እንችላለን::

#### ረ. ፍቅር

እግዚአብሔር እኛን ይወደናል (ሮሜ 5:8)፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ በመስጠቱ በዚህ ፍቅሩን ገልጿል (ገላ 2:20፣

1ዮሐ 3:16)። ፍቅሩ ሊገመት የማይችል፣ ከመታወቅ በላይ ነው (ኤፌ 3:18-19)።

ሰ. <u>ምሕረት</u>

እግዚአብሔር በርኅራኄ የተሞላ የምሕረት አምላክ ነው። ምሕረት ከአብ፣ ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ይገኛል። ኢየሱስ ክርስቶስ መሐሪ አምላክ ነው። እርሱ ለዘላለም ሕይወት የሚደርስ ምሕረት ያለው (ሮሜ 15:9፣ 1ቆሮ 7:25፣ 1ጢሞ 1:2፣ 2ጢሞ 1:2፣ ይሁዳ 21)፣ በሰማያት ያለፈ የሚምርና የታመነ ትልቅ ሊቀ ካህናት ነው። ጌታ ኢየሱስ ዙፋኑ የጸጋ ዙፋን ነው (ዕብ 4:14-16)። ጸጋ የሚሰጠው ከእግዚአብሔር አብና ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ቆላ 1:2፣6፣ ፊሊ 1:2፣ 4:23፣ 1ተሰ 1:1፣ 5:28)።

### 6.2.3 <u>የመለኮት ሥልጣን አለው /መለኮታዊ ሥራዎች ይሠራል</u>

ባለፉት ክፍሎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን በስሙና በባሕሪው ተመልክተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ አምላክ የሚሠራቸውን ተግባሮች የሚሠራ በመሆኑ በሥራውም አምላክነቱን እናስተውላለን።

ሀ. <u>መፍጠር፣ መንከባከብ፣ ሕይወትን መስጠት</u>

መፍጠር የእግዚአብሔር (ያህዌ) መለኮታዊ ሥራ ነው። እግዚአብሔር የመፍጠርን ሥራ ያከናወነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመፍጠር ሥራ ሲናገር «ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ይላል (ዮሐ 1:3)። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ነገር በሥልጣኑ ቃል ደግፎ (ጠብቆ፣ ተንከባክቦ) የሚይዝ አምላክ ነው (ዕብ 1:3)።

እግዚአብሔር ልጅ በሰጣት ጊዜ ሐና ስለ እግዚአብሔር ስትናገር «እግዚአብሔር ይገድላል ያድንማል» (1ሳሙ 2:6) በማለት ሕይወት የሚሰጥ ያህዌ ብቻ መሆኑን ገልጻለች። ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ስለሆነ ሕይወትን ይሰጣል። መጽሐፍ እንደሚል «... አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወት እንደሚሰጣቸው፣ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል» (ዮሐ 5:21)። እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሙታን ባስነሣበት ጊዜ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፣ የሚያምንብኝም ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል» ሲል እርሱ



ሕይወት የሚሰጥ አምላክ መሆኑን አስታውቋል (ዮሐ 11:25)። ኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል (ዮሐ 10:28)።

ለ. <u>ኃጢአትን ይቅር ማለት</u>

በማር.2:1-12 እንደምናነበው ሽባውን የተሸከሙ ሰዎች የቤቱን ጣሪያ ነድለው ሽባውን ካወረዱት በኋላ ጌታ ኢየሱስ ሽባውን «አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው።» ይህን በሰሙ ጊዜ ጻፎች ኢየሱስን «ስለምን እንዲህ ያለ ስድብ ይናገራል?» ብለው አሰቡ። በእርግጥም ኃጢአትን ይቅር ሊል የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑንና ኃጢአትን ለማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው እንዲያውቁ ሽባው ተነስቶ አልጋውን ተሸክሞ ወደ ቤቱ እንዲሄድ አዘዘው። ሽባውም ተነስቶ አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ።

ፈሪሳውያንን ያስቆጣቸውና ኢየሱስ ክርስቶስን በድንጋይ ሊወግሩት ያሰቡት ኃጢአትን ይቅር የሚል እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን በማወቃቸው ነው። ሆኖም ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን አላስተዋሉም።

ሐ. <u>ፍርድ</u>

አብርሃም «... የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» (ዘፍ 18:25) እንዳለው በቅን መፍረድ የእግዚአብሔር ሥልጣንና ባሕርዩ ነው። እንዲሁም በኢዩኤል 3:12 እንደምናነበው «... በዙሪያ ባሉ አሕዛብ ሁሉ ላይ እፈርድ ዘንድ በዚያ እቀመጣለሁና» ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ በማቴ 25:31-46 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፣ በጎችንና ፍየሎችን በመለየት በጻድቃንና በኃጥአን ላይ ይፈርዳል። እርሱ በሙታንና በሕያዋን ላይ ይፈርዳል (ሐዋ 10:42፣ 2ጢሞ 4:1)፣ የፍርድ ወንበር አለው (2ቆሮ 5:10፣ ሮሜ 14:10)፣ እርሱ የሚፈርድበት ቀን አለው (ሮሜ 2:16)። አብም «ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው» (ዮሐ 5:22)። እርሱ የምድር ነገሥታት ገዥ ነው (ራእ 1:5)። በመጨረሻው ዘመን በሰዎች ላይ መፍረድ በእግዚአብሔር ብቻ የሚከናወን መለኮታዊ ሥራ ነው። መንግሥት የእግዚአብሔር ነው (1ተሰ 2:12)፣ መንግሥት የኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ቆላ 1:13)፣ መንግሥት የክርስቶስና የእግዚአብሔር ነው (ኤፌ 5:5)።

### መ. ማዳን

እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ (አዳኝ) አምላክ ነው:: መድኀኒት እርሱ ብቻ ነው:: በቃሉም እንዲህ ይላል:- «እኔ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም» (ኢሳ 43:11)፣ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኀኒት ነኝ» (ኢሳ 45:21):: እግዚአብሔር ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው በሰዎች በኩል ያዳነ (የጠበቀ) አምላክ ሲሆን (ኢያ 10:6፣ መሳ 2:16፣18፣ 6:4) ከኃጢአት ማዳን ግን እግዚአብሔር ብቻ የሚያደርገው ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው:: እርሱ «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» (ማቴ 1:21)፣ እርሱ መድኃኒት ነው (ሐዋ 5:31፣ ፊሊ 3:20)፣ እርሱ ዓለምን የሚያድን (ዮሐ 3:17) ነው:: መዳን የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ሐዋ 4:12፣ ኤፌ 5:23፣ 1ተሰ 5:9):: እርሱ ከአመጽ ሁሉ የሚቤዠን አምላካችንና መድኃኒታችን ነው (ቲቶ 2:12-14)::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ የሚያስተምረውን በሠንጠረዥ 5 ባጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል::



ሠንጠረዥ 5
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮት ከአብ ጋር እኩል ነው

| | ስም /ሥራ | እግዚአብሔር አብ | እግዚአብሔር ወልድ |
|---|---|---|---|
| 1 | እግዚአብሔር/ አምላክ | ዘፍ 1፣ ዘዳ 6:4፣ መዝ 45:6, 7 | ኢሳ 7:14፣ 9:6፣ ቆላ 2:9፣ ኢሳ 1:1, 14፣ 20:28፣ ሮሜ 9:5፣ ቲቶ 2:13፣ ዕብ 1:8፣ ፊሊ 2:6፣ ዮሐ 14.9 |
| 2 | አልፋና ኦሜጋ | ኢሳ 41:4፣ 48:12፣ ራእ 1:8 | ራእ 1:17-18፣ 2:8፣ 22:12-16 |
| 3 | ጌታ | ኢሳ.45:23 | ማቴ 12:8፣ ሐዋ 7:59-60፣ 10:36፣ ሮሜ 10:12፣ 1ቆሮ 2:8፣ 12:3፣ ፊሊ. 2:10-11 |
| 4 | አዳኝ | ኢሳ 43:3, 11፣ 63:8፣ ሉቃ 1:47፣ 1ጢሞ 4:10 | ማቴ 1:21፣ ሉቃ 2:11፣ ዮሐ 1:29፣ 4:42፣ ቲቶ 2:13፣ ዕብ 5:9 |
| 5 | የሚቤዥ | መዝ 130:7-8፣ ኢሳ 48:17፣ 54:5፣ 63:9 | ሐዋ 20:28፣ ኤፌ 1:7፣ ዕብ 9:12 |
| 6 | ፈጣሪ | ዘፍ 1:1፣ ኢዮ 33:4፣ መዝ 95:5-6፣ 102:25-26፣ ኢሳ 40:28 | ዮሐ 1:2-3, 10፣ ቆላ 1:15-18፣ ዕብ 1:1-3, 10 |
| 7 | ሕይወትን የሚሰጥ | ዘፍ 2:7፣ ዘዳ 32:39፣ 1ሳሙ 2:6፣ መዝ 36:9 | ዮሐ 5:21፣ 10:28፣ 11:25 |
| 8 | ኃጢአትን ይቅር የሚል | ዘጸ 34:6-7፣ ነህ 9:17፣ ዳን 9:9፣ ዮሐ 4:2 | ማር 2:1-12፣ ሐዋ 26:18፣ ቆላ 2:13፣ 3:13 |

### 6.2.4 አምልኮና ክብር ይገባዋል

እግዚአብሔር ክብሩን ለማንም የማይሰጥ ቀናተኛ አምላክ ነው:: በኢሳይያስ በኩል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የተናገረው «እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ፣ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም» ብሎ ነው (ኢሳ.42:8):: እንዲሁም በሙሴ በኩል «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ...:: አትስገድላቸው አታምልካቸው ... እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» ብሏል (ዘጸ 20:3-6):: በአዲስ ኪዳን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ «ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም

ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና» በማለት ነው የመለሰለት (ማቴ 4:10):: ስለሆነም አምልኮና ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሰጥ መሆኑን እንረዳለን::

ሐዋርያው ጴጥሮስ «በጌታችን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ:: ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን አሜን» (2ጴጥ 3:18) በማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር የሚገባው አምላክ እንደሆነ ገልጿል:: የዕብራውያን ጸሐፊም «ለክርስቶስ ክብር ይሁን» (ዕብ 13:20-21) ይላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር ጌታ ነው (1ቆሮ 2:8፣ ያዕ 2:1)::

ጌታ ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ጴጥሮስን ወደታንኳ ባስገባውና ነፋሱም በተወ ጊዜ «በታንኳይቱም የነበሩት፣ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት» (ማቴ 14:33):: ከትንሣኤም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን «ኢየሱስ አገኛቸውና ደስ ይበላችሁ አላቸው:: እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት» (ሉቃ 24:52):: እንዲሁም ማቴ 2:2,8፣ 14:33፣ ማር 5:6፣ ዮሐ 9:38 ይመልከቱ:: ሐዋርያው ቶማስ የኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን መነሣት በመጠራጠሩ ጌታ ኢየሱስ የተወጋውን ጐኑንና እጆቹን ለቶማስ ካሳየው በኋላ «ጌታዬና አምላኬ» ብሎታል:: ጌታም ቶማስን የገሰጸው «ጌታዬና አምላኬ» ብሎ ስለጠራው ሳይሆን ስለመጠራጠሩ እንደሆነ ከክፍሉ እንገነዘባለን (ዮሐ 20:26-29)::

በሌላ በኩል ደግሞ መላእክት ወይም ሰዎች አምልኮ ወይም የመለኮትነት ክብር ሊሰጣቸው እንደማይገባ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል:: ቆርኔሌዎስ ለጴጥሮስ ከእግሩ በታች ወድቆ በሰገደለት ጊዜ «ጴጥሮስን ግን:- ተነሣ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው» (ሐዋ 10:26):: እንዲሁም መልአኩ ለሐዋርያው ዮሐንስ ራእዩን ካሳየው በኋላ «ይህን ባሳየኝ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ:: እርሱም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ:: ከአንተ ጋር ከወንድሞችህ ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፣ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ» ብሎ መስክሯል (ራእ 22:8-9)::

በግሪክኛ ኘሮስክኒያ (Proskyneia) በተሰኘው ቃል የሚገለጸውና ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርበው አምልኮ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ውሏል:: ሐዋርያው ዮሐንስ የሰማይ በር ተከፍቶ ሲያይ በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ሁሉንም ለሚገዛ ጌታ አምላክ «ይገባሃል» እያሉ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም እንደሰጡት ሁሉ (ራእ.4:8-11) ለታረደው በግ «ይገባሃል» እያሉ ክብርና ውዳሴም ምስጋናም ይሰጡታል፣ በፊቱም



ወድቀው ይሰግዱለታል (ራዕ.5:12-14):: አዎን፣ አሜን:: ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር፣ አምልኮ፣ ስግደት የሚገባው ታላቅ አምላክ ነው::

> «በሰማይና በምድር ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያሉ ሁሉ:- በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ:: አራቱም እንስሶች:- አሜን አሉ:- ሽማግሌዎቹም ወድቀው ሰገዱ» (ራእ 5:13-14)::

### 6.2.5 <u>የወልድን መለኮትነት የሚከዱ ክፍሎች የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች ትንታኔ</u>

የስህተት አስተማሪዎች አንዱ ስህተትነታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ወይም ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ ነጥለው በማውጣት ለሀሳባቸው የሚስማማ ትርጉም መስጠታቸው ነው:: ይህ አሠራር ዲያቢሎስ ጌታ ኢየሱስን የፈተነበት ጥበቡ ነው:: የጌታ ኢየሱስ አመላለስ ግን በመጽሐፍት ውስጥ የተጻፉ ሌሎች ጥቅሶችን ወይም ደግሞዎችን በመጥቀስ «የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ» በማገናዘብ ነበር:: ከዚህ ጌታ ኢየሱስ ለዲያቢሎስ ከመለሰለት አመላለስ በመነሳት የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም ሙሉውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማገናዘብን <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞዎች</u> ብሎ ሊጠራቸው ወዷል::

#### <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞዎች</u>

ዲያቢሎስ ጌታ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ሲፈትነው በሦስቱም ጊዜያት «ተጽፎአል»ና ስለዚህ አድርገው እያለ ነው (ማቴ 4:3-10):: የተጻፈ ከሆነ ጌታ ኢየሱስ ሊፈጽመው ይጠበቃልና::

ጌታ ኢየሱስ የመጣው የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ ነው:: መጽሐፍ «ከተጻፈው አትለፍ» (1ቆሮ 4:6) ይላልና የተጻፈውን ያደርግ ዘንድ ይገባል:: የዲያቢሎስ አሳችነቱ ግን «ከፊል እውነት» ከሆነው ተነስቶ «ሙሉ እውነት»[69] ለማድረግ መሞከሩ ነው::

---

69 በዚህ መጽሐፍ ሙሉ እውነት የሚለው የተተረጎመው አንደኛውን አጉልቶ ለማሳየት ሲባል ሌላውን መቃወም ወይም እንደሌለ መቁጠር አለመሆኑን ለማመልከት ነው:: በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል እውነት በመሆኑ «ከፊል

ፈታኝ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የፈተነበትን ሁለተኛውን ፈተና እስቲ እንመልከት:: ፈተናው «መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ወደ ታች ራስህን ወርውር» (ማቴ 4:6) የሚል ነው:: ዲያቢሎስ የጠቀሰው ቃል በብሉይ ኪዳን መዝ 91:11-12 የሚገኝ ቃል ነው:: ነገር ግን የዲያቢሎስ አሳችነት በሁለት መንገድ ይገለጻል::

የመጀመሪያው አሳችነቱ ይህን የብሉይ ኪዳን ጥቅስ የጠቀሰው በዚያ ምዕራፍ ማለትም በመዝ 91 ካለው መልእክት ወይም (አውድ) ውጪ መሆኑ ነው:: ምዕራፉ እጅግ አስፈሪና ከባድ በሆኑ ሁኔታዎች ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይህ የእግዚአብሔር ጥበቃ ግን ራሱን በችግርና በአደጋ ውስጥ ስለሚያስገባ ሰው አይደለም የሚናገረው:: ራሱን በችግር ውስጥ ዱሎ እግዚአብሔርን «አድነኝ» የሚል እግዚአብሔርን የሚፈታተን ሰው ነው::

ሁለተኛውና ዋናው የዲያቢሎስ አሳችነቱ ደግሞ አንድን ጥቅስ ከሌላው «የእግዚአብሔር ምክር ሁሉ» (ሐዋ 20:27) ነጥሎ ማውጣቱና ለራሱ ዓላማ እንዲውል አድርጎ መጥቀሱ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዲያቢሎስ መልስ ሲሰጠው የጠቀሰው በዘዳ 6:16 የሚገኘውን «አምላካችሁን እግዚአብሔርን አትፈታተኑት» የሚለውን ቃል ነው:: እግዚአብሔርን መፈታተን ማለት በእርሱ ላይ ማጉረምረም፣ የእርሱን ምሕረት፣ ስጦታ (ሰጪነቱን)ና መልካምነት መጠራጠር ወይም ሁሉን ቻይነቱን መጠየቅ/ መፈታተን ነው::

የጌታን መልስ ልብ ብለን ስናስተውለው «ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ70 ተጽፎአል» የሚል ነው:: በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሚገኘው «ደግሞ» የተሰኘው ጥሬ ቃል ከምንባቡና በአጠቃላይ

---

እውነት» ሊባል የሚችል አይኖርም:: ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የሚስማማ እንጂ የማይቃረን መጽሐፍ ነው::

70 በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ማቴ 4:7 እንደዚህ ይነበባል:- «ኢየሱስም:- እንደዚሁም በመጻሕፍት 'እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል' ብሎ መለሰለት:: ይህ ጥቅስ በKJV "Jesus said unto him, it is written again Thou shall not tempt the Lord thy God" ይላል:: ሌሎች ብዙ ትርጉሞችም "The scriptures also says ..." ይላሉ:: ይህ alsc ወይም again የሚለው ቃል አገባቡ «እንደዚሁም»፣ «ደግሞ» (on the other hand, further more) ማለት ነው::



ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት አንጻር ትልቅ ትምህርት አለው:: ከዚህ የጌታ አመላለስ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን እናስተውላለን::

አንደኛው:- ፈታኝ ከመዝሙረ ዳዊት ጠቅሶ የተናገረውን ጌታ ኢየሱስ እንዲህ የሚል ቃል የለም በሚል ዓይነት አመላለስ አልመለሰለትም:: የተጠቀሰው ከብሉይ ኪዳን መሆኑ ቢታወቅም ዲያቢሎስ «የብርሃን መልአክ» መስሎ እንዲቀርብ ይታወቃል::

ሁለተኛው:- ቁልፍ ነጥብ «ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል» የሚለው አመላለስ ነው:: ዲያቢሎስ የጠቀሰው ቃል በመጽሐፍ ውስጥ ቢኖርም ጌታ የሰጠው መልስ የሚያመለክተው አብሮ መታየት የሚገባው ሌላ ቃል በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ መኖሩንና ቃሉም የሚደጋገፍ እንጂ እርስ በርስ የማይቃረን መሆኑን ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድ ክፍል/ ቦታ የተጻፈን ቃል በመውሰድ በዚሁ መጽሐፍ በሌላ ክፍል/ ቦታ ከተጻፈ ቃል ጋር እንደሚቃረን አድርጐ መቁጠር የመጽሐፉን ዋና መልእክትና የደራሲውን ማንነት አለመረዳት ይሆናል:: የእግዚአብሔር «እስትንፋሳዊ ቃል» የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ አይቃረንምና::

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ «ደግሞ ተብሎ ተጽፏል» ሲል ይህ ደግሞ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት «ያኛው» ጥቅስና «ይኼኛው» ጥቅስ በአንድ ላይ ሊወሰዱ እንደሚገባ የሚያመለክት ቃል ነው::

እንግዲህ የዲያቢሎስ ፈተና ዋና ሀሳብ ኢየሱስ ክርስቶስ «የእግዚአብሔር ልጅ» መሆኑን ለመካድ ነው:: ዛሬም ቢሆን የስህተት ትምህርቶች ስህተትነት/ ዋና ችግር ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መካዳቸው ነው:: ዲያቢሎስ በሁለቱ ፈተናዎቹ ጌታ ኢየሱስን የጠየቀው «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ» (ማቴ 4:3-6) በማለት እንደነበር ሁሉ ዛሬም ይህን ጥያቄ የሚጠይቁ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅነቱን የሚክዱ ብዙዎች ናቸው:: ይሁን እንጂ በተለይ መጽሐፍ ቅዱስን እየጠቀሱ እግዚአብሔር በሦስት አካል ተገልጦ መኖሩን የሚክዱ እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የማያምኑ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞዎችን ሊያስተውሉ ይገባቸዋል::

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትንና እግዚአብሔር በሦስት አካል ተገልጾ እንደሚኖር (ሥላሴን) የሚክዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የሚጠቅሷቸውን ጥቅሶችና ለእነዚህ በቂ መልስ የሚሆኑ «ደግምዎችን» እንደሚከተለው ባጭሩ እንመለከታለን::

ሀ. «<u>ከፍጥረት ሁሉ በኩር ነው</u>» (ቆላ.1:15-16)

ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው ወይም ፍጡር መሆኑን ነው ብለው የሚተረጉሙ አሉ:: የዚህን ጥቅስ ትክክለኛ ፍቺ ለመረዳት አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «በኩር» የሚለው ቃል ያለውን ትርጉም መገንዘብ ያሻል::

«በኩር» የሚለው ቃል ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በተያያዘ ከአንድ ጊዜ በላይ የተጠቀሰ ሲሆን የቃሉ አጠቃቀም እንደሚከተለው ነው::

1. «<u>የመውለጃዋ ወራት ደረሰ የበኩር ልጇንም ወለደች...</u>» (ሉቃ 2:7):: ይህ ጥቅስ ማርያም በድንግልናዋ የመጀመሪያ ልጅዋን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደወለደችና ከዚያ በፊት ልጅ አለመውለድዋን ያመለክታል::

2. «<u>ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ ...</u>» (ሮሜ 8:29):: ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ወንድሞች» በተባሉት ማለትም በእግዚአብሔር ቤተሰቦች መካከል ከፍ ያለ፣ የተከበረ መሆኑን ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ሞትና ትንሣኤ አዲስ ፍጥረት ከሆኑትና ወንድሞች ተብለው ከሚጠሩት ሁሉ (ዕብ 2:10-13) በኩር የሆነ ወይም የተከበረና አለቃ ነው:: በሌላ ክፍል ደግሞ በኩር የሚለውን ቃል አጠቃቀም ስንመለከት ለምሳሌ ስለ ዳዊት በመዝ 89:19-27:-

> ... ከሕዝቤ የተመረጠውን ከፍ ከፍ አደረግሁ
> ባሪያዬንም ዳዊትን አገኘሁት፣
> ... እርሱም አንተ አባቴ ነህ፣
> አምላኬም የመድኃኒቴም መጠጊያ ይላል::
> እኔ ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ፣
> ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል

የሚል እናነባለን::

ንጉሡ ዳዊት እግዚአብሔር የፈጠረው የመጀመሪያ ሰው አልነበረም፣ ለእሴይም እንኳ የመጨረሻ ልጅ ነው (1ሳሙ 16:6-11):: ነገር ግን



እግዚአብሔር ዳዊትን «በኩሬ አደርገዋለሁ»፣ ሲል ከሌሎች እርሱን ከሚመስሉ ነገሥታት ሳይቀር በክብር ከፍ ያለና ቀዳሚ ይሆናል የሚለውን ትርጉም ያስገኛል::

3. «<u>... ከሙታን በኩር ... ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ...</u>» (ራእ 1:5)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ለመነሣት የመጀመሪያው ሰው አልነበረም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው የአንዲት ሴት ልጅ (1ነገ 17:22)፣ የሱነማዊቷ ልጅ (2ነገ 4:35)፣ የመኮንኑ ብላቴና (ማቴ 27:52)፣ የአንዲት ሴት ልጅ (ሉቃ 7:15)፣ አልአዛር (ዮሐ 11:44)፣ ብዙ ቅዱሳን (ማቴ 27:52)፣ ዶርቃ (ሐዋ 9:40)፣ እነዚህ ሁሉ ከሞት ተነስተዋል:: ነገር ግን ሁሉም ተመልሰው የሚሞቱ (የሞቱ) ናቸው::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከሞት ከተነሣ በኋላ ተመልሶ አይሞትም፣ እርሱ ለዘላለም ሕያው ነው:: እርሱ ሙታንን የሚያስነሣ ነው (ዮሐ 5:28-29):: እንግዲህ ጌታ ከሙታን በኩር የተሰኘው እርሱ ተመልሶ የማይሞት በመሆኑና ወንድሞቹ ተብለው ከሚጠሩትና በትንሣኤ ጊዜ ከሞት በመነሣት ተመልሰው ከማይሞቱት ሁሉ ቀድሞ የተነሣ የመጀመሪያ፣ ቀዳሚ ስለሆነ ነው::

በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ በኩር የሚለው ቃል ሁልጊዜ በመፈጠር ወይም በመወለድ የመጀመሪያ መሆንን እንደማያመለክት የሚከተለውን ማስረጃ እናገኛለን::

- እስራኤል የእግዚአብሔር በኩር ልጅ ተብሏል (ዘጸ 4:22፣ ኤር 31:9)::
- በ1ዜና 5:1 ላይ «የእስራኤል በኩር የሮቤል ልጆች እነዚህ ናቸው:: እርሱ የበኩር ልጅ ነበረ ነገር ግን ... ብኩርናው ለእስራኤል ልጅ ለዮሴፍ ልጆች ተሰጠ፣ ...» ይላል::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሆነና (ፊልጵ 2:6)፣ እራሱ እግዚአብሔር የሆነ ነው:: እርሱ ከሰማይ የመጣ እንጂ ከመሬት የተፈጠረ አይደለም (1ቆሮ 15:47)::

በኩር (First Born) የሚለው ቃል ኘሮቶቶካስ (Prototokas) ከተሰኘ የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ትርጉሙም አለቃ፣ የበላይ፣ ቀዳሚ፣ ከፍ ያለ (Chief, first in importance, first, most leading) ማለት ነው:: መጀመሪያ የተፈጠረ ለማለት የግሪኩ ቃል ኘሮቶክቲስቶስ (Protoktistos) ነው:: በቆላ 1:15-16 ለጌታ

የዋለው ቃል ኘሮቶቶካስ የሚለው በመሆኑ ጌታ ኢየሱስ ፍጡር ላለመሆኑ ሌላው ማስረጃ ነው::

ከዚህም በላይ በዚያው በቆላ 1:16 «በእርሱ ተፈጥረዋልና ... ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋል» የሚለው ቃል ክርስቶስ የሁሉ ፈጣሪ መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን በ1:18 ላይ ደግሞ «ራስ» መሆኑና «በኩር» መሆኑ «በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ» እንደሆነ ይገለጻል::

እንግዲህ ክርስቶስ ኢየሱስ ከፍጥረት ሁሉ በኩር ነው የሚለው ቃል የሚያመለክተው እርሱ ከፍጥረት ሁሉ በፊት ያለ መሆኑን፣ የፍጥረት ሁሉ አለቃ ወይም የበላይ መሆኑንና በክብር ከፍ ያለ መሆኑን እንጂ እርሱ በመፈጠር መጀመሪያ መሆኑን አይደለም:: ኢየሱስ ክርስቶስ «ከዘላለም እስከ ዘላለም» የሚኖር (ራእ 5:13)፣ የዘላለም አምላክ (ዮሐ 5:20) ነው:: አሜን::

ለ. <u>«... አብ ከእኔ ይበልጣልና ...»</u> (ዮሐ 14:28)

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት መቀበል የማይፈልጉ ወገኖች ይህን ጥቅስ በመጥቀስ «ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ያንሳል ስለዚህ አምላክ አይደለም» የሚል ትምህርት ይመሠርታሉ:: ነገር ግን ከክፍሉ እንደምንረዳው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አብ ከእኔ ይበልጣልና፣ ያለበት ምክንያት ጌታ ከእነርሱ በመለየቱ ልባቸው እንዳይታወክ (14:11) ይልቁን እርሱ ወደ አብ እየሄደ በመሆኑ ደስ እንዲላቸው ነው:: ይህ ደግሞ የበላይና የበታችነትን አያመለክትም::

ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ የባሪያን መልክ በመያዝ ክብሩን ትቷል:: ክብሩንም ስለተወና የባሪያን መልክ ስለያዘ ራሱን ዝቅ አድርጓል:: ከዚህም የተነሳ በሥጋው ወራት ማለትም በምድራዊው ኑሮው ለጊዜው ከአብ አንሷል:: ሆኖም አምላክነቱን አልተወም:: በምድር እያለ «እኔን ያየ አብን አይቷል» (ዮሐ 14:9) «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ 10:30) ብሏልና:: እንዲሁም በቆላ 2:9 ላይ «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና» ይላል:: እርሱ በሥጋው ወራት የመለኮትነት ክብሩን በፈቃዱ ቢተውም በመለኮትነት ሙሉ ነው::

ቀደም ሲል በክፍል 6.2.1 እንደተመለከትነው:- ብዙ ጊዜ ፈሪሳውያንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያነሳሳቸውና ሊወግሩት የፈለጉት እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን በማስተማሩና ይህንንም በእግዚአብሔር ላይ



ስድብ እንደ መናገር አድርገው ስለቆጠሩት ነው:: በዮሐ 5:58 «ኢየሱስም፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው»:: ጌታ ኢየሱስ «<u>እኔ አለሁ</u>» ሲል ከአብርሃም ይልቅ በዕድሜ የሸመገለ ወይም ብዙ ዓመት በምድር ላይ የኖረ መሆኑን ለመግለጽ አልነበረም:: «ገና ሃምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን» (ዮሐ 8:56) ብለውታል:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ «እኔ አለሁ» ሲል እግዚአብሔር ለሙሴ በዘጸ 3:14 ላይ የገለጠለትን «I am» የሚለውን ስሙን ለእራሱም መጠቀሙ ነው:: «እኔ ነበርሁ» አላለም «እኔ አለሁ» እንጂ:: ይህን በሰሙ ጊዜ አይሁድ «ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ» (ዮሐ 8:19):: በሙሴ ሕግ ሰው «የእግዚአብሔርን ስም በሰደበ ጊዜ ይገደል» ይላልና (ዘሌ 24:16)::

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «አብ ከእኔ ይበልጣል» ሲል እርሱ ክብሩን ትቶና ራሱን ዝቅ አድርጎ በመጣበትና ምድር ላይ በነበረበት ሁኔታ በሙሉ ክብሩ ከሚኖረው ከአብ ክብር ጋር ሲወዳደር ዝቅ ያለ መሆኑን ማመልከቱ ነው::71

ሐ. <u>«የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር»</u> (1ቆሮ 11:3)

ይህን ጥቅስ ለመገንዘብ በወንድና ሴት መካከል ያለውን እኩልነት ማየት ይገባል:: ወንድና ሴት ሁለቱም በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩ ናቸው:: ሴት ለወንድ ከአጥንቱ የሆነች አጥንት፣ ከሥጋው የሆነች ሥጋ ናት:: ሁለቱም ከምድር አፈር የተበጁ ናቸው:: ሁለቱም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የዘላለም ሕይወት ወራሾች ናቸው፣ በመካከላቸውም ልዩነት የለም (ገላ.2:28):: ስለዚህ «የሴትም ራስ ወንድ» የሚለው አገላለጽ በተመሳሳዮችና በእኩያዎች መካከል ያለ የግንኙነት ወይም የተዛምዶ ሁኔታ ነው:: ሁለቱም እኩል ሆነው ሳለ በትዳር ውስጥ ደግሞ ሚስት ለባል እንድትገዛ የጌታ ትዕዛዝ ነው:: ይህ መገዛት የሚያሳየው የበላይና የበታችነት አይደለም፣ በመካከላቸው የሚኖረውን የግንኙነት ወይም የአኗኗር ሥርዓትን እንጂ:: በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮት ከአብ ጋር እኩል ሆኖ ሳለ የእግዚአብሔርን የደህንነት እቅድ ለመፈጸም ራሱን ለእግዚአብሔር

71 Erickson also argues that Jn 14:28 "must be seen in the light of the son's functional subordination during the incarnation. "In his earthly ministry Jesus was dependent upon the Father, particularly for the exercise of his divine attributes." Milard Erickson, <u>Ibid.</u>

ማስገዛት ነበረበት፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት የደህንነት ሥራ የሚፈጸመው በዚህ መልክ በመሆኑ ነው፡፡

መ. «... ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል (1ቆሮ 15:28)

በልጅና በአባት መካከል ያለው ግንኙነት ምንም እንኳን ሁለቱም አንድ ማንነት ወይም ባሕርይ (Substance/ essence) ቢኖራቸውም ልጅ ለአባት ይታዘዛል፣ ይገዛል፣ ፈቃዱን ያገለግላል፡፡ ይህ መብለጥንና ማነስን አያመለክትም፡፡

ቀደም ሲል እንዳየነው በሙሴ ሕግ «የእግዚአብሔርን ስም የሰደበ ፈጽሞ ይገደል ... የእግዚአብሔርን ሕግ በሰደበ ጊዜ ይገደል» (ዘሌ 24:16) ይላልና ጌታ ኢየሱስን «... ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ» ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር» (ዮሐ 5:18) ተብሎ ተጽፏል፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር «ኃያል አምላክ» እንደተባለ ሁሉ (ኢሳ 10:21፣ ኤር 32:18) ኢየሱስ ክርስቶስም ኃያል አምላክ፣ ሥልጣን ሁሉ የእርሱ የሆነ ነው (ማቴ 28:18)፡፡

ስለዚህ በዚህም ክፍል ቢሆን የሚታየው የበላይነትና የበታችነት አይደለም፡፡ ጌታ ኢየሱስ በፍጻሜው መንግሥትን ለአብ ሲሰጥ የዚያን ጊዜ በእግዚአብሔርነቱ፣ ከአብ ጋር አንድ በመሆኑ፣ የሥላሴ ሁለተኛው አካል በመሆኑ ይገዛል፡፡

ሠ. «ልጁም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም» (ማር 13:32)

ጌታ ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር የመጣው የባሪያን መልክ ይዞ፣ ራሱን ፈጽሞ ለአብ በማስገዛት ነው፡፡ እርሱ ፍጹም አምላክ ሆኖ ሳለ ፍጹም ሰው ደግሞ ሆነ፡፡ በዮሐ 10:33 እንደምናነበው በእርሱ ዘመን የነበሩት አይሁድ «ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፣ ስለስድብ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት» ይላል፡፡ ይህ የሆነው ጌታ ኢየሱስ እርሱ አምላክ እንደሆነ ለአይሁድ ስለነገራቸው ነው፡፡



በዚህ በማር 13:22 በጥቅም ላይ የዋለው «ማወቅ» ወይም «የሚያውቅ» የሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች እንደሚገልፁት «አንድን ነገር ማሳወቅ ወይም ማወጅ» የሚል ትርጉም እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ ይህ ማለት ጥቅሱ የሚያመለክተው ጌታ ወደ ምድር የመጣበት ዓላማ ሁለተኛ የሚመጣበትን ጊዜ ለማሳወቅ ወይም ቀኑን ለመናገር አለመሆኑን ነው፡፡ የእርሱ መመለስ በሰው ዘንድ የሚታወቅ አይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የማወቅ ችሎታ የለውም የሚል ትርጉም አይሰጥም፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የሚመለሰውም ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ በዚህ ክፍል የሚያስተምረው ሀሳብ ስለ እርሱ መመለስ የሚያስፈልገው ዋና ነገር ራስን አዘጋጅቶ መጠባበቅ እንጂ ዘመን ቆጠራ አለመሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት አስመልክቶ በሥላሴ ትምህርት ላይ የተሳሳቱ አስተሳሰቦች የሚመነጩት ፊሊ 2:6-11 ስለ ጌታ ኢየሱስ የሚያስተምረውን በውል ባለመገንዘብ ነው፡፡ ይህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት መልክ የእግዚአብሔር መልክ (በቁ.6) እና የባሪያ መልክ (በቁ.7) እንዳለው ያመለክታል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ከአብ እንደሚያንስ የሚመስልበት ሁኔታ ሁሉ ጌታ በሥጋ በሰው መካከል የተገኘበትና ራሱን ያዋረደበት ዘመን ነው፡፡ መሠረታዊ ችግር መንፈሳዊውን ነገር በምድራዊ እውቀት ብቻ ለመረዳት መጣራቸው ነው፡፡ የዓለም ጥበብ ደግሞ በእግዚአብሔር የተናቀ ነው፡፡

ከአዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በምድር ላይ የተለያየ ቀለም፣ ቋንቋ፣ ባሕል ያለው በተለያዩ አሕጉራትና በታዎች 40 ቢሊዮን ያህል ሕዝብ እንደኖረ ይገመታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጸው የእያንዳንዱ ሰው የዘላለም ኑሮው የሚወሰነው ግን ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለው እውነተኛ ግንኙነት ላይ ነው፡፡

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ፣ ፍጹም ሰው መሆኑን ነው፡፡ የታመነው ምስክር የሆነው ቃሉም አሜን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ስለራሱ የሚመሰክረው እርሱ ፍጹም አምላክ እንደሆነና ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ ያለው መሆኑን እንዲሁም ፍጹም ሰው መሆኑን ነው፡፡ ምስክርነቱ ደግሞ እውነት እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ስለዚህ ፍጥረት ሁሉ የታመነውን ምስክር ኢየሱስን ይስማ፡፡

## 6.3 መንፈስ ቅዱስ

ይህ ክፍል ከሥላሴዎች አንዱ ስለሆነው ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት ይገልጻል:: መንፈስ ቅዱስ እኔነት ያለው፣ ያህዌ መሆኑንና ስለ ስሞቹና መግለጫዎቹ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

### 6.3.1 መንፈሱ ቅዱስ እኔነት አለው

መንፈስ ቅዱስ የእኔነት ወይም የአካል (Personality) መግለጫዎች የሆኑት ፈቃድ፣ እውቀት፣ ስሜት አሉት:: እርሱ የሚናገር ፈቃዱንና ስሜቱን የሚገልጽ አምላክ ነው:: ኃይል (Influence) የሆነ ፈቃድ፣ ዕውቀት፣ ስሜት የለውም:: ስለዚህ እርሱ (He) እንጂ በግዑዝ አጠራር (It) አይባልም:: መንፈስ ቅዱስ እንደ ኤሌክትሪክ ወይም ነፋስ ኃይልን የሚሰጥ ግዑዝ አካል ሳይሆን እኔነት ያለው ሕያው አምላክ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ኃይልን የሚሰጥ አምላክ ነው (ሐዋ 1:8፣ መሳ 14:19፣ 1ሳሙ 10:10፣ ሉቃ 4:14፣ ሮሜ 15:13)::

#### ሀ. በአካላዊ አጠራር ይጠራል

በእንግሊዝኛ የሰዋሰው ሕግ መሠረት አካላዊ አቋም ያለው የሚጠራበት ተውላጠ ስም እርሱ (He) የሚለው ነው:: የዚህ ተውላጠ ስም አጠቃቀም በአማርኛ ቋንቋ የእንግሊዝኛውን ያህል ግልጽ ባይሆንም አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪኩ ቋንቋ ለመንፈስ ቅዱስ የዋለው ተውላጠ ስም አካላዊ አቋም ላለው የሚውለው ነው::

#### ለ. የአካላዊ አቋም መግለጫዎች አሉት

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ያውቃል (ሮሜ 8:27፣ 1ቆሮ 2:10-11):: እርሱ ይፈቅዳል፣ ይከለክላል፣ ስጦታንም እንደሚወድ እያካፈለ ይሰጣል (1ቆሮ 12:7-11፣ ሐዋ 16:6):: እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ሰዎች ሊዋሹትና (ሐዋ 5:3-9) ሊቃወሙት (ሐዋ 7:51) የሞከሩት አካላዊ እኔነት ስላለው ነው:: ቤተ ክርስቲያንን ያሳድጋል፣ ሰዎችን ያጽናናል (ሐዋ 9:31):: ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅም፣ ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል (ዮሐ 16:8):: አማኞችን ወደ እውነት ሁሉ ይመራል (16:13)፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ያከብራል (16:14)፣ ሰዎችን ያጥባል፣ ይቀድሳል (ሮሜ 15:16፣ 1ቆሮ 6:11) እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅድሳን ይማልዳል (ሮሜ 8:27)::



መንፈስ ቅዱስ እኔነት ስላለው በሰዎች አለማመንና ኃጢአት ይመረራል፣ ያዝናል (ኢሳ 63:10፣ ኤፌ 4:30)::

መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምር (ሉቃ 42:12፣ ዮሐ 14:26፣ 1ቆሮ 2:13)፣ የሚመሰክር (ዮሐ 15:26)፣ የሚመራ (ሮሜ 8:14)፣ የሚማልድ (ሮሜ 8:26)፣ በሰዎች የሚናገር (ማቴ 10:20)፣ ትዕዛዝ የሚሰጥ (ሐዋ 8:29)፣ የሚልክ (ሐዋ 10:19-21፣ 11:12)፣ ሰዎችን ለአገልግሎት የሚሾም (ሐዋ 13:4፣ 20:28) ነው:: ይህ ሁሉ መለኮታዊ ሥራ እኔነት ያለው መለኮታዊ አካል የሚያከናውነው ነው::

#### ሐ. ከሥላሴዎች አንዱ ነው፣ ከሥላሴ አካላት ጋር በእኩልነት ተጠርቷል

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር አብን ወይም ወልድን ሳይተካ ለዘላለም በእርሱነቱ ይኖራል:: መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በእኩልነት ተጠርቷል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸውን መልዕክት ሲያጠቃልል «የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔርም ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን» (2ቆሮ 13:14) የሚለው መንፈስ ቅዱስ ከሥላሴ አካላት ጋር በእኩልነት የተጠራና እርሱ ራሱ አምላክ ለመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ ነው:: እንዲሁም ማቴ 3:16-17፣ 28:19፣ ዮሐ 14:26፣ 15:26 ይመልከቱ::

### 6.3.2 መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው

ክርስቲያኖች ተብለው የሚጠሩ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን የማያውቁ ብዙዎች እንደሚኖሩ ይገመታል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን የነበሩትን «ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?» ብሎ ሲጠይቃቸው «መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት» (ሐዋ 19:1-2)::

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ስምና፣ ባሕርይ ያለው አምላክ ነው:: ከመሬቱ ሽያጭ አስቀርቶ ያመጣውን ሐናንያን ይህን በማድረጉ መንፈስ ቅዱስን እንዳታለለ ማለትም እግዚአብሔርን መዋሸቱ መሆኑን ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲነግረው መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን ማስረገጡ ነው (ሐዋ 5:1-6):: ከዚህ በተጨማሪ መንፈስ ቅዱስ ጀሆቫ መሆኑንና መለኮታዊ ሥራዎችን እንደሚሠራ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

## ሀ. መንፈስ ቅዱስ ጀሆቫ (ያህዌ) ነው

እግዚአብሔር አምላክ እስራኤላውያንን ከግብጽ አውጥቶ በምድረ በዳ ሲመራቸው በእርሱ ባለማመናቸው ለሙሴ «ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል? በፊቱስ ባደረግሁት ተአምራት ሁሉ እስከመቼ አያምንብኝም?» (ዘኁ 14:11) በማለት እስራኤላውያንን ይወቅሳል:: ስለዚሁ ሁኔታ ዳዊት ሲናገር «... ልዑልንም በምድረ በዳ አስቆጡት:: ... እግዚአብሔርንም በልባቸው ፈተኑት» (መዝ 78:17-18) ብሏል:: እንዲሁም ስለዚህ የእስራኤላውያን መፈታተን መንፈስ ቅዱስ የሚለውን የዕብራውያን ጸሐፊ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል:- ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል... አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመሩበት...» (ዕብ 3:7-11):: እስጢፋኖስም ለአይሁድ ሲናገር «... እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ አባቶቻችሁ እንደተቃወሙት እናንተ ደግሞ» ይላቸዋል (ሐዋ 7:51):: በተጨማሪ ዘጸ 17:7 እና መዝ 95:7-11ን ይመልከቱ:: ከዚህ ማገናዘብ እንደሚቻለው እስራኤላውያን ጀሆቫን ሲቃወሙና ሲፈታተኑት መንፈስ ቅዱስን መቃወማቸውና መፈተናቸው መሆኑን ነው::

እንዲሁም በኢሳ 6:9-10 እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል «መስማትን ትሰማላችሁ፣ አታስተውሉምም ... ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው» ብሎ የተናገረውን ሐዋርያው ጳውሎስ አትመለከቱምም በላቸው» ብሎ የተናገረውን ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ ይህን የተናገረው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በሐዋ 28:25-27 ላይ «መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ ለአባቶቻችን መስማትን ትሰማላችሁና አታስተውሉም ... በላቸው» ብሏል በማለት ይገልጻል:: ጀሆቫ የተናገረው መንፈስ ቅዱስ የተናገረውን ነው:: ይህ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ያረጋግጣል:: በተጨማሪ ዘኁ 12:6፣ 24:2-4፣ 15-16 እና 2ጴጥ 1:21ን ይመልከቱ::

## ለ. የእግዚአብሔር ባሕርያት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት ናቸው

የእግዚአብሔርን ባሕርያት ሰፋ ባለ ሁኔታ በምዕራፍ 4 ተመልክተናል:: እነዚህ ባሕርያት ለሁሉም የሥላሴ አካላት ባሕርያት ናቸው:: መንፈስ ቅዱስ እነዚህ ባሕርያት እንዳሉት ለማየት የሚከተሉትን ጥቂት ጥቅሶች እንመለከታለን:: መንፈስ ቅዱስ ሁሉም ቦታ ይገኛል (መዝ 139:7)፣ ሁሉን ያውቃል (ኢሳ 40:13-14፣ 1ቆሮ 2:10-11)፣ ቅዱስ ነው (መዝ 51:11፣ 143:10)፣ ይወድዳል (ሮሜ 15:30)፣ መልካም ነው (ነህ 9:20)::



## ሐ. መለኮታዊ ሥራዎችን ይሠራል

የእግዚአብሔር ሥራዎች ሁሉ በሥላሴዎች የሚሠሩ መሆናቸውን በቀደመው ምዕራፍ አይተናል:: መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ሥራዎችን እንደሚሠራ የሚከተሉትን ጥቅሶች ማየት ይበቃል:: በመፍጠር ሥራ (ዘፍ 1:2፣ ኢዮ 33:4፣ ዮሐ 6:63)፣ የተፈጠረውን በመንከባከብ (መዝ 104:30)፣ በዳግም ልደት (ዮሐ 3:5-6) መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ሥራዎችን ይሠራል::

## 6.3.3 የመንፈስ ቅዱስ ስሞችና መግለጫዎች

### ሀ. ስሞች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ ስሞች ተጠርቷል፣ ከእነዚህ ስሞች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ::

#### ሀ.1 የእግዚአብሔር መንፈስ

ኃጢአተኞችን ወደ ክርስቶስ የሚጠራ (ዮሐ 6:44)፣ እውነትን የሚገልጽ (ማቴ 11:25)፣ አማኞችን የሚመራ መንፈስ ቅዱስ (ሮሜ 8:14) የእግዚአብሔር መንፈስ ነው:: በተጨማሪ ዘጸ 31:3፣ ዘኁ 24:2፣ 1ሳሙ 10:10፣ 19:20፣ 2ዜና 24:20፣ ኢዮ 33:4፣ ዘፍ 1:2፣ ኢሳ 61:1፣ ሮሜ 8:9-14፣ 1ቆሮ 2:11፣ 2ቆሮ 3:2-3፣ ኤፌ 4:30 ይመልከቱ::

#### ሀ.2 የክርስቶስ መንፈስ /የጌታ መንፈስ/ ሮሜ 8:9፣ 2ቆሮ 3:17

ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ የተቀበለውን የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ ለአማኞች ስለሰጠ ወይም ስላፈሰሰ (ሐዋ 2:33) መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ መንፈስ ይባላል:: ጌታም እንዳስተማረው የመንፈስ ቅዱስ መምጣትና በአማኞች ውስጥ መኖር እንደ ክርስቶስ መምጣት ተቆጥሯል (ዮሐ 14:16-20)::

#### ሀ.3 አጽናኝ / ጰራቅሊጦስ ዮሐ 14:16፣ ዮሐ 15:26

ጰራቅሊጦስ የሚለው የግሪክ ቃል «በአንድ ወገን መሆን» እና «መጥራት» ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገኘ ነው:: የቃሉ አመጣጥ

ከፍርድ ቤት አሠራር ጋር የተዛመደ ነው:: በፍርድ ቤት ክርክር ላይ አንድ ተከሳሽ በከሳሹ በጣም ሲወጠርና ስለራሱ እንዴት ብሎ ማስረዳት ወይም መማለድ ሲያቅተው የሚያግዘው ሰው ፍለጋ ዙሪያውን ያማትራል:: ከሕዝቡ መካከል አንድ የሚያውቀው ጓደኛ ሲያይ ተከሳሹ ያን ወዳጁን እንዲረዳው ይጠራዋል:: ይህ ወዳጁም ከሕዝቡ መካከል ወጥቶ ወደ ተከሳሹ ይጠጋና በጎኑ በመቆም ተከሳሹን ክሱን እንዲያሸንፍ ያግዘዋል::

«ሌላ አጽናኝ» የሆነው መንፈስ ቅዱስ በችግር ውስጥ ላለ አማኝ በጎኑ የሚቆምና ችግረኛውን የሚያግዝ/ የሚያጽናና ነው:: ተከሳሹ በጠላቱ ላይ ድል እንዲቀዳጅ ይመክረዋል፣ ያጽናናዋል፣ ይማልድለታል፣ ያበረታዋል፣ ያግዘዋል:: ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው አጽናኝ ነው (ኢሳ 9:6)::

ኢየሱስ ክርስቶስ ጠበቃችን ወይም ጰራቅሊጦስ ነው (1ዮሐ 2:1):: መንፈስ ቅዱስ ሌላው አጽናኝ ወይም ሌላው ጰራቅሊጦስ ነው:: «ሌላው» የሚለው ቃል በግሪኩ «አሉስ» (allos) ሲሆን ይኸም «የአንድ ዓይነት ሆኖ ሌላ» (other, some other) ማለት እንጂ «ሂትሮስ» (heteros) ወይም «የተለያዩ ዓይነት ሆኖ ሌላ» (of uncertain affinity, strange) ማለት አይደለም:: መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ አካል ያለው ግን ያው የእርሱን (የኢየሱስ ክርስቶስን) ዓይነት አጽናኝ ነው::

ከእነዚህ ስሞች በተጨማሪ መንፈስ ቅዱስ ሌሎች መጠሪያዎች አሉት:: እነዚህም:-

- የእውነት መንፈስ፣ ዮሐ 14:16-17፣ 15:26፣ 16:13
- የእግዚአብሔር ጣት፣ ሉቃ 11:20፣ ማቴ 12:28
- የዘላለም መንፈስ፣ ዕብ 9:14
- የቅድስና መንፈስ፣ ሮሜ 1:4
- የክብር መንፈስ፣ 1ጴጥ 4:14
- የሕይወት መንፈስ፣ ሮሜ 8:2 እና 4

## ለ. <u>መግለጫዎች</u>

የመንፈስ ቅዱስ መግለጫዎች የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ወይንም ባሕርይ ለመግለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ምሳሌዎች ናቸው::



### ለ.1 <u>ነፋስ</u> ዮሐ 3:8፣ ሐዋ 2:1-2

ነፋስ ኃይል አለው እንደፈቃዱም ያደርጋል:: የጥፋት ውኃ የቆመው በነፋስ ነው (ዘፍ 8:1)፣ እስራኤላውያን እንዲሻገሩ ባሕሩ የደረቀው በነፋስ ነው (ዘጸ 14:2):: የነፋስ አሠራር ሚስጢራዊ ነው:: ከየት እንደሚነሳና ወደየት እንደሚሄድ አይታወቅም:: የሚታየው ውጤቱ ነው:: ዳግመኛ መወለድ ከዚህ ጋር ተመሳስሏል::

ሰው እንደሚፈልገው የነፋስን አቅጣጫ መቀየር ኃይሉንም መግታት አይችልም:: መንፈስ ቅዱስ የራሱ ፈቃድ ስላለውና እንደ ሀሳቡም ስለሚሠራ የዚህን ቅዱስ ነፋስ አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል::

ነፋስ በእንቅስቃሴ ላይ በመሆኑ የሸተተውንና መጥፎ ጠረን ያለውን አየር ያጠራዋል:: ንጹህና ለጤና ተስማሚ ያደርገዋል:: እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ድካምን ወደ ብርታት፣ ሀዘንን ወደ ደስታ ይለውጣል::

### ለ.2 <u>ዘይት/ ቅባት</u> (1ሳሙ 16:14፣ 1ዮሐ 2:20፣ 2:27 እና ዮሐ 14:26)

በዘይት የተቀባ ለእግዚአብሔር የተለየ ለአገልግሎት የተመረጠ ነው:: ዘጸ 30:25-30፣ 40:9-16፣ ኢሳ 61:1-2):: ዘይቱ / ቅባቱ የመቀደስ ምሳሌ ነው:: እንዲሁም ዛሬ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለመቀደስና ውጤት ላለው አገልግሎት አስፈላጊ ነው (ሐዋ.1:8)::

በብሉይ ኪዳን በማደሪያው ድንኳን እግዚአብሔር በሚመለክበት ቦታ የነበረው መብራት ከቅዱስ ዘይት ከመቅረዙ ብቻ የሚመጣ ነበር:: እግዚአብሔርን ለማምለክ ብርሃን የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ነው::

ዘይት በብረቶች መካከል በመግባት ግጭትና መፈጋፈግ እንዳይኖር ያደርጋል፣ ከድርቀት ይጠብቃል፣ ቋቋቴ እንዳይኖር ይከለክላል:: መንፈስ ቅዱስ በሰዎች መካከል ሰላምና ፍቅርን ያመጣል::

### ለ.3 <u>እሳት</u> (ማቴ 3:11-12፣ ሉቃ 3:16፣ ሐዋ 2:2-3)

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ክብር ተገልጧል (ዘጸ 3:1-5፣ ሕዝ 1:4፣ 13):: እሳት እግዚአብሔር የቀረበለትን መስዋዕት የመቀበሉ ምልክት ነው (ዘሌ 9:24፣ 1ነገ 18:32፣ 2ዜና 7:1-3)::

እሳት የማይፈለገውን ቆሻሻ ያቃጥላል፣ ያጠራል:: ገለባውን ይበላል:: አማኙም የሚቀደሰው በውስጥ ያለውን የማይፈለገውን የመንፈስ

ቅዱስ እሳት ሲያቃጥለው ነው (ኤር 23:29፣ ዕብ 12:29):: እንዲሁም እሳት የእግዚአብሔር ጥበቃ ምልክት ነው (ዘጸ 13:21፣ 2ነገ 6:17)::

ለ.4 ርግብ (ማቴ 3:16፣ ማር 1:10፣ ሉቃ 3:22፣ ዮሐ 1:32)

ርግብ የየዋህነት ምልክት ናት (ማቴ 10:16):: ርግብ የሰላም ምልክት ናት:: ከጥፋት ውኃ በኋላ የእግዚአብሔር ቁጣ ማለፉን ለኖህ ለመጀመሪያ ጊዜ ያበሰረች ርግብ ናት (ዘፍ 8:10-11):: አማኙም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ከሞት ወደ ሕይወት መተላለፉን፣ መታረቁንና ሰላም ማግኘቱን (ዮሐ 5:24) መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርለታል::

ለ.5 ማኅተም (2ቆሮ 1:22፣ ኤፌ 1:13፣ 4:20)

ሰው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን በመንፈስ ቅዱስ ይታተማል:: ማኅተም ከንብረት ባለቤትነት ጋር የተያያዘ ቃል ነው (ኤር 32:9-10)፣ የማንነት መግለጫ ነው:: የእግዚአብሔር ሕዝብ በመንፈስ ቅዱስ መታተሙ የእግዚአብሔር ብቻ መሆኑንና በእርሱ ባለቤትነትና ጥበቃ ሥር መሆኑን ያመለክታል:: ይህም መታተም ለደህንነት ቀን ነው::

ማኅተም የሥልጣን ምልክት ነው:: አንድ ሰው ለመሾሙ ሥልጣን እንደተሰጠው በማኅተም ያረጋግጣል (ዘፍ 41:42):: እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ የታተመ ወንጌልን ለማሰራጨትና በጠላት ላይ ለመጫማት ሥልጣን ተሰጥቶታል::

ለ.6 መያዣ (2ቆሮ 1:22፣ 5:5፣ ኤፌ 1:14)

መያዣ የሚለው ቃል ወደፊት በእርግጥ ለሚፈጸም ነገር በአሁን ጊዜ የተሰጠ ማረጋገጫን ወይም ቀብድን ያመለክታል:: አማኙ በእርግጥ የዳነ ለመሆኑና መንግሥተ ሰማያትንም እንደሚወርስ የተሰጠው ዋስትና መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ማደሩ ነው:: ጠላት በየጊዜው ለሚያነሳበት ጥያቄ፣ ጥርጥርና ክስ የመጀመሪያ መልስ የሚሆነው የመንፈስ ቅዱስን መያዣ መቀበሉ ነው:: ግሪኮች «መያዣ» የሚለውን ቃል ለእጮኛምነት ቀለበት ይጠቀሙበታል:: በመጽሐፍ ቅዱስ «መያዣ» መንፈስ ቅዱስን ለመቀበላችን መግለጫ ሲሆን ይህም በሰማይ ያለው አባታችን ለእኛ ቃል ኪዳን መግባቱን ያረጋግጥልናል::

መያዣ ቅድሚያ ክፍያ ነው፣ ሙሉው ሂሳብ በኃላ እንደሚከፈል ውል ለመገባቱ ማረጋገጫ እንዲሆን ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለመንግሥተ



ሰማያትና በዚያ ላለው ሕይወት እንደ ቅድሚያ ክፍያ ነው:: አማኙ የዚያን ሕይወት ደስታ፣ ሰላምና እረፍት በቅድሚያ ክፍያነት አሁን በዚህ ምድር እያለ ይቀምሳል:: እግዚአብሔር ራሱ ይህን መያዣ መስጠቱ የሰጠውን የደኅንነት ተስፋ እንደሚፈጽመው ያረጋግጣል::

ለ.7 ወይን ጠጅ (ኤፌ 5:18፣ ሐዋ 2:12-13)

የወይን ጠጅ መግለጫነት ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር በተቃራኒ ሁኔታና በተመሳሳይነትም ጭምር ነው::

በወይን ጠጅ በመስከርና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መካከል ተመሳሳይነቱ የሰከረውና የተሞላው ሁለቱም በሌላ ኃይል ቁጥጥር ሥር መሆናቸው ነው:: ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በተወሰነ መንገድ ከወይን ጠጅ ስካር ጋር ተመሳስሎ ይታያል:: ይሁን እንጂ በወይን ጠጅ መስከርና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሁለቱም በምንነት፣ በድርጊትና በውጤት ተቃራኒዎች ናቸው::

የወይን ጠጅ ስካር ውጤት ራስን ለጊዜው ለመደለል/ «ለማስደሰት» ሲሆን በጤንነት ላይ ደግሞ የሚያመጣው ጉዳት ከፍተኛ ነው:: ይህም ማባከን ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ግን መንፈሳዊ ደስታ ነው:: ይህ ደግሞ በመዝሙር፣ በመንፈሳዊ ቅኔ፣ በምስጋና ይገለጻል (ኤፌ 5:19-21):: የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በእምነት ለመጠንከር፣ ለአገልግሎት የበለጠ ለመነቃቃት፣ ክርስቶስን ለመምሰል ነው:: ስካር ጠጭው ሕሊናውን በመሳት ለጊዜው ሀዘንንና ጭንቀትን እንዲረሳ ያደርጋል:: የስካር መጨረሻው ጸጸትና ኃጢአት ነው:: ስካር ጠጭውን ከጤናማ አስተሳሰብ በማውጣት አጉል ድፍረትና ኃይል እንዲሰማው ያደርጋል:: የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ግን ሰውን ወደ ጤናማ አስተሳሰብና በጎ ሕሊና ይመራል:: ፈጽሞ በሰላም ይሞላል:: ፈሪውንና ደካማውን ለወንጌል ሥራና ለእግዚአብሔር ክብር ያበረታታል፣ ኃይል ይሰጣል:: ኃጢአትን በማሸነፍ የድል ሕይወት እንዲኖር ያደርጋል::

የመንፈስ ቅዱስ መግለጫዎች የእርሱን ሥራና ባሕርይ ለመረዳት ያግዛሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህን የመንፈስ ቅዱስ መግለጫዎች ምንነት በመተርጎም ጊዜ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ እርግብና ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ መግለጫዎች ናቸው:: ነገር ግን ርግብ የኀዘን ምሳሌ ሆናለች (ኢሳ 59:11)፣ ነፋስ በስህተት ትምህርት ሥራ ምሳሌነት ተጠቅሷልና (ኤፌ 4:14)::

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የሥላሴ አካላትን ማንነት፣ ባሕርይና ሥራ ለማየት ሞክረናል። በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ የእግዚአብሔን ሥራዎች ባጭሩ እንመለከታለን።



# ምዕራፍ 7. የእግዚአብሔር ሥራዎች

የእግዚአብሔር ሥራዎች የእርሱን ጥበብ፣ ችሎታ፣ ሥልጣንና ሌሎቹንም ባሕርያቱን የሚያሳዩ የማንነቱ መግለጫዎች ናቸው። ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራዎች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ ማለትም ማቀዱን፣ መምረጡን፣ መፍጠሩንና የፈጠረውን የሚንከባከብ መሆኑን በዚህ ምዕራፍ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

## 7.1 ማቀድ

እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ የሚሆነውን ሁሉ ለክብሩ እንዲሆን አስቀድሞ የወሰነበት ወይም የፈቀደበት የዘለለም ሀሳብ የእግዚአብሔር ዕቅድ ይባላል (ሮሜ 8:29፣ ኤፌ 3:11)። እግዚአብሔር አንድ ዘላለማዊ የተሟላ ዕቅድ አለው። ይህ የእግዚአብሔር የተሟላ አንድ ዕቅድ በሰዎች ዘንድ ሲታይ ብዙ ዕቅዶች ይመስላሉ።

የእግዚአብሔር ዕቅድ በእርሱ ሁሉን አዋቂነቱ፣ ሁሉን ቻይነቱና ባለመለወጡ ላይ የተመሠረተ ነው። የእግዚአብሔር ዕቅድ የእርሱነቱ ወይም የባሕሪው ክፍል አይደለም፤ እግዚአብሔር በእርሱነቱ የዘላለም ዕቅድ አለው እንጂ። እግዚአብሔር ሊሆን ያለውን ማናቸውንም ነገር በሁሉን አዋቂነቱ አስቀድሞ አውቆአል። ይህ ደግሞ በዕቅዱ ውስጥ ተጠቃልሏል። ነገሮች በሚፈጸሙበት ወይም በሚከናወኑበት ጊዜ በእርሱ ዘንድ አስቀድመው የታወቁ ናቸው።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ግን በሙሉ ለሰው የተገለጠ አይደለም (ዘዳ 29:29፣ ሐዋ 17:30-31)። የእግዚአብሔር ዕቅድ የሰውን ነጻ ምርጫ ወይም ፈቃድ የሚቃረን አይሆንም። በተጨማሪ (ዘፍ 45:8፣ 50:20፣ መዝ 33:11፣ 78:29፣ 106:15፣ ምሳ 16:33፣ 19:21፣ ኢሳ 46:10፣ ሐዋ 4:27-28፣ 14:16፣ 17:26-30፣ ኤፌ 2:8-10፣ 1ጴጥ 1:2) ይመልከቱ።

እግዚአብሔር ጻድቅ አምላክ ነው። የኃጢአት ጀማሪ፣ ወይም ፈጣሪ፣ ወይም ባለቤት፣ ወይም ተጠያቂ አይደለም። እርሱ ኃጢአትን አልፈጠረም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ አምላክ በመሆኑ የሰው ልጅ ኃጢአት እንደሚሠራ በእርሱ የቀደመ እውቀት የታወቀ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ነጻ ፈቃድ ያለው

ፍጡር አድርጐ ነው፡፡ ሰው ግን ይህን ነጻ ፈቃድ ወይም በክፉና በመልካም መካከል ለመምረጥ የተሰጠውን ነጻነት ተጠቅሞ ክፉን መረጠ፡፡ በዚህም ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ፡፡ ሰው ለሚመርጠው ነገር ተጠያቂ ነው፡፡

ኃጢአት የፈጸሙ ነጻ ፈቃድና ምርጫ የተሰጣቸው ፍጥረታት (ሰዎችና መላእክት) ናቸው፡፡ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ይቆጣል (ዘጸ 32:9-10፣ ኢሳ 30:27-28)፡፡ የእግዚአብሔር ቁጣ ሁልጊዜም ቢሆን የሚገለጸው በጽድቅ ነው፡፡ የእርሱ ቁጣ ጽድቁንና ቅድስናውን ያሳያል (ሕዝ 25:17)፡፡

## 7.2 <u>መምረጥ</u>

### 7.2.1 <u>ሰው ነጻ ፈቃድ አለው</u>

እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው መልካሙንና ክፉውን ለመምረጥ የሚችል ፍጡር አድርጐ ነው፡፡ በገነት ባኖረውም ጊዜ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፣ ነገር ግን መልካሙንና ክፉን ከሚያስታውቅ ዛፍ አትብላ፣ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» በማለት ሕይወትን እንዲመርጥ አዝዞታል (ዘፍ 2:16-17)፡፡

እንዲሁም በዘዳ 30:19-20 ጌታ እግዚአብሔር እስራኤልን «እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፣ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፣ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው፣ ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ» በማለት ሕይወትን ይመርጥ ዘንድ አዞታል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በሌላ ቦታ እስራኤላውያን በሕይወትና በሞት፣ በመልካምነትና በክፋት፣ በበረከትና በመርገም መካከል ምርጫ እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ያዛል፡፡ በረከቱ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠበቅ የሚገኝ ነው (ዘዳ 11:26-28)፡፡

እግዚአብሔር በሕዝቅኤል በኩል፡-

> ኃጢአተኛው ካደረጋት ኃጢአት ሁሉ ቢመለስ ትዕዛዜንም ሁሉ ቢጠብቅ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም፡፡ የበደለው በደል ሁሉ አይታሰብለትም፤ በሠራው



> ጽድቅ በሕይወት ይኖራል፡፡ በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዱስ ይመለስና በሕይወት ይኖር ዘንድ አይደለምን? (ሕዝ 18:21-23)፡፡

ስለሆነም ሰው በሕይወት ለመኖር እንዲችል ከኃጢአቱ ሁሉ በንስሐ ለመመለስና እግዚአብሔርን በመፍራት ለመኖር ምርጫ የማድረግ ነጻነትና ችሎታ ተሰጥቶታል፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈልግ በሕይወት ይኖራልና፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ትምህርቱን በመቀበል የሚከተሉት እንደነበሩ ሁሉ የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው የሚጥሉም ነበሩ (ሉቃ 7:29-30)፡፡ በማቴ 22 እንደምናነበው ንጉሡ ባደረገው የሠርግ ግብዣ ላይ የተገኙት ጥሪውን ሰምተው የተቀበሉት ናቸው፡፡ ጥሪው ለብዙዎች ደርሷል በጥሪው የተጠቀሙ ግን ጥሪውን ለመቀበል የመረጡት ወይም ፈቃደኞች የሆኑት ናቸው (ማቴ 22:1-4)፡፡ እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኢየሩሳሌም ሲናገር («... ዶሮ ጫጩቶቿን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ አልወደዳችሁምም» (ማቴ 23:37) በማለት በፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር ጥሪ እምቢተኞች እንደሆኑ ይናገራል፡፡

ሰዎች ሁሉ ይድኑና እውነትን ወደማወቅ ይደርሱ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (1ጢሞ 2:4፣ ቲቶ 2:11)፡፡ ሸክም የከበደው ወደ ጌታ ይምጣ እርሱም ያሳርፈዋል (ማቴ 11:28-30፣ ዮሐ 3:16፣ 5:39)፡፡

### 7.2.2 <u>እግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣን አለው</u>

መጽሐፍ «አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ ሰማዩንና የሰማያት ሠራዊታቸውንም ሁሉ፣ ምድሩንና በእነርሱ ላይ ያሉትን ሁሉ፣ ባሕሮቹንና በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ፈጥረሃል፣ ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል የሰማዩም ሠራዊት ለአንተ ይሰግዳሉ» እንደሚል (ነህ 9:6) በሰማይ፣ በምድር በባሕር ውስጥ ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፡፡ የሰው ነፍስ የእግዚአብሔር ናት፡፡ «እነሆ ነፍሳት ሁሉ የእኔ ናቸው የአባት ነፍስ የእኔ እንደ ሆነች ደግሞ የልጅ ነፍስ የእኔ ናት» (ሕዝ 18:4)፡፡ ሰው ያለው ነገር በሙሉ የእግዚአብሔር ንብረት ነው (1ቆሮ 4:6-7)፡፡ ብሩና ወርቁ የእግዚአብሔር ነው (ሐጌ 2:8)፡፡

ኢዮሣፍጥ ሲጸልይ «አቤቱ የአባቶቻችን አምላክ ሆይ፣ በሰማይ ያለህ አምላክ አንተ አይደለህምን? የአሕዛብንስ መንግሥታት ሁሉ የምትገዛ

አንተ አይደለህምን? ኃይልና ችሎታ በእጅህ ነው፣ ሊቋቋምህ የሚችል የለም» እንዳለው (2ዜና 20:6) እግዚአብሔር ብቻ የምድር ነገሥታት ሁሉ አምላክ፣ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ ነው (ዘጸ 15:18፣ 2ነገ 19:15፣ ኢሳ 33:22፣ 66:1፣ ሚል 1:14፣ 1ጢሞ.6:15)። እግዚአብሔር አምላክ የሚያደረገውን ሁሉ በሥልጣን ያደርጋል። እግዚአብሔር «ድምጹን ባሰማ ጊዜ ውኖች በሰማይ ይሰበሰባሉ፣ ከምድርም ዳር ደመናትን ከፍ ያደርጋል ለዝናብም መብረቅን ያደርጋል፣ ነፋስንም ከቤተ መዛግብቱ ያወጣል (ኤር 10:13)። ዳንኤል እንዳለው:-

> ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፣ ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል ነገሥታትን ያፈልሳል፣ ነገሥታትንም ያስነሣል፣ ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል። የጠለቀውንና የተሠወረውን ይገልጣል፣ በጨለማ ያለውን ያውቃል፣ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው (ዳን 2:20-22)።

እግዚአብሔር የወደደውን ያደርጋል፣ የሚከለክለውም የለም (ኢዩ 23:13፣ መዝ 135:6)። መንግሥትን ለወደደው ይሰጣል፣ በሰዎች መንግሥት ላይ ይሰለጥናል (ዳን 4:35፣ 5:21፣ ሆሴ 13:10፣ ሮሜ 13:1)። እግዚአብሔር ሃሳቡንና ፈቃዱን በሰዎች ውስጥ ያደርጋል፣ በእነርሱም በኩል ሊያደርግ የሚወደውን ይፈጽማል። «በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በመጀመሪያው ዓመት እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን መንፈስ አስነሣ» (2ዜና 36:22) ተብሎ እንደተጻፈው እግዚአብሔር ፈቃዱን ይፈጽም ዘንድ የአሕዛብን ነገሥታት መንፈስ ሳይቀር ያስነሳል (ዘጸ 12:36፣ 1ዜና 5:26፣ ዕዝ 5:26፣ 7:27)።

እግዚአብሔር ባለሙሉ ሥልጣን ስለሆነ እንደወደደ የሰውን ሀሳብ ይሽራል፣ የሚወደውን የራሱን ሀሳብ ያደርጋል። ሶሪያዊው ላባ ያዕቆብን ተከታትሎ በደረሰበት ጊዜ ያዕቆብንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን «ክፉ አደርግባችሁ ዘንድ ኃይል ነበረኝ፣ ነገር ግን የአባታችሁ አምላክ ትናንት:- ያዕቆብን በክፉ ነገር እንዳትናገረው ተጠንቀቅ ብሎ ነገረኝ» በማለት ምንም እንኳ ላባ ክፉ ቢያስብባቸውም እግዚአብሔር ግን በሥልጣኑ እንዳልፈቀደለት ይመሰክራል (ዘፍ 31:29)። እንዲሁም ዘፍ 24:50፣ 45:5-8፣ 50:19-20፣ ዘኁ 24:10-13፣ ዘዳ 23:3-5፣ 2ሳሙ 17:14፣ 1ነገ 12:22-24 ይመልከቱ።

የእግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣን በምርጫውም ይገለጻል። እግዚአብሔር በምሕረቱ እርሱ እንደወደደ ይመርጣል። እስራኤላውያንን እግዚአብሔር እንዴት እንደመረጣቸው ሙሴ ሲናገር



«እግዚአብሔርም የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከአሕዛብ ሁሉ በቁጥር ጥቂቶች ነበራችሁና፤» ይላቸዋል (ዘዳ.7:7)። እስራኤል የተመረጠችው እግዚአብሔርን ለአሕዛብ እንድታውጅ ነበር። ሆኖም እስራኤል ታማኝ አልሆነችም (ሆሴ 11:1-3)።[72]

እግዚአብሔር ሰዎችን ለተለያዩ ዓላማ መርጧል። እግዚአብሔር መሪዎችን አብርሃምን (ነህ 9:7)፣ ያዕቆብን (ሚል 1:2)፣ ሙሴን (መዝ 106:23)፣ ዘሩባቤልን (ሐጌ 2:23) ወዘተ፣ ነቢያትን:- ኤርምያስን (ኤር 1:4-8)፣ አሞጽን (አሞ 7:14-15)፣ ሕዝቅኤልን (ሕዝ 2:1-3)፣ ካህናትን:- የሌዊን ወገን (ዘዳ 18:1-5)፣ ነገሥታትን:- ሳዖልን (1ሳሙ 10:24)፣ ዳዊትን (2ሳሙ 6:21)፣ ሰሎሞንን (1ዜና 28:5)፣ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት (ዮሐ 6:70)፣ አገልጋዮችን (ሐዋ 9:15) መርጧል።

እግዚአብሔር ሰዎችን በግል ለደህንነት ቢጠራና ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ በእምነት ተቀብለው መመረጣቸውን ቢያረጋግጡ እንኳ እግዚአብሔር በሥራው ፍጹም ጻድቅ ነው፣ የሚያደርገውን ያውቃል። ይህን በማድረጉ ለማንም ተጠያቂ አይደለም። ሥራ ሠሪውን ለምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ብሎ ሊጠይቀው እንደማይችል ሁሉ ሰውም እግዚአብሔርን ለምን እንዲህ ታደርጋለህ ብሎ ይጠይቀው ዘንድ አይችልም (ሮሜ 9:14-21)።

ሰው በእግዚአብሔር ለአገልግሎት የተመረጠ ቢሆን እንኳ እግዚአብሔርን በመፍራት እየኖረ እስከ መጨረሻው ካልጸና የተመረጠው ሊተው (ሊጣል) የተሾመው ሊሻር ይችላል። የተመረጠው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የገባውን ቃል ኪዳን የመጠበቅ ተጠያቂነት አለበት (ዘጸ 19:5-6፣ አሞ 3:2)።

- ካህኑ ዔሊ ለክህነት በእግዚአብሔር የተመረጠ ነበር (1ሳሙ 2:27-28) ነገር ግን እግዚአብሔርን ባለመፍራቱና በቅድስና

---

72 Israel's election does not mean God has rejcted the other nations. Rather, election creates for Israel the task of representing God among other nation's so that salvation might come to them. Election essentially means that God called Israel to sene Him and to reflect His character. Similar to God's choice of individuals, election does not guarantee to every Israelite eternal salvation." William W.Klein, 1990, The new chosen people:A corporate view of election, Gran Rapids: zondervan publishing House, p,43.

### 7.3.3 የፍጥረት ዓላማ

እግዚአብሔር ራሱ በራሱ የሚኖር፣ ለመኖር ምንም ነገር የማያስፈልገው ኃያል አምላክ ነው:: እግዚአብሔር በራሱ ሕይወት አለው (ዮሐ 5:26):: ከፍጥረቱም ምንም አይፈልግም (ሐዋ 17:25):: ሰውን ሳይፈጥር በዚያው ሁኔታ ለዘላለም ሊኖር ይችላል:: ነገር ግን በእርሱ መልካም ፈቃድ ሰውን ለመፍጠር ፈቀደ:: ሰውን የፈጠረበት ምክንያት ሰው እግዚአብሔርን ይፈልግና ለክብሩም ይኖር ዘንድ ነው፣ እርሱ የፈጠረውን ሁሉ ለክብሩ ፈጥሯልና:: «እግዚአብሔር ሁሉን ለእርሱ ለራሱ ፈጠረ» (ምሳ.16:4):: የፈጠረውም የእርሱን ክብር ይናገራል (መዝ 19:1):: እንዲሁም (ኢሳ 43:7 ሮሜ 11:36 ቆላ 1:16) ይመልከቱ::

ሰው በመፈጠሩ በእግዚአብሔር እርሱነትና ባሕርይ ላይ የሚጨምረው ነገር የለም:: ሰው መልካምም ሆነ ክፉ ቢሆን የሚጠቅመውና የሚጐዳው ራሱን ነው (ኢዮ 35:7-8):: እኛ ለእግዚአብሔር ከታዘዝን በኋላ የማንጠቀም ባሪያዎች ነን እንድንል ታዘናል (ሉቃ 17:10)::

## 7.4 መጠበቅ/ መንከባከብ

እግዚአብሔር ሁልጊዜም የዓለም ማለትም የፍጥረቱ ገዥና ጠባቂ ነው:: እግዚአብሔር የፈጠረውን የሚጠብቅና የሚንከባከብ የፍቅር አምላክ ነው (ዕብ.1:3):: ይህን እንዲያደርግ አደራ የሰጠው የለም:: እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ያደረገውን «መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደ ራሱ ቢሰበስብ፣ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል፣ ሰውም ወደ አፈር ይመለሳል» (ኢዮ 12:10፣ ሐዋ 17:28):: «በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም» ያለ አምላክ (ዘፍ 8:22) በታሪክ ውስጥ ቃል ኪዳኑን እንደጠበቀ ሁሉም ሰው ምስክር ነው:: እግዚአብሔር በዘመናት ውስጥ «... መልካም ሥራ እየሠራ፣ ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም» (ሐዋ 14:17):: ይህ መልካምነቱ ለምድር ሁሉ በተለይ በእርሱ ለሚያምኑት ያለውን ጥበቃ / እንክብካቤ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል::



### 7.4.1 የሚያስፈልገውን በመስጠት

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ለመኖር የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጥቶአል:: አየር፣ ውኃ፣ ምግብ፣ ወዘተ... የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው:: ፍጥረት ሁሉ ራሱን በራሱ ችሎ ሊኖር አይችልም (ኢዩ 8:11):: ሰዎችም ሆኑ እንስሳት ለምግብነት የሚሆኑ እፅዋትን ባያገኙ ኖሮ በሕይወት ባልኖሩም ነበር::

እግዚአብሔር ለልጆቹ ደግሞ የተለየ ጥንቃቄ ያደርጋል:: ለእስራኤላውያን በርሃብ እንዳይጠፉ ቅሬታዎችን (Remnants) አስቀርቷል (ዘፍ 45:7)፣ መናን መግቧል፣ ውኃን ከዓለት አፍልቋል፣ ለአርባ ዓመት ልብስ እንዳያልቅ በማድረግ ተአምራት[74] አድርጓል:: ስለ ልጆቹ ይጠነቀቃል ዘዳ 8:3-4፣ ዘጸ 13:21፣ መዝ 78:25፣ ማቴ 6:26፣ 10:29-31፣ ይመልከቱ::

### 7.4.2 ከክፉ በመጠበቅ

እግዚአብሔር ልጆቹን በድንቅ ይጠብቃል:: ለሕጻናት መላእክት (ማቴ 18:10)፣ ለዳኑትም የሚያገለግሉ መላእክት (ዕብ.1:14) አዘጋጅቷል:: እግዚአብሔር ሕዝቡን ከክፉ ይጠብቃል:: ኤልሳዕን ከሶሪያ ሠራዊት (2ነገ 6:14-17)፣ ጠብቋል:: ያለ እርሱ ፈቃድ ከራሳችን አንዳች ፀጉር እንዳትጠፋ በማድረግ (ሉቃ 21:18)፣ እኛን ይጠብቃል:: ከክፉ ሁሉ ይጠብቃል፣ መውጫንም ያዘጋጃል (መዝ 91:10፣ 12:3-8፣ 1ቆሮ 10:13)::

### 7.4.3 በመምራት

እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመኑትን ይመራል፣ መንገዱን ያሳያቸዋል (ዘፍ 45:7፣ ኢሳ 4:14፣ መዝ 37:5፣ ዳን 2:21)::

---

74 ታምራት ከተፈጥሮ ሕግጋትና ከተለመደው ሁኔታ ውጪ ወይም ከሰው ችሎታ በላይ በእግዚአብሔር ኃይል የሚፈጸም ድንቅ ነገር ነው:: ታምራት የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነትና እርሱ በፈጠረው በማናቸውም ነገር ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለው የሚያሳዩ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች ናቸው:: ታምራት ለእግዚአብሔር ቃል (ለመጽሐፍ ቅዱስ) እውነተኛነት ተጨማሪ ማስረጃዎች ይሆናሉ:: ታምራት የሚደረገው ለእግዚአብሔር ክብር ነው (1ነገ 17:3-6፣ ማቴ 14:20-25፣ ዮሐ 2:23፣ 20:30-31፣ ሐዋ 2:19)::

እግዚአብሔር ፍጥረትን ይደግፋል፣ ያቆማል፣ ይቆጣጠራል:: የወራት መፈራረቅ፣ የእፅዋት መብቀልና ማደግ፣ የእንስሳት ሕልውና፣ የመሬትና የጨረቃ እንቅስቃሴ፣ ወዘተ ሁሉም በእግዚአብሔር ጥበቃና ቁጥጥር ሥር ያለ ነው:: እግዚአብሔር የሰውን እስትንፋስ ሁሉ በእጁ ይዟል:: እግዚአብሔር የፈጠረውን ባይጠብቅ፣ ባይንከባከብና ባይቆጣጠር ፍጥረት ሁሉ በሕይወት ባልኖረም ነበር (ኤር 31:35፣ ዳን 5:23፣ ቆላ 1:17)::

አንባቢ ሆይ እስከ አሁን ስለ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ ጊዜና ቦታ እንዲሁም የጸሐፊው መረዳት የፈቀደውን ያህል ብቻ እንጂ በሰው ደረጃ እንኳን ለማለት የሚቻለውን ሁሉ ማለት እንዳልተቻለ ጸሐፊው በሚገባ ይገነዘባል:: ይሁንና እስካሁን በተጻፈው ብቻ እንኳን አምላካችን ሕያው እግዚአብሔር ክቡር፣ ታላቅና የተፈራ፣ ምስጢሩም ጥልቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: ስለሆነም እርሱን በማወቅ እንድናድግ (ቆላ 1:10) የሚፈልገው ይህ እግዚአብሔር ይህች ትንሽ መጽሐፍ ልትል ከቻለችው በላይ እንድናውቀውና እንድናመልከው ይርዳን::

ክብር ለአብ፣ ክብር ለወልድ፣ ክብር ለመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሁን:: አሜን::



# አባሪ 1

## የእግዚአብሔር ቅድመ ውሣኔና የሰው ነጻ ፈቃድ

### ሀ. ከዚህ ጋር በተያያዘ መንገድ በታሪክ ውስጥ የተነሱ አስተሳሰቦች

ከዚህ ርዕስ ጋር በተያያዘ በታሪክ ውስጥ ብዙ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች እንደነበሩ ይታወቃል:: ከነዚህም ውስጥ በተለይ በጣም ጐልተው የሚታዩት የጆን ካልቪንና የጃኮብ አርሚኒየስ[75] ሲሆኑ ሁለቱ አስተሳሰቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል::

| ጆን ካልቪን | ጃኮብ አርሚኒየስ |
| --- | --- |
| 1. ሰው ፈጽሞ በኃጢያት የሞተ ነው:: | 1. ሰው ፈጽሞ ኃጢአተኛ ስለ ሆነ የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገዋል:: |
| 2. የእግዚአብሔር ምርጫ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ | 2. የእግዚአብሔር ምርጫ በቅድመ ዕውቀትና በታየ እምነት መሠረት:: |
| 3. ክርስቶስ የሞተው ለተመረጡት ብቻ ነው:: | 3. የክርስቶስ ሞት ለሰው ሁሉ ነው:: |
| 4. የክርስቶስን ጸጋ መቃወም አይቻልም:: | 4. የክርስቶስን ጸጋ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ይቻላል:: |
| 5. አማኞች እስከ መጨረሻ ይጸናሉ:: | 5. አማኞችም ቢሆኑ እምነታቸውን ሊጥሉና ደኅንነታቸውንም ሊያጡ ይችላሉ:: |

### ለ. ብዙ ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎች

እላይ የተጠቀሱት ሁለት አስተሳሰቦች በብዙ የሚመሳሰሉ ቢሆንም የሚለያዩባቸው መንገዶች መኖራቸው ግልጽ ነው:: ስለሆነም ከነዚህ አስተሳሰቦች ጋር በተያያዘ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ጥያቄዎች ይነሳሉ:: ከጥያቄዎቹ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. አንድ ጊዜ የዳነ ሰው በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢገባ ለዘላለም የዳነ ነውን?
2. ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ጊዜ የሚሄድ ሁሉ የዳነ ነው ማለት ይቻላልን?
3. እንደ እኛ ክርስቲያኖች ናቸው ያልናቸውና እግዚአብሔርም የተጠቀመባቸው ከሐዲዎች ሊሆኑ አይችሉምን?
4. ሰው አንድ ጊዜ ከዳነ በኋላ ምንም ዓይነት ሕይወት ቢኖር በመጨረሻው ጊዜ የሚቀርበት ሽልማት ወይም አክሊል እንጂ ደኅንነቱን ግን ያገኛል የሚባለው እውነት ነው?
5. ዳግመኛ የተወለደውንና ያልተወለደውን እንዴት ማወቅ ይቻላል?
6. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ሕብረት ካቋረጠ በኋላ እንደገና ካላስተካከለው መጨረሻው ምን ይሆናል?
7. ክርስቲያን ነው ሲባል ኖሮ በመሐል ግን ወደ ኋላ የተንሸራተተ ሁሉ በእርግጥ ከመጀመሪያውም ዳግመኛ ያልተወለደ ስለሆነ ነውን?
8. እውነተኛ አማኝ ኃጢአትን እያደረገ ቢቀጥልና ራሱን ባያስተካክል የሚደርስበት በሥጋው ላይ ቅጣት (ፍርድ) ብቻ ነውን?
9. ሰው ዳግመኛ ሲወለድ የክርስቶስ አካል ይሆናል:: አማኝ ደኅንነቱን ሊያጣ ይችላል ከተባለ ከክርስቶስ አካል እንደገና ይወጣል (ይለያል) ማለት ነው?

---

75 የእነዚህን ሁለት አመለካከቶች የእንግሊዝኛ ቅጅ በአባሪ 2 ይመልከቱ::

## ሐ. በዕብ 6:4-8 ላይ የሚቀርቡ የተለያዩ መረዳቶች

ስለ እግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔና የሰው ነጻ ፈቃድ ወይም «አንድ ጊዜ መዳን ለዘላለም መዳን» በሚለው እና «ደኅንነትን ማጣት ሊኖር ይችላል» የሚሉትን አመለካከቶች የሚደግፉ አማኞች በማስረጃነት ከሚያቃርቧቸውና የተለያየ አተረጓጐም ከሚሰጣቸው ጥቅሶች ሁለቱ በዕብ 6:4-8 እና ዕብ 10:26-31 የሚገኙት ናቸው:: በዚህ ክፍል በዕብ 6:4-8 የሚገኘውን በ5 ነጥቦች በማጠቃለል መመልከት ይቻላል::

1. በዕብ 6:4-8 የተጠቀሱት ሰዎች ክርስቲያኖች የነበሩ አይደሉም:: በሰዎች ዘንድ ክርስቲያን እንደሆኑ የተቆጠሩ ነገር ግን እውነተኛ ለውጥ ያላገኙ ወይም ዳግመኛ ያልተወለዱ ናቸው:: መልእክቱ የተላከላቸውንም ሰዎች የሚመለከት አይደለም:: ምክንያቱም አጻጻፉ ከአንደኛ ወደ ሦስተኛ መደብ ይሸጋገራል::

2. «... እንደገና ለንስሐ እነእርሱን ማደስ የማይቻል ነው» የሚለው በሰው ዘንድ የማይቻል መሆኑን ሲያመለክት እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን የማይቻል ነገር የለም::

3. ስለ ጊዜያዊ ቅጣት ማለትም በሥጋ የሚሆን ቅጣትን እንጂ ለዘላለም የሚሆን መንፈሳዊ ቅጣትን አያመለክትም::

4. ኢየሱስ ክርስቶስን አጥብቆ የተቃወመ እንደገና ሊስተካከል አይችልም:: ወደ ኋላ በማፈግፈግና ፈጽሞ በመካድ መካከል ልዩነት አለ:: ክርስቲያኖች ሊያፈገፍጉ ይችላሉ:: ግን አፈግፍገው ወደ መካድ ከደረሱ በመጀመሪያም ዳግመኛ የተወለዱ አልነበሩም ማለት ነው::

5. በዕብ 6:4-8 ላይ የተለጸው ኃጢአት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ከሚሠራው ኃጢአት ጋር ይመሳሰላል:: «... የቀመሱት ...» የሚለው በመዝ 34:8 እንደተገለጸው እግዚአብሔርን ያወቁ ወይም የተለወጠ ሕይወት የነበራቸው ስለሆኑ ነው የሚሉ ናቸው::

ከዚህ በላይ የተነሱትንና ሌሎች ተዛማጅ ነጥቦችን በሁለት ወገን በመክፈል እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል::



ሠንጠረዥ 6

## የዘላለም ዋስትና

| አንድ ጊዜ መዳን ለዘላለም መዳን | ደህንነት ማጣት ሊኖር ይችላል |
|---|---|
| 1 የእግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣኑ፣ ሁሉን ማወቁ፣ አለመለወጡና በዘላለም ዕቅድ መሥራቱ (ሮሜ 9:11-13፣ ዮሐ 15:16፣ ኤፌ 1:4-5፣ ሮሜ 8:29-30፣ ይሁዳ 24፣ 1ጴጥ 1:2) | 1 ሰውም ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶታል፣ ማንም ቢወድ ይድናል (ዘዳ 30:19-20፣ ማቴ 11:28፣ ዮሐ 3:16-18፣ ሮሜ 10:9-19፣ ኢሳ 24:15፣ ሐዋ 10:43፣ ራእ 22:17፣ ሕዝ 18:4፣ 33:11) |
| 2 ክርስቶስ የሞተው ለተመረጡት ነው (1ጢሞ 4:10) | 2 ክርስቶስ የሞተው ለሁሉም ነው (ቲቶ 2:11፣ ዮሐ 3:16፣ ሮሜ 10:13፣ ዮሐ 1:29፣ ዕብ 2:9፣ 1ጢሞ 2:30) |
| 3 ሰው ሲድን አዲስ ፍጥረትና የክርስቶስ አካል ይሆናል፣ በመንፈስ ቅዱስም ይታተማል (ሚክ 3:3፣ 1ቆሮ 5:17፣ ኤፌ 4:30፣ 1:13) | 3 አማኝ ስለ ኃጢአቱ ንስሐ በመግባት ኅብረቱን ያድሳል ያዳነውን ጌታ ካክፋፋ አካል መሆኑን አልፈለገውም (1ዮሐ 1:8-9) |
| 4 ኢየሱስ ክርስቶስ ለአማኞች ይማልዳል፣ መንፈስ ቅዱስም ይቃትታል (ሮሜ 8:34፣ ዕብ 7:24-25፣ ሮሜ 8:26-27) | 4 ወድዶ ኃጢአት ከሰራና በዚያውም ከቀጠለ መንፈስ ቅዱስን ያሳዝል (ዕብ 10:26) |
| 5 ደህንነት በጸጋ ነው፤ የእምነታችን ራስ እርሱ ነው (ቲቶ 3:5፣ ኤፌ 2:8-10፣ ዕብ 12:2፣ ሮሜ 11:5-6) | 5 በደህንነት ውስጥ ሰውም በእምነት የመቀበልና የመኖር ድርሻ አለው (ፊሊ 2:12) |
| 6 ከእግዚአብሔር እጅ ማንም አይነጥቅም (ዮሐ 10:27-30) | 6 ራስን በመግዛትና በቅድስና በመመላለስ በእምነት እንድንኖር ምክሮችና ማስጠንቀቂያዎች ተሰጥተዋል (ቲቶ 2:12-13፣ ዕብ 3:6-14፣ ሮሜ 11:21-22፣ ያዕ 5:19-20፣ 2ጢሞ 2:12፣ 1ቆሮ 10:12) |
| 7 በሩጫ ወይም በመታገል እንደሚሆን አምኖ የካደም ቢሆን የሚያጣው ሽልማት ብቻ ነው፣ ከእሳት እንደሚድን ይሆናል (1ቆሮ 3:15፣ 1ቆሮ 9:24-27) | 7 ያመነውን ከካደና ከንስሐም ካልተመለሰ ለደህንነቱ ማረጋገጫ የለውም (ዕብ 6:4-8) |
| 8 ነፍሳቸው እንዲድን ሥጋቸው ግን ለሰይጣን አልፎ የተሰጡት ምሳሌዎች ይሆናሉ (1ቆሮ 5:3-5፣ 1ጢሞ 1:19-20፣ ሐዋ 5:1-11) | 8 እነዚህ ድንገተኛ ውሳኔዎች ሲሆኑ እግዚአብሔርን ለመፍራትና ለቤተ ክርስቲያን መንጻት (ሐዋ 5:5-11) |
| 9 ዳግመኛ የተወለዱና ፍሬ የነበራቸው ደህንነታቸውን አያጡም፣ ደህንነት የሚያጡት መጀመሪያም ዳግመኛ ያልተወለዱ ስለነበሩ ነው:: | 9 አላውቃችሁም የሚባሉ አሉ ከሕይወት መጽሐፍ መደምሰስም አለ (ማቴ 7:21-23፣ ራእ 3:5፣ ዘጸ 32:32-33) |
| 10 አንድ ጊዜ የዳኑት እስከ መጨረሻው ይጸናሉ:: | 10 አምነው የካዱ ምሳሌዎች ሲሆኑ የሚችሉም አሉ:: በሚያጸናው በእግዚአብሔር በመታመን ለመጽናት አማኙ መትጋት አለበት (2ጴጥ1:10-11፣ 2:1-2፣ ዮሐ6:66፣ 2ጢሞ4:10) |

ችግሮች/ ጥያቄዎች

1 ሰው ነጻ ምርጫ እንዲያደርግ መጠየቁ
2 መትጋት፣ ነቅቶ መጠበቅና መጽናት ማስፈለጉ

3 ዳግመኛ ከመወለድ በኋላ ያለው ኑሮ የሚጠቅመው ለሽልማት ብቻ ከሆነ ቸልተኝነትና ስንፍና ሊያስከትል መቻሉ

ችግሮች/ ጥያቄዎች

1 እግዚአብሔር የወደፊቱን ማቀዱን መምረጡ
2 ደህንነት በሥራ ሳይሆን በእምነት በጸጋ የሚገኝ መሆኑ
3 ደህንነቱ ይጠፋል ብሎ መፍራትና እርግጠኛ አለመሆንን ማስከተሉ

## መ. የእግዚአብሔር ቅድሚያ ዕውቀትና ምርጫ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የቀደመ ዕውቀቱና ምርጫው ብዙ ያስተምራል:: በጥቂቱ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት::

### መ.1. ቅድሚያ ዕውቀት (ውሣኔ)

- «በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ...» (ሐዋ 2:23)
- «አስቀድሞ ያወቃቸውን... አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና... አስቀድሞ የወሰናቸውን...» (ሮሜ 8:29)::
- «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም...» (ሮሜ 11:2)::
- «እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን...» (1ቆሮ 2:7)::
- «ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን ... በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን» (ኤፌ 1:5)::
- «እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው... ለተመረጡት...» (1ጴጥ 1:1-2)::
- «ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ» (1ጴጥ 1:20)::

እነዚህንና ሌሎችም ተመሳሳይ ጥቅሶች የሚያመለክቱት እግዚአብሔር የወደፊቱን አስቀድሞ የሚያይና የሚያውቅ መሆኑን፣ እንዲሁም ስለወደፊቱ ሙሉ ሥልጣን ያለው አምላክ እንደሆነ ነው::

እግዚአብሔር የወደፊቱን ማወቁን ከትንቢቶችም መገንዘብ ይቻላል::

1. ወደፊት የሚሆነውን የሚገልጹ ትንቢቶች

እንደዚህ ዓይነት ትንቢቶች ድርጊቶች ከመሆናቸው በፊት የሚነገሩና ጊዜያቸውን ጠብቀው መከናወናቸው የማይቀር ነው:: ለዚህም በኢሳ 46:10 «በመጀመሪያ መጨረሻውን ከጥንትም ያልተደረገውን እናገራለሁ ምክሬም ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ አፈጽማለሁ» ይላል:: እንዲሁም በኢሳ 48:3 «የቀድሞውን ነገር ከጥንት ተናግሬአለሁ... ተፈጽሞአል» ይላል:: ወደፊት ሊሆን ያለውን ሙሉ በሙሉ ስለሚያውቅ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ስለወደፊቱና ስለሚመጣው ነገር ይናገራል:: የተናገረውም በሙሉ ይፈጸማል::

2. ሊሆን ያለውን የሚያሳውቁና ሁኔታው ቶሎ እንዲስተካከል የሚመክሩ ትንቢቶች

እንደዚህ ዓይነት ትንቢቶች እንደሌሎቹ ሁሉ መከናወናቸው እርግጠኛ ቢሆንም መፈጸማቸው ግን የሚወሰነው በተነገረለት ሰው (ሕዝብ) አቀባበል ነው:: ለዚህም ኤርሚያስ በ8:8 «ስለ እርሱ የተናገርሁበት ሕዝብ ከክፋቱ ቢመለስ እኔ አደርግበት ዘንድ ካሰብኩት ክፉ ነገር እጸጸታለሁ» ይላል:: በተመሳሳይ ሁኔታ በነቢዩ በዮናስ



በኩል ነነዌ በሦስት ቀን ውስጥ እንደምትገለበጥ ትንቢት የተነገረ ቢሆንም ሕዝቡ ግን ንስሐ በመግባታቸው የተነገረው ጥፋት አልተፈጸመም (ዮናስ 3:1-10)::

### መ.2. የእግዚአብሔር ምርጫ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው እግዚአብሔር ሕዝብንና ሰውን ይመርጣል:: አንዳንድ ጊዜም ምርጫው የተደረገው የተመረጠው ሰው ገና ሳይወለድ እንደነበርም ይናገራል::

1. የእስራኤል መመረጥ

«አባቶችህን ወድዶአልና ከእነርሱ በኋላ ዘራቸውን መረጠ» (ዘዳ 4:37)

2. የሰዎች ለአገልግሎት መመረጥ

- ሙሴ - «ና... እልክሃለሁ» (ዘጸ 3:10)::
- ሶምሶን - «ልጁም... ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናልና...» (መሳ 13:5)::
- ሳዖል - «ያ የነገርሁህ ሰው እነሆ...» (1ሳሙ 9:17)::
- ዳዊት - «ንጉሥ አዘጋጅቻለሁና... እግዚአብሔርም ይህ ነውና ተነስተህ ቀባው አለ» (1ሳሙ 16:1-13)::
- ኤርሚያስ - «በሆድ ሳልሰራህ አውቄሃለሁ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ» (ኤር 1:4-5)::
- ያዕቆብ - «... ልጆቹ ገና ሳይወለዱ በጎ ወይም ክፉ ምንም ሳያደርጉ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ ለእርስዋ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለለት» (ሮሜ 9:11-12)::
- 12ቱ ደቀመዛሙርት - «... ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ» (ማር 3:13)::

3. ለደህንነት መመረጥ

- አብርሃም - «አንተ እግዚአብሔር አምላክ ነህ አብራምን መረጥህ» (ነህ 9:7፣ ኢሳ 1:8)::
- አማኞችን - «... በክርስቶስ መረጠን» (ኤፌ 1:4)::

## ሠ. የክርስቶስ የሁሉም አዳኝነትና የሰው ነጻ ፈቃድ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው ለጥቂት ኃጢአተኞች ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሁሉ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል::ከዚህም ጋር ማንም ቢወድ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ደህንነት እንዲያገኝ ነጻ ምርጫ ተሰጥቶአል::

ሠ.1. <u>የክርስቶስ አዳኝነት</u>

- በ1ጢሞ 4:10 እንደምንመለከተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ሁሉ የሚያድን (የሰው ሁሉ አዳኝ) መሆኑን ያመለክታል::
- «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» ሮሜ 10:13::
- በዮሐ 3:16 እንደምናነበው ጌታ የሞተው ለዓለም ሁሉ ነው:: በእርሱ የሚያምን ሁሉ ደግሞ ይድናል::
- ኢየሱስ ክርስቶስ «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ተብሏል (ዮሐ 1:29)::
- «ሁሉም በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና» 1ቆሮ 15:22፣ ሮሜ 5:18-19::
- ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን የቀመሰው ስለ ሰው ሁሉ ነው ዕብ 2:9::
- «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ እግዚአብሔር» (1ጢሞ 2:3፣ ቲቶ 2:11)::
- ጌታችን ከመመለስ መዘግየቱ «... ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ» ነው (2ጴጥ 3:9)::

ሠ.2 <u>እያንዳንዱ ሰው ነጻ ፈቃድ/ ውሣኔ አለው</u>

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ነጻ አድርጎ ፈጥሮታል:: ሰውንም የሞትና የሕይወት አማራጮችንና ውጤቶችን ከማሳየት አልፎ በግድ ትክክለኛ የሆነውን እንዲወስን አያስገድድም:: ስለዚህ ሰው ለሚከተለው መንገድ ወይም ለሚያደርገው ውሣኔ ተጠያቂ ነው ::

እግዚአብሔር ለሰዎች ነጻ ፈቃድ መስጠቱንና በምርጫውም የሚሄድ መሆኑን ከሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

- «... አትብላ በበላህ ቀን ...» (ዘፍ 2:17)::
- «... አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ ... ምረጥ» (ዘዳ 30:19-20)::
- (የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ እኔና ቤቴ ግን ... » (ኢያሱ 24:15)::
- «እስከ መቼ ድረስ በሁለት ሀሳብ ታነክሳላችሁ?» (1ነገ 18:21)::
- «ኃጢአትን የምትሰራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች» (ሕዝ 18:4)::
- «ተመለሱ፣ ተመለሱ ስለምን ትሞታላችሁ» (ሕዝ 33:11)::
- «ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» (ማቴ 11:28)

ረ. ማስጠንቀቂያዎች

አማኞች አንድ ጊዜ ጌታን ካመኑ በኋላ የማይመለሱ የማይክዱ ወይም የዘላለምን ሕይወት የማያጡ ቢሆን ኖሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ማስጠንቀቂያዎች ምናልባት ባላስፈለጉ ነበር:: በእነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ላይ የአተረጓጐም ልዩነት ሊኖር ቢችልም በአጠቃላይ ግን አማኞች በክርስትና ሕይወት በተገቢው ሁኔታ



መኖር እንዳለባቸውና ለደህንነታቸውም መጠንቀቅ እንደሚያስፈልጋቸው ያስገነዝባል ከእነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

- «በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት ባንተ ላይ ነው ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ» (ሮሜ 11:22)::
- «እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (1ቆሮ 10:12)::
- «በሰማችሁትም ወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል» (ቆላ 1:23)::
- «ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል» (ዕብ 2:1)::
- «የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናል» (ዕብ 3:14)::
- «ዳተኞች እንዳትሆኑ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ» (ዕብ 6:11)::
- «የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መስዋዕት አይቀርልንምና የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ» (ዕብ 10:26-27)::
- «እናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን የኃጢአትንም ብዛት እንዲያሸንፍ ይወቅ» (ያዕ 5:19-20)::
- «ብንጸና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሳለን ብንክደው እርሱ ደግሞ ይክደናል» (2ጢሞ 2:12)::

በአጠቃላይ እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች የሚያመለክቱት እያንዳንዱ አማኝ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ እስከ መጨረሻው መጽናት እንዳለበት ነው::

ሰ. <u>ማገናዘቢያ</u>

እላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች መሠረት በማድረግና መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ እንደማይቃረን በማመን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል::

1. እግዚአብሔር ይመርጣል ግን በቅድመ ዕውቀት ነው (ሮሜ 8:29፣ 2ተሰ 2:13፣ 1ጴጥ 1:1-5)::
2. እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅና የማያደላ ነው (ሐዋ 10:34፣ ሮሜ 2:11፣ ኤፌ 6:9፣ ቆላ 3:25፣ 1ጴጥ 1:1)::
3. ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለኃጢአተኞች ሁሉ ነው (ዮሐ 1:29፣ ዮሐ 3:16፣ 1ጢሞ 4:10፣ ዕብ 2:9)::
4. ሰው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ይድን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (1ጢሞ 2:3፣ ቲቶ 2:11፣ 2ጴጥ 3:9)::
5. ሰው መዳኑን የሚያረጋግጠው እስከ መጨረሻ ጸንቶ በመቆሙ ነው (ማቴ 7:15-20፣ ዮሐ 8:31፣ ዕብ 3:6-24፣ 1ዮሐ 2:18-19)::
6. ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ቅዱሳን ሁልጊዜ ይማልዳል (ዮሐ 11:42፣ 17:11፣ ሮሜ 8:34፣ ዕብ 7:25)::

7. አማኞች በመንፈስ ቅዱስ የታተሙ ናቸው (2ቆሮ 1:22፣ ኤፌ 1:13፣ ኤፌ 4:30)::
8. የእግዚአብሔር ዓላማና ኃይሉ እጅግ ታላቅ ነው (ዮሐ 10:27-30፣ 11:26፣ ሮሜ 8:29-30፣ ኤፌ 1:4፣ ፊሊ 1:6፣ 1ጢሞ 1:12፣ 4:18፣ 2ጢሞ 1:12፣ ይሁዳ 24)::
9. ሰው የራሱን ምርጫ እንዲያደርግ ነጻነት ተሰጥቶታል (ዘዳ 30:19-20፣ ሕዝ 18:4፣ 33:11፣ ማቴ 11:28)::
10. የተመረጠ ወይም የተጠራ ሰው ከፊት ይልቅ ሊጸና እንጂ ለኃጢአትና ለስንፍና በር ሊከፍት አይገባውም (2ጴጥ 1:10)::
11. እምነው እንደገና የካዱ ምሳሌዎችም ተጠቅሰዋል (1ጢሞ 1:19-20፣ 2ጢሞ 2:17-18፣ 4:10፣ 2ጴጥ 2:1-2)::
12. ነቅቶ መጠበቅ፣ መጸለይ፣ መትጋት አስፈላጊ ነው:: ለመጽናት አማኙም ድርሻ አለው:: ያለዚያ አማኞች የማይወድቁ ቢሆኑ ኖሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማስጠንቀቂያዎች ምናልባት ባላስፈለጉ ነበር (ሮሜ 11:21-22፣ ቆላ 1:21-23፣ ዕብ 6:4-9፣ 10:26-29፣ 1ዮሐ 2:19፣ ራእ 22:19)::

ሸ. ስለዚህ

ሀ. እግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣን ያለው አምላክ በጽድቅና በቅድመ እውቀቱ ይመርጣል:: ማን እንደተመረጠ ግን በሰው ዘንድ የሚታወቅ አይደለም::
ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለዓለም ሁሉ ነው:: ማንም ቢወድ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የዘላለም ሕይወት እንዲወርስ ግብዣ/ ጥሪ ተደርጓል:: ምርጫው የእያንዳንዱ ሰው ይሆናል::
ሐ. የአማኞች የዘላለም ደህንነት በእግዚአብሔር ማንነትና ሥልጣን የተጠበቀ ነው:: ነገር ግን አማኞች በእምነት ጸንተው ሊኖሩ ይገባቸዋል:: እስከ መጨረሻው የሚጸና ይድናል::

## ቀ. ማጠቃለያ

በጆን ካልቪንና በጃኮብ አርሜንየስ መካከል የተጀመረውና ለብዙ ዓመታት የቀጠለው ውይይት (ክርክር) እንደዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ መረዳት:-

- ሁለቱም ትንታኔያቸውን የመሠረቱት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው፣
- ሁለቱም ትክክል ነው ብለው ያሰቡትን ለመግለጽ ብዙ ተግተዋል፣
- ሁለቱንም ወገኖች የሚደግፉ ወገኖች የደገፉትን ወገን ትክክለኛነት ለማሳየት ለብዙ ዓመታት «በቅንነት» ሲጥሩ ይታያሉ::

ይሁን እንጂ:-

- ሁለቱ ወገኖች አንድ መረዳት ላይ ሊደርሱና ሊስማሙ ያልቻሉት መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት የተለያየና እርስ በርስ የማይስማሙ ሀሳቦችን ስለያዘ ሳይሆን የሰው መረዳት ውስን በመሆኑ ነው::

ስለሆነም ይህ ጸሐፊ ለአንባቢያን ማስገንዘብ የሚፈልገው:-



1. ጆን ካልቪንና ጃኮብ አርሜንየስ ያቀረቧቸው ትንታኔዎች ብዙ ጸሐፊዎች ለዓመታት ለመጻፍ እንደሞከሩት «ጉራ የለዩ» የሥነ መለኮት አመለካከቶች ሳይሆኑ አብረው ተደጋግፈውና ተያይዘው አንድ «ሙሉ እውነት» የሚሰጡ ትንታኔዎች መሆናቸውን፣

2. መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ያለው የጆን ካልቪንን ወይም የጃኮብ አርሚኒየስን ትንታኔ በተናጠል በመውሰድ ሳይሆን ሁለቱንም በአንድነት በመውሰድና በጥንቃቄ በማዋሃድ ወይም «ሚዛናዊ መረዳት» ላይ በመድረስ መሆኑን፣

3. እላይ በተራ ቁ.2 የተገለጸው «ሚዛናዊ መረዳት» ላይ መድረስ የሚቻለው ደግሞ በእግዚአብሔር ቅድሚያ እውቀትና የሰው ነጻ ፈቃድ፣ በምርጫና በመጽናት፣ አንድ ጊዜ መዳን ለዘላለም መዳን ወይም ደኅንነትን መጣት ሊኖር ይችላል በሚሉና በሌሎችም ክበድ ባሉ ርዕሶች ላይ በዚህ መጽሐፍ 6.2.5 «ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞዎች» የተገለጸውን ዓይነት ሚዛናዊ ትንታኔ በማድረግ እንደሆነ፣ እና

4. የሰው መንፈሳዊ መረዳቱ የቱንም ያህል የመጠቀ ቢሆን እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀውና ሰው ግን ገና የማያውቀው ወይም በድንግዝግዝ ብቻ የሚያየው ብዙ እውነት እንዳለ በመገንዘብ በእግዚአብሔር ፊት በትሕትና መመላለስ እንደሚገባ ነው::

በመጨረሻም የአማኙ የዘላለም ሕይወት በእግዚአብሔር ማንነትና ሥልጣን የተጠበቀ ነው:: እግዚአብሔር የጀመረውንም ይጨርሳል:: ነገር ግን አማኙ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር መተባበር አለበት:: እግዚአብሔርን እየመሰለ መመላለስና በመጀመሪያው እምነት ጸንቶ በመኖር ፍሬ ማፍራት ከአማኙ ይጠበቃል::

## ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን::

ክፍል 2

TWO VIEWS ON SALVATION AND ETERNAL SECURITY OF THE BELIEVER[76]

John Calvin
1. Total depravity
2. Unconditional election
3. Limited atonement
4. Irresistible grace
5. Perseverance of the Saints

James (Jacob) Arminius
1. Man is a sinner & needs grace
2. God's election based on foreseen faith.
3. Atonement of Christ was universal.
4. God's grace is resistible and it is to all.
5. Probably true believers can loose their faith and loose their salvation

EXPLANATIONS

A . JOHN CALVIN

1. Man through Adam has inherited the guilt of Adam's sin and can do nothing for his own salvation because his will is totally corrupted.
2. Salvation is unconditional election apart from human merit or divine foreknowledge. Election is based on the sovereign will of God and is a dual: Predestination of some to salvation and others to condemnation.
3. The work of Christ on the cross is limited to those elected to salvation.
4. The elect will be saved apart from their own initial desire as the Holy Spirit irresistably draws them to Christ.
5. Those elect who are irresistibly saved by the work of the Holy Spirit will never be finally lost

B JACOB ARMINIUS

1.Man is under the wrath of God. But man was able to initiate his salvation after God had granted him the primary grace to enable his will to cooperate with God.
2. There is election, but the decree to save some and damn others has "its foundation in the foreknowledge of God." This election was conditional rather than unconditional.
3. Christ's death was suffiecient for all but that it is was efficient only for believers.
4. Men might resist the saving grace of God.
5. God would give the saint grace so that they need not fall but that the scripture seemed to teach that it was possible for man to fall away from salvation.

---

76 Adapted from, Earle E. Cairns, Christianity through the Centuries A History of the Christian Church (Revised Ed.), 1981, Zondervan Publishing House, Grand Rapids PP. 310-311, 324-325.